SR&R እንግሊዝኛ

# 2022–2023

## የተማሪ መመሪያ

# መብቶች እና ኃላፊነቶች

## በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

www.montgomeryschoolsmd.org

የፌዴራል እና የስቴት ሕጎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ፖሊሲ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳደራዊ ደንቦች እና ሌሎች መመሪያዎች ሊለወጡና እና በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን መግለጫዎች እና ማጣቀሻዎች ሊተኩ ይችላሉ።

የተማሪ ስም ______________________________

አድራሻ ______________________________

ስልክ ______________________________

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

## VISION ራእይ

ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ መማርን እናበረታታለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ ተማሪ በኮሌጅ እና በሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በአካደሚክስ፣ ችግር የመፍታት ዘዴ/ ብልሃት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክህሎቶች ይኖሩታል/ ይኖሯታል።

## ዋና ዓላማ

ሁሉንም ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸው እንዲዳብር/ እንዲበለጽግ ማዘጋጀት፡ ፡

## ዋነኛ እሴቶች

መማር/እውቀት
ግንኙነቶች
አክብሮት
ልቀት
ፍትኃዊነት/ሚዛናዊነት


Board of Education የትምህርት ቦርድ

Ms. Brenda Wolff ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ
President ፕሬዚደንት

Ms. Karla Silvestre ሚ/ስ ካርላ ሲልቬስትሬ
Vice President ም/ፕሬዚደንት

Dr. Judith R. Docca ዶ/ር ጁዲት አረ. ዶካ

Mrs. Shebra L. Evans ወ/ሮ ሼብራ ኤል. ኢቫንስ

Ms. Lynne Harris ሚ/ስ ለይኔ ሃሪስ

Dr. Scott Joftus ዶ/ር ስኮት ጆፍተስ

Mrs. Rebecca K. Smondrowski ወ/ሮ ርብቃ ኬ. ስሞንድሮውስኪ

Mr. Arvin Kim ሚ/ር አርቪን ኪም
Student Member ተማሪ አባል

Montgomery County Public Schools (MCPS) Administration
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አስተዳደር

Monifa B. McKnight, Ed.D. ሞኒፋ ቢ. መክነይት ዶ/ር
Superintendent of Schools የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

Mr. M. Brian Hull ሚ/ር ኤም. ብረያብ ሁል
Chief Operating Officer ዋና የሥራ ኃላፊ

Patrick K. Murphy, Ed.D. ፓትሪክ ኬ. መርፊ ዶ/ር
Deputy Superintendent ምክትል ሱፐርኢንተንደንት

Mr. Brian S. Stockton ሚ/ር ብረያን ኤስ. ስቶክተን
Chief of Staff ዋና የሠራተኞች አስተዳደር ኃላፊ

Mrs. Stephanie P. Williams ወ/ሮ ስቴፈኒ ፒ. ዊልያምስ
General Counsel ጀነራል ካውንስል

Ms. Elba M. Garcia ሚ/ስ ኤልባ ኤም. ጋርሽያ
Senior Community Advisor ዋና የማህበረሰብ ጉዳይ አማካሪ

Dr. Patricia E. Kapunan ዶ/ር ፓትሪሽያ ኢ. ካፑናን
School System Medical Officer የትምህርት ቤቶች ጤና ጥበቃ ኃላፊ



850 Hungerford Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# 2022–2023

## የተማሪ መመሪያ

# መብቶች እና ኃላፊነቶች

## በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

www.montgomeryschoolsmd.org

ይህ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መመሪያ በእንግሊዝኛ፣ በስፓኒሽኛ፣ በፈረንሣይኛ፣ በቻይንኛ፣ በኮሪያንኛ፣ በቬትናምኛ፣ በአማርኛ እና በፖርቱጋልኛ በ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ላይ ይገኛል www montgomeryschoolsmd.org/students/rights/

ስለ መብቶች እና ኃላፊነቶች የተማሪ መመሪያ (በእንግሊዝኛ)
Student's Guide to Rights and Responsibilities (English)

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

© ሰፕተምበር 2022
Montgomery County Public Schools
Rockville, Maryland

ሰፕተምበር 2022

ውድ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና የሥራ ባልደረቦች

2022–2023 በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ይህንን የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች መመሪያ ሳቀርብ ደስታ ይሰማኛል። የዚህ ሰነድ አላማ ስለ ስቴት እና የፌደራል ህጎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች እና ህጎች፣ እና ሌሎች ተማሪዎችን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ጠቃሚ መረጃ ማቅረብ ነው። ፖሊሲዎች እና ደንቦች ውጤታማ እና በሥርዓት በሚተዳደር ተቋማት ውስጥ አስፈላጊ ሲሆኑ፣ ተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦችን ከወረርሽኙ በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን በፍትሃዊነት፣ በተገቢ ግንዛቤ እና በመረዳት መተግበራችን አስፈላጊ ነው። በኮቪድ-19 የተቀሰቀሱ እና በቤተሰቦች፣ቢዝነሶች እና ትምህርት ቤቶች ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ በማህበረሰባችን ውስጥ ቀጣይነት ያለው ውጥረትና ሥጋት ይፈጥራል። ተማሪዎችን መደገፍ፣ በሚያስፈልግበት ጊዜ ለእነርሱ ምንጮችን ማግኘት እና የአኗኗር ልምዳቸውን ለመረዳት ቀልጣፋ መሆን አለብን።

ከማህበረሰብ ጋር መተማመንን መፍጠር፣ የአእምሮ ጤና እና ደህንነትን ማረጋገጥ እና ለሁሉም ተማሪዎች ፍትሃዊ ትምህርት ላይ ትኩረት ማድረግ በዚህ አመት ጥረታችን ላይ ትኩረት ለማድረግ እንዲረዳን ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ያቀረብኩበት አንዱ ምክንያት ነው። ይህ የተማሪዎች የመጀመሪያ አካሄድ ተማሪዎቻችን ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ጋር በሚያደርጉት የትምህርት ጉዞ የምንደግፋቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ይህ ሰነድ የሚያረጋግጥላቸው መመሪያ መሆን አለበት።

MCPS በፖሊሲ JFA፣ የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች ለተቀመጠው የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ራዕይ፣ የአእምሮ እድገትን፣ ዜግነትን፣ ሃላፊነትን እና በሰራተኞች እና ተማሪዎች መካከል መከባበርን ለማጎልበት በማስተማር እና በመማር ላይ ለሚሳተፉ ማህበረሰብ የተነደፈ መመሪያ መሆኑ ቁርጠኛ ነው። የትምህርት ቤት ማህበረሰባችን አባላት በሙሉ ለሁሉም ተማሪዎች፣ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እና ለሠራተኞች ለመማር አስፈላጊውን ክብር፣ አካባቢን የመጠበቅ፣ የማክበር እና የመደገፍ ኃላፊነቱን ይጋራሉ።

ከመልካም ወዳጅነት ጋር

Monifa B. McKnight

# ጉዳዩ፡-


ፈጣን መመሪያ . . . iii
መግቢያ . . . 1
ነፃ ህዝባዊ ትምህርት . . . 1
የተማሪ ተሳትፎ . . . 1
የግል ገበና የመጠብቅ መብቶች . . . 1
myMCPS Classroom . . . 2
ትምህርት ላይ መገኘት . . . 2
የተፈቀደ መቅረት . . . 2
ያልተፈቀደ መቅረት . . . 2
በቀሩበት ጊዜ ያመለጠ ስራ . . . 2
የክፍል ሥራ . . . 3
ማርክ አሰጣጥና ሪፖርት . . . 3
የላቀ ችሎታ-Honors፣ ከፍተኛ-ደረጃ፣ እና የላቀ ደረጃ ምደባ - Advanced Placement (AP) ኮርሶች . . . 3
በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የተወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች . . . 3
የተማሪ የሥራ አገልግሎት ትምህርት - Student Service Learning . . . 4
የተማሪ አመራር - Student Government . . . 4
ተሳትፎ . . . 4
የፋኩልቲ ድጋፍ . . . 4
የተማሪ አመራር ስልጣን . . . 4
የመጠየቅ እና ኃሳብን የመግለጽ ነፃነት - Freedom of Inquiry and Expression . . . 4
ንግግር . . . 4
ስብሰባ . . . 4
አቤቱታዎች . . . 4
ሕትመቶች፣ ትግባሬዎች፣ እና መረጃዊ ቁሳቁስ . . . 4
የፖለቲካ ቁሳቁሶች . . . 5
በፖሊቲካ ውድድሮች ላይ መሣተፍ . . . 5
የአገር ወዳድነት-የዜግነት መገለጫዎች . . . 5
የሐይማኖት ነፃነት . . . 5
ክለቦች፣ ቡድኖች፣ እና የተማሪ ድርጅቶች . . . 6
ት/ቤት የሚያንቀሳቅሳቸው ድርጅቶች . . . 6
ት/ቤት የማያንቀሳቅሳቸው የተማሪ ድርጅቶች . . . 6
ስለ አለባበስ እና መዋብ . . . 6
ቴክኖሎጂ . . . 6
ሃላፊነት የተሞላበት የተማሪ መመርያዎች አጠቃቀም . . . 6
የግል ተንቀሳቃሽ መገልገያዎች . . . 6
ፀረ-መድሎአዊነት . . . 7
ጉልበትን ተጠቅሞ ሌሎችን መጉዳት፣ ጭቆና-በደል-ጥቃት፣ ወይም ማስፈራራት . . . 7
ጾታዊ/ወሲባዊ ትንኮሳ . . . 8
የተማሪ ሪኮርዶች . . . 8
ፍተሻ እና መውረስ . . . 8
የትምህርት ቤት ደህንነት እና ሠላም . . . 9
በስቴት ተፈላጊ የሆኑ የሕክምና ጣልቃ ገብነቶች . . . 10
አለርጂ ስለሚቀሰቅሱ ነገሮች ግንዛቤ (Anaphylaxis Awareness) . . . 10
ስለ ስኳር በሽታ ግንዛቤ . . . 10
ስለ ናሎክሰን እና ኦፒዮድ ግንዛቤ - Naloxone and Opioid Awareness . . . 10
መጓጓዣ-ትራንስፖርቴሽን . . . 10
ጤንነት-ደህንነት . . . 11
ስለ ተማሪ ሰንስክሪን አጠቃቀም - Student Sunscreen Use . . . 11
ራስን ስለማጥፋት ግንዛቤ - Suicide Awareness . . . 11
የህክምና አሰጣጥ . . . 11
የተማሪ ሥነ ምግባር ደንብ 11
MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ኮድ . . . 11
ማህበራዊ ሚዲያ፡- ለሠራተኞች መልካም ተሞክሮዎች - Best Practices for Employees . . . 11
የይግባኝ- ቅሬታ አቀራረብ ቅደምተከተል -የአፈጻጸም ሂደት . . . 12
በት/ቤት ደረጃ ውሳኔ . . . 12
በርእሰመምህር ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለመጠየቅ . . . 12
ውሳኔ ይግባኝ መጠየቅስለ ፋይናንስ እና የሥራ ሂደት ዋና ኃላፊ . . . 12
አባሪ (ተጨማሪ መረጃዎች)—MCPS Regulations . . . 13–15
የቃላት ትርጉም - መፍቻ እና ማስታወሻዎች . . . 16

# ፈጣን የማገናዘቢያ መመሪያ
# የተማሪዎች መገልገያዎች

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ለድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመሮች
### 24 ሰዓት መረጃ፣ ወደሚመለከታቸው ማስተላለፍ እና ድጋፍ ሰጪ ውይይት

Maryland Crisis Hotline/EveryMind/ . . 301-738-2255 and https://www.every-mind.org/
በድረ-ገጽ ላይ ሰራተኛ የሚያነጋግሩበት የስልክ መስመር እና 24 ሰዓት የውይይት አገልግሎት ክፍት መስመር።

Montgomery County Crisis Center - የሞንትጎመሪ ካውንቲ የድንገተኛ ሁኔታ ማእከል 240-777-4000
የድንገተኛ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች ድንገተኛ የስልክ ጥሪ መስመር፡-
Youth Crisis Hotline of Montgomery County
301-738-9697
24 ሰዓት በስልክ ነቅቶ የማዳመጥ እና ሪፈራል አገልግሎት በሰለጠኑ ካውንስለሮች አማካይነት የምስጢር አገልግሎት ድጋፍ ይሰጣል።

## የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡-

MCPS ሲስተም አቀፍ የአደጋ ጊዜ ማኔጅመንት ዲፓርትመንት
240-740-3066
የ MCPS ትምህርት ቤቶችን እና ድ/ቤቶችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው የ MCPS ቢሮ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የተማሪ ደህንነት እና ህግ ማክበር፡- SWC@mcpsmd.org or TitleIX@mcpsmd.org . 240-740-3215
የ MCPS ዲስትሪክት አቀፍ የ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ግንኙነት ኃላፊ። የተማሪ ደህንነት እና ስርአት ማክበር ድረ-ገጽ https://www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/. SWC ከትምህርት ቤቶች፣ ከጀነራል ካውንስል ጽ/ቤት እና ከሌሎች የ MCPS ጽ/ቤቶች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር እንደ ፖሊሲዎች ፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች፣ ከሰዎች ግንኙነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ከመተግበር አኳያ፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (Title IX ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ እና ማስፈራራት፣ የሕፃናትን በደል እና ቸልተኝነትን መገንዘብ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻና-አድሏዊነት፣ የጥላቻ እና የተማሪ የጾታ ማንነት ጉዳዮችን በሚመለከት ከላይ ከተጠቀሱት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ይሠራል።

MCPS Cyber Safety dropbox፡- CyberSafety@mcpsmd.org
በ MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔትዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር -
Cyber Tipline 1-800-843-5678
ለወሲባዊ ድርጊቶች፣ ከቤተሰብ ውጭ ያለ ልጅ ወሲባዊ ጥቃት፣ የልጆች ወሲባዊ ሥዕሎች፣ የልጆች ወሲባዊ ቱሪዝም፣ የሕፃናት ወሲባዊ ዝውውር፣ ሳያስፈልግ ወደ ትንሽ ልጅ የተላኩ ጸያፍ ቁሳቁሶች፣ አሳሳች ልዩ ስሞችን መጥራት፣ አሳሳች ቃላት ወይም ዲጂታል በይነመረብ ላይ ምስሎችን መለጠፍ የመሣሰሉትን ጥርጣሬዎች ሪፖርት ማድረጊያ 24/7 ክፍት መስመር።

ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ የስልክ መስመር
Safe Schools Maryland Hotline . . . 833-MD-B-Safe (833-632-7233)
የ 24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስለ ክስተቶች መረጃ ሪፖርት ሲደረግ የደዋዩን ስም -ሳይገለጽ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ለሚመለከታቸው ቢሮዎች ይደርሳል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት፣ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (24 ሰዓት) 240-777-4417 ወይም 240-777-4815 TTY
የተጠረጠረን የሕፃናት በደል ወይም ቸልተኝነት ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎቶች ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር ክፍት ይሆናል።

ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎቶች 240-777-3000፣ 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የጎልማሶችን መበደል እና ቸልተኝነት ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የስልክ መስመር

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ መምርያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ፡- 240-773-5400
በልጆች እና በጎልማሶች ላይ የወሲብ ወንጀሎችን፣ በሕጻናትን ላይ አካላዊ በደል መፈጸም፣ ከቤት ሽሽት፣ የጠፉ ልጆችን፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃትን፣ የአዛውንቶችን በደል/ተጋላጭ የአዋቂዎችን በደል፣ እና የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን የፈጸሙ ግለሰቦች የምዝገባ ጥሰቶችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ ፡-
የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች የጥቆማ መስመር። . . 240-773-ወሮበላ (GANG (4264) ወይም 240-773-አደንዛዥ እፅ (DRUG) (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ህገ -ወጥ የአደንዛዥ ዕፅ/የወንበዴ እንቅስቃሴዎችን መረጃ ማንነትን ሳያሳውቁ ጥቆማ ለመተው 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

## የ MCPS ሪሶርሶች

ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership

ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች 240-740-4692

ተማሪ የቦርድ አባል
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx

የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ፡- 240-740-3030

የአከባቢ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንቶች፣ የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ 240-740-3100

የአከባቢ ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት፣ የተማሪ እና የቤተሰብ ድጋፍ እና ተሳትፎ 240-740-5630

ስለ ሰክሽን 504 ውሳኔ እና አፈጻጸም 240-740-3230

## የሞንትጎመሪ ድንገተኛ ያልሆነ ሪሶርሶች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ አስቸኳይ ላልሆነ ጥሪ የስልክ መስመር 301-279-8000

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና  የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ውጭ240-777-0311

## የ MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org
አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎች ለማግኘት፡-

ትዊተር፡- MCPS on Twitter . . www.twitter.com/mcps

ትዊተር በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español www.twitter.com/mcpsespanol

ፌስቡክ፡- MCPS on Facebookwww.facebook.com/mcpsmd

ፌስቡክ በስፓንሽኛ፡- MCPS en Españolwww.facebook.com/mcpsespanol

የማስጠንቀቂያ መልክቶች፡-
Alert MCPS www.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

## የ MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፈጣን መልክቶች፣ ኢሜይል መልክቶች እና ዘገባዎች - MCPS QuickNotes Email Messages and Newsletter . . . . www.mcpsQuickNotes.org

የ MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ፦
ስልክ . . . . . . . . . . . . . . .240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር 240-740-2845
Email . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

የ MCPS የህዝብ መረጃ ቢሮ 240-740-2837
MCPS Television www.mcpsTV.org;ቴሌቪዥን Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36
በድምፅ የተቀረጸ የአደጋ ጊዜ እና የአየር ሁኔታ መረጃ . . . . . . . . . . .301-279-3673

## የ MCPS ሪሶርሶች ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኝት፦

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የት/ቤት ዝርዝር ማውጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሰራተኞች ዝርዝር ማውጫ

MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ

አትሌቲክስ

Be Well 365

የትምህርት ቦርድ
B The One

ጉልበት መጠቀም፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት

የአውቶቡስ መስመሮች

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል

የግንዛቤ ጥበብ ትምህርት
Common Sense Education

የኮርስ ጥንቅር መግለጫ

የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety

የዲፕሎማ መስፈርቶች

ወሮበሎች እና የወሮበሎች እንቅስቃሴ

## የ MCPS ሪሶርሶች ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መገለጫ መመሪያ

የምሣ ዝርዝር

የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ግምገማዎች

myMCPS Classroom

ፀረ-መድሎ

በኦንላይን የመመረቂያ ፈለግ

የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት

መርኖች እና ደንቦች

ስነልቦናዊ አገልግሎቶች

የተማሪ ፐርሶኔል አገልግሎቶች

የልጅ መበደል እና በቸልተኝነት የተተወ ሁኔታን ሪፖርት ማደረግ

ፍትኃዊ ተሐድሶ

በት/ቤት የካውንስሊንግ አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ደህንነት

ፆታዊ ጥቃት

የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ - Social Media Digital Citizenship

ልዩ ትምህርት

ልዩ ፕሮግራሞች

ስልታዊ የፕላን ዝግጅት

የተማሪ የስነ-ምግባር ደንብ

የተማሪ በኤሌክትሮኒክ ሚዲያ መማር - eLearning

የተማሪ ገመና የመሸፈን መብት

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

ራስን መግደል መከላከል

የሰመር ትምህርት

# መግቢያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በትምህርት ሂደት ላይ ሲሳተፉ በተማሪዎች እና በሠራተኞች መካከል የአዕምሯዊ እድገትን፣ ዜግነትን፣ ኃላፊነትን እና የጋራ መከባበርን ለማጎልበት የተነደፈ የትምህርት ማህበረሰብን ለመገንባት ይጥራል። የዚህ ማህበረሰብ አባላት እንደመሆንዎ፣ ሁሉም ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ  የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ፖሊሲዎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች፣ እና የስቴት እና የፌደራል ህጎች በተቀመጡት መሰረት የተወሰኑ መብቶች፣ ኃላፊነቶች እና ልዩ መብቶች አሏቸው።

ተማሪዎች ለራሳቸው ትምህርት፣ ለግል ስነምግባራቸው እና ስለ መብቶቻቸው አጠቃቀም ኃላፊነት አለባቸው። በትምህርት ማህበረሰብ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ይጠበቅባቸዋል፤ ድርጊታቸው የሚያስከትለውን መዘዝ መቀበል፤ እና ህጎችን፣ የቦርድ ፖሊሲዎችን እና የ MCPS ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያከብራሉ። የተማሪ መብቶች ሁል ጊዜ ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችን፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን እና የማህበረሰብ አባላትን ጨምሮ ሌሎች ሰዎች ካላቸው ሕጋዊ መብቶች እና ኃላፊነቶች ጋር የተገናዘበ መሆን አለባቸው።

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ተማሪዎችን የሚነኩ የስቴት እና የፌዴራል ሕጎች፣ የቦርድ ፖሊሲዎች፣ የ MCPS ደንቦች እና ሌሎች መመሪያዎች (እዚህ የ MCPS ደንቦች ተብለው ይጠራሉ) አጠቃላይ እይታ ይሰጣል። እነዚህ አጭር ማጠቃለያዎች በመሆናቸው፣ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ወይም ቤተሰቦች በእያንዳንዱ ክፍል መጨረሻ ላይ የተጠቀሱትን የተወሰኑ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች እና ደንቦችን ማንበብ ወይም ለበለጠ መረጃ ከአካባቢያቸው የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ጋር መነጋገር አለባቸው። የቦርድ ፖሊሲዎች እና የ MCPS ደንቦች እዚህ ይገኛሉ፡-www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy. አንዳንድ የሚመለከታቸው የ MCPS ደንቦች ዝርዝር በዚህ የመመሪያ መጽሔት ከገጽ 14 ጀምሮ ይገኛል።  የ MCPS ደንብ JFA-RA፣  የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች  ፣ በጠቅላላው ይተገበራል።  ሌሎች ማጣቀሻዎች ከእያንዳንዱ ክፍል በታች ተጠቅሰዋል። በነዚህ ህትመቶች መካከል ህጎች እና የ MCPS ደንቦች ሊለያዩ እንደሚችሉ ልብ ይበሉ፣ ስለሆነም እነዚያ ህጎች እና መመሪያዎች በዚህ ህትመት ውስጥ ያሉትን መግለጫዎች እና ማጣቀሻዎች ይተካሉ።

ይህ መጽሔት ተማሪዎች ስለመብቶቻቸው፣ ስለ ግዴታዎቻቸውና ሃላፊነቶቻቸው በ MCPS እርካታ የሚያገኙበት መመሪያ ነው። ይህ መጽሔት ተማሪዎችን የሚመለከቱ የስቴት እና የፌደራል ህጎች፣ የቦርድ ፖሊሲዎች እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች እና ሌሎች መመሪያዎች ማጠቃለያ ነው። በማንኛውም የተለየ ሁኔታ ይህ የተማሪ መብቶች ፍጹም የሆነ መግለጫ/ትንታኔ አይደለም። ለተጨማሪ መረጃ፡- እባክዎ በእያንዳንዱ ንኡስ ክፍል መጨረሻ ላይ  እና ከ ገጽ 14-16 የተጠቀሱትን ልዩ/ግልጽ ድንጋጌዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ እና ደንቦችን ያንብቡ። የቦርድ ፖሊሲዎች እና የ MCPS ደንቦች እዚህ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy ይገኛሉ።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ሕጎች የሚለወጡና በዚህ ሕትመት ውስጥ በተካተቱት መግለጫዎችና ማጣቀሻዎች ላይ የበላይነት አላቸው። አንዳንድ የሚመለከቷቸው የሞንትጎመሪ ፐብሊክ ክሱልስ (MCPS) ደንቦች ዝርዝር በዚህ መመሪያ ገጽ 14 ላይ ይጀምራል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation JFA-RA፣ የተማሪ መብቶች እና ግዴታዎች/ሃላፊነቶች፣ በሁሉም ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። ሌሎች ተጨማሪ ማጣቀሻዎች ከእያንዳንዱ ክፍል ግርጌ ላይ ተጠቅሰዋል።

## ■ ነፃ የህዝብ ትምህርት

እድሜአቸው ሴፕቴምበር 1 ላይ 5 ዓመት የሞላቸው፣ እና በት/ቤት መጀመርያ ቀን 21 አመት እድሜ ያልደረሱ፣ የሞንጎሞሪ ካውንቲ ነዋሪዎች በካውንቲው ፐብሊክ ስኩልስ ያለክፍያ በነፃ የመማር መብት አላቸዉ። ይህ መብት እስከ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማጠናቀቅ ድረስ፣ ወይም ተማሪው/ዋ 21 አመት በሚሆንበት/በምትሆንበት የትምህርት አመት መጨረሻ ድረስ፣ የትኛውም ቀዳሚ ቢሆን የሚሰጥ እድል ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ተማሪ ዕድሜው(ዋ) 21 ዓመት በሆነበት የትም ህርት ዓመት መጨረሻ ከተወለደ(ች)በት ጊዜ ጀምሮ ነፃ ተገቢ ህዝባዊ ትምህርት የማግኘት መብት አለው።

## ■ የተማሪ ተሳትፎ

ተማሪዎች ስለ እያንዳንዱ ኮርስ አጠቃላይ ዓላማዎች እና አፈፃፀማቸው የሚገመገምበትን መሠረት ይገለጽላቸዋል። ተማሪዎች በትምህርት ክፍል እንቅስቃሴዎች የመሳተፍና ለትምህርት ክፍል ደንቦች፣ ግዴታዎች፣ እና የአፈፃጸም ሂደቶች የመገዛት ሃላፊነት አለባቸው።

ተማሪዎች ከፋከሊቲው ጋር በመመካከር፥ በትምህርት ቀን ከመደበኛ ፕሮግራም  በተጨማሪ እና/ወይም ከት/ቤት ቀን ውጭ ፍላጎት በሚኖራቸው ፕሮግራሞች፣ የበጎ ፈቃድ ፕሮግራሞች፣ በተመረጡ ርእሶች ላይ ሴሚናሮችን፣ ስብሰባዎችን፣ ወይም አጫጭር የትምህርት ኮርሶች እንዲሰጡ ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ።

ተማሪዎች ፕሮግራሞችን ለመንደፍ/ለመቅረጽ ከርእሰ መምህራን እና ከአስተዳደር አባላት ጋር ተባብረው ይሰራሉ። ፕሮግራሞች ከድስትሪክቱ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ እና ከ MCPS መሠረታዊ የትምህርት ተልዕኮ ጋር የሚስማሙ፣ ከሚመለከታቸው ዕድሜ እና ብስለት ጋር ተስማሚ መሆን አለባቸው፣ እና አወዛጋቢ በሆኑ ርዕሶች አቀራረብ ላይ ሚዛናዊነትን በመፍጠር የተዋቀሩ መሆን አለባቸው።

ተማሪዎችን የሚመለከት ዋና ዋና የቦርድ ፖሊሲ ክለሳ ወይም ቀረጻ በሚደረግ ጊዜ የተማሪ ተወካዮች እንዲሳተፉ ይደረጋል። እንደዚህ ዓይነቱ ተሳትፎ ሊከናወን የሚችለው በስብሰባዎች ላይ የተማሪ ተወካ ዮችን በማሳተፍ፣ ወይም ክለሳው በማናቸውም ደረጃ ላይ እያለ ተማሪ አስተያየት እንዲሰጥበት በመጠየቅ ይሆናል።  ተማሪዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና የአካባቢ ት/ ቤት መመሪያ ወይም ደንቦች ክለሳ ወይም በዝግጅት ሂደት ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ የመሳተፍ መብት አላቸው። ተማሪዎችን የሚመለከቱ አበይት የአካባቢ ት/ቤት መመርያዎች ወይም ደንቦች ከመጻበር ወይም ከመከለሳቸው በፊት የተማሪ አስተያየት እንዲ ሰጥባቸው ለተማሪዎች አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ ቅጅዎች ከበቂ (አስተ ያየት መስጫ) ጊዜ ጋር ይቀመጣሉ/ይለጠፋሉ።

የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪው(ዋ) በስቴት መስፈርት ተፈላጊ በሆነው አጠቃላይ የጤና ሥርዓተ ትምህርት "ስለ ቤተሰብ ሕይወት በሚሰጥ የክፍል ትምህርት ላይ እንዳይሳተፍ-እንዳትሳተፍ ከጠየቀ ለተማሪ ው(ዋ) ተለዋጭ ትምህርት ይሰጣል። የ "MCPS Regulation IGP-RA" አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማሪያ ፕሮግራምን ይመልከቱ።

## ■ የግል ህይወት/ግላዊ መብት

**የተማሪ የግል ህይወት/ግላዊ ጉዳይ በት/ቤት የሥራ ባልደረቦች ይከበራል።**

ዝግጅቱ የተማሪ ብትህውነት ላይ የሚያጠላ መሆኑን ከተገነዘቡ ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቁ ተማሪ የተማሪን የትምህርት ውጤቶችን በመጥቀስ፣ ኃይማኖት፣ ጾታ፣ እሴቶች፣ ወይም አካላዊ ሁኔታዎችን የሚነካ መሆኑን ካመኑበት ተማሪዎች ወይም ወላጆች/ሞግዚቶች መምህሩ(ሯ) ሌላ አማራጭ እንዲሰጣቸው የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል።

ተማሪዎች የቤተሰብን የግል ክስተቶች ወይም የግል ልማዶች/አመሎች፣ ግንኙነቶች፣ ምርጫዎች፣ ባሕሪያት፣ ውሳኔዎች፣ ወይም ችግሮችን ሳይገልጡ፣ ወይም ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰቦቻቸውን ከሌሎች ጋር ሳያወዳድሩ ትምህርታዊ ዓላማዎች ላይ ብቻ በማተኮር በክፍል ውስጥ ውይይት ማድረግ፣ ሥራዎችን /ተግባራትን መስራት፣ ወይም በሌላ መንገድ የማከናወን መብት አላቸው።

በአጠቃላይ የትኛውም የ MCPS የደህንነት ካሜራዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ሪኮርድ ሲደረግ ወይም ፎቶግራፍ በሚነሳበት ጊዜ ማንም ተማሪ፣ ሠራተኛ ወይም ጎብኚ የተለየ መብት ወይም ግላዊ ልዩነት አይኖረውም፥ መተላለፊያ ኮሪደሮች ላይ፣ በካፌቴሪያዎች፣ ጂምናዚየሞች፣ አዳራሾች፣ እና ከቤት ውጭ በሚሰጡ የትምህርት ቦታዎች ላይ፣ እንዲሁም የ MCPS ትምህርት ቤት አውቶቡሶች ውስጣዊ እና ውጫዊ አካል ጨምሮ በ MCPS ንብረት ላይ የሚፈጸሙ የሥነ ምግባር ጉድለቶችን እና/ወይም የወንጀል ድርጊቶችን የ MCPS የደህንነት ካሜራዎች የቪዲዮ ቀረጻ ሊያመለክት ይችላል።። የመማሪያ ክፍሎች እንደ ህዝባዊ ቦታዎች አይቆጠሩም፣ እናም MCPS በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የቪዲዮ ክትትል አያደርግም።

ማንኛውም ተማሪ ወይም ሰራተኛ በእንደዚህ ዓይነት የድምፅ ወይም የቪዲዮ ክትትል በኩል በተሰበሰበ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ በዲስፕሊን ሊቀጣ ይችላል። በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ አባላትም እንደዚሁ ከትምህርት ሠዓት በፊት፣ በትምህርት ሠዓት ላይ ወይም ከዚያ በኋላ በቪዲዮ ካሜራ ክትትል ይደረጋሉ፣ ይህም ለሕግ አስከባሪዎች ሊተላለፍ የሚችል ነው።

ማጣቀሻዎች:-
የ MCPS ደንብ EGF-RB
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ "MCPS Regulation JOA-RA"

## ■ myMCPS Classroom

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች  በ myMCPS Classroom ላይ ውጤታቸውን፣ የቤት ሥራዎችን፣ የክፍል ማስታወቂያዎችን፣ የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰዓቶችን፣ እና የትምህርት ክትትል ምዝገባዎችን ማግኘትና፣ እንዲሁም ከመምህራኖቻቸው ጋር ግንኙነቶችን ማድረግ ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች በ MyMCPS Parent Portal ላይ ተመሳሳይ መረጃ ማግኘት ይችላሉ፥ እና በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች የተማሪን የድንገተኛ ሁኔታ ወቅታዊ መረጃ ማሳወቅ እና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ የምዝገባ ቅጾችን መሙላት ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ myMCPS Classroom ድረ ገጽ በwww.montgomeryschoolsmd.org/mymcps-classroom/index.aspx ይመልከቱ።

## ■ ክትትል (ተማሪው(ዋ) በክፍል ውስጥ መገኘቱ(ቷ)ን መቆጣጠሪያ)

ለተማሪ ስኬት በትምህርት ገበታ ላይ በየእለቱ መገኘት አስፈላጊ ሲሆን እንዲሁም አንድን የትምህርት ቁሳቁስ በደንብ ማወቅን ለማሳየትና የኮርሶች ክሬዲትም ለማግኘት ይጠቅማል/ያስፈልጋል። ተማሪዎች ት/ቤት እንዲከታተሉ እና ወደ ት/ቤትና የመማርያ ክፍሎች በወቅቱ እንዲደርሱ ይጠበቅባቸዋል።

ተፈቅዶላቸው ካልሆነ በስተቀር፣ ተማሪዎች በትምህርት ቀን በመማርያ ክፍሎችና በሌሎች ተፈላጊ እንቅስቃሴዎች ላይ መገኘት አለባቸው። የትምህርት ክትትል ለወላጆች/ሞግዚቶች በተማሪ ሪፖርት ካርድ እና myMCPS Classroom ላይ ሪፖርት ይደረጋል። ተማሪው(ዋ) ሙሉ ቀን በትምህርት ገበታ ላይ ተገኝቷል/ታለች ተብሎ የሚታሰበው በትምህርት ቀን ውስጥ አራት ሰአት ወይም ከዚያ በላይ ከተገኘ(ች) ብቻ ነው። ተማሪው/ዋ ግማሽ ቀን በትምህርት ገበታ ተገኝቷል/ታለች ተብሎ የሚታሰበው በትምህርት ቀን ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሰአት፣ ነገር ግን  ከአራት ሰአት በታች ከተከታተለ/ች ነው።

በአካባቢ ት/ቤት አሰራር መሰረት፣ አንድ ተማሪ ከት/ቤት ከቀረ(ች) ት/ቤቱ የመቅረቱ(ቷ)ን ምክንያት ይከታተላል።

### ምክንያት/ፈቃድ ያላቸው መቅረቶች

በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ተማሪዎች ከት/ቤት መቅረት ይችላሉ፡-

- በትምህርት ቤት፣ MCPS ወይም MSDE የጸደቀ ወይም የተደገፈ ሥራ
- የቅርብ ዘመድ ከሞተ
- የተማሪ ሕመምና የደኅንነት ስጋቶች (በሽታው ሥር ከሰደደ ወይም በተራዘመ መቅረት ምክንያት ርእሰ መምህሩ(ሯ) የሐኪም የምስክር ወረቀት እንዲያቀርቡ ወላጅን/አሳዳጊን መጠየቅ ይችላል።)
- ከእርግዝና እና ከወላጅነት ጋር በተያያዙ ሁኔታዎች (በህመም ወይም በተማሪዋ(ው) ልጅ የህክምና ቀጠሮ ምክንያት መቅረት እና ከቤተሰብ ጋር በተገናኘ ህጋዊ ቀጠሮ ምክንያት መቅረትን ጨምሮ ጉዲፈቻ፣ አሳዳጊ እና ጉብኝትን ያካትታል)። እነዚህ እናት እና አባት ለሆኑ ተማሪዎች የተሰጡ መብቶች ናቸው።
- የፍርድ ቤት መጥሪያ
- አደገኛ የአየር ሁኔታ (ተማሪው/ዋ ከቤት ወደ ት/ቤት ለመመላለስ የአየር ሁኔታ የሚያሰጋ ከሆነ)
- የዶክተር/የህክምና ቀጠሮዎች
- ኃይማኖታዊ በዓል ለማክበር
- የስቴት አስቸኳይ ሁኔታ
- መታገድ
- የተፈቀደ የመጓጓዣ እጦት (ለምሳሌ፥ የትምህርት ቤቱ አውቶቡስ ካልመጣ)
- የርእሰ መምህር ፈቃድ

እነዚህ ከተዘረዘሩት በአንዱ ምክንያት ተማሪዎች ከት/ቤት ከቀሩ፣ ወደ ት/ቤት ሲመለሱ በሶስት ቀን ውስጥ ከወላጅ/ከአሳዳጊ ማስታወሻ ማምጣት አለባቸው። ለምሳሌ፣ አንድ ተማሪ ረቡዕና ሃሙስ ከት/ቤት ቢቀር/ብትቀር እና ዓርብ ቢመለስ/ብትመለስ፣ ስለመቅረቱ/ቷ ምክንያት የሚያብራራ ማስታወሻ በሚቀጥለው ማክሰኞ  ማቅረብ አለበ(ባ)ት። አለዚያ መቅረቱ ያልተፈቀደ ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ት/ቤት "በት/ቤት እንከን የሌለበት መገኘት" ሽልማት ማዘጋጀት ቢፈልግ፣ ተማሪዎቹ የቀሩባቸው ቀናት በሀይማኖት ምክንያት የተፈቀዱ ቀናት ብቻ ከሆኑ ሽልማቱን ማስቀረት አይችልም።

ተማሪዎች 18 ዓመት እድሜ ወይም ከዚያ በላይ ወይም ያገቡ ከሆኑ፣ የMCPS ቅጽ 281-12Eligible Student Declaration Form (የተማሪ ብቁነት ማረጋገጫ ቅጽ) ከሞሉ በኋላ የራሳቸውን ማስታወሻ መፃፍ ይችላሉ። እድሜው(ዋ) የሚፈቅድ ያለ ምክንያት/ያለፈቃድ የሚቀር (የምትቀር) ተማሪ ከወላጅ/አሳዳጊ ጋር በጥገኝነት የሚ(ምት)ኖር ከሆነ ለተማሪው/ዋ ሳይገለጽ ያለፈቃድ ከት/ቤት ስለመቅረቱ(ቷ) ለወላጅ/አሳዳጊ ተጨማሪ ማሳወቂያ ሊላክ ይችላል።

ወላጅ/ሞግዚት፣ (ብቁ ተማሪ) ቢያንስ ከአምስት የትምህርት ቀናት አስቀድሞ ፈቃድ ጠይቀው ከሆነ ርእሰ መምህር ለሥራ ወይም ሌላ እንቅስቃሴ ለተማሪዎች መፍቀድ ይችላል/ትችላለች። ተማሪዎች ከሚከተሉት አንዳቸውን ለማከናወን ከት/ቤት ቢቀሩ ርእሰ መምህሩ/ሯ ይቅርታ ያደርግላቸዋል/ታደርግላቸዋለች፡-

- የኮሌጅ ግቢ ለመጎብኘት
- በኮሌጅ የመተዋወቅያ ፕሮግራም ለመሳተፍ
- ስራ ለመቀጠር ቃለ መጠይቅ ለማድረግ
- የጋራ ትምህርት ፕሮግራም አካል የሆነ ስራ ለመስራት
- የአጭር ጊዜ ወይም የሙሉ ጊዜ ስራ ለመሳተፍ

የቤተሰብ እረፍቶች በአብዛኛው አይፈቀዱም። ከተለመደው ውጭ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ ግን፣ ርእሰ መምህሩ/ሯ መቅረቱን ይቅርታ ማድረግ ይችላል/ትችላለች።

እያንዳንዱ ት/ቤት በየቀኑ በት/ቤት መገኘትን፣ በት/ቤት የተገኙበትን ቀናቶች ለመቆጣጠር፣ እና (ጣልቃ-ገብ) ርምጃዎችን ለማቅረብ/ለመውሰድ አካሄድ/አሠራር ይዘረጋል።

### ፈቃድ የሌላቸው ቀሪዎች

እላይ በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት ያልተፈቀደ ቀሪ "ያልተፈቀደ ቀሪ" ነው። አንድ/ዷት ተማሪ አንድ የትምህርት ቀን ከቀረ/ከቀረች እና ፈቃድ/ይቅርታ ከሌለው/ከሌላት፣ ተማሪው/ዋ ባመለጠው/ባመለጣት በያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ያለፈቃድ መቅረት ይመዘገብበታል/ይመዘገብባታል።

ያለፈቃድ በተቀረበት ቀን ርእሰመምህሩ/ሯ ተማሪው/ዋ ከትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ መከልከል ይችላል/ትችላለች።

አምስት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት ያለፈቃድ የቀሩ ተማሪዎች ት/ቤት ቀሪ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል። የአንደኛ ደረጃ እና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በሰበብም ሆነ ይቅርታ ሳይደረግላቸው፣ ከመጠን ያለፈ መቅረት እና/ወይም ዘግይተው፣ መምጣት ካበዙ ለተገቢው ጣልቃገብነት እንዲተላለፉ ይደረጋል። በርእሰመምህሩ(ሯ) ወይም በእርሱ(ሷ) ተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘትን ለመጨመር የተቀረጹ ከበድ ያለ የጣልቃ-ገብ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደ ሚገኙ ሌሎች ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ።

የትምህርት ቤት ካውንስለር ከተማሪ እና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር በመምከር ለመቅረት ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ እንደ ትምህርት ቤቱ ልምድ እና የ MCPS Regulation JEA-RA መሠረት ተገቢ ጣልቃ ገብነትን መወሰን ያስፈልጋል የተማሪ መቅረት/Student Attendance።

### በቀሪነት ወቅት ያመለጡ ስራዎች

የቀሩበት ህጋዊ ይዘት የፈለገም ቢሆን ያመለጣቸውን ስራ ለማስተካከል መጣር ለተማሪዎች እጅጉን አስፈላጊ ነው። ተማሪዎች ከማናቸውም ክፍል ከቀሩ በኋላ ሲመለሱ መምህራን ተመጣጣኝ፣ ነገር ግን የተለየ ስራ ወይም ግምገማ መስጠት ይችላሉ። ላልተፈቀዱ ቀሪዎች፣ በርእሰ መምህርሩ/ሯ እና በአመራር ቡድኑ በፀደቀው አካሄድ/አሠራር መሰረት፣ መምህራን ላመለጡ/ላልተሰሩ ስራዎች ወይም ግምገማዎች ክሬዲት መንሳት ይችላሉ።

ማጣቀሻዎች፡-

MCPS Regulations IKA-RA, IOA-RA, IOE-RA, IQB-RA, JEA-RA, JGA-RB, and JGA-RC.

ሜሪላንድ የተማሪ ሪከርድ አያያዝ መመርያ - Maryland Student Records System Manual

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ መፅሄት (MCPS High School Course Bulletin)

## ■ የክፍል ሥራ

### ውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ ልምምዶች ፍትሃዊ፣ ትርጉም ያላቸው፣ እና ለሁሉም ተማሪዎች ጥብቅ የአፈፃፀም መመዘኛ ደረጃዎችን የሚያሟሉ ይሆናሉ። በከሪኩለሙ ላይ እንደተገለጸው፣ የትምህርት ውጤቶች እንደየክፍል ደረጃ እና በየኮርሶቹ እንደሚጠበቀው ውጤት መጠን በጠቅላላ ዲስትሪክቱ ውስጥ ወጥ የሆነ ትርጉም ይኖራቸዋል። ይህንን የቦርድ ፖሊሲ "Board Policy IKA, Grading and Reporting" ይመልከቱ። ስለ ውጤት አሠጣጥ፣ ስለ ቤት ሥራ፣ ዳግም ማስተማር፣ እና እንደገና የመፈተን አሠራር ሂደቶች በየትምህርት ቤቶቹ በአንድ አይነት ይተገበራሉ። በትምህርት ቤት ደረጃ የሚካሄዱ አሠራሮች በርእሰመምህር አማካይነት፣ ከትምህርት ቤት አመራር ቡድን ጋር በትብብር ይተገበራሉ።

ከ1ኛ እስከ 5ኛ ባሉት ክፍሎች፣ የውጤት አሰራር የሚወሰነው የክፍል ደረጃን የሚመጥን ወይም የኮርስ መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ይሆናል። መምህራን ተማሪዎች እውቀታቸውን፣ ምክንያታዊ አስተሳሰባቸውንና የፈጠራ ችሎታዎቻቸውን፣ እንዲሁም በቃል፣ በጽሁፍ፣ እና በአፈጻጸምና በውጤቶች የአካዴሚያዊ ስኬት ክህሎቶቻቸውን ማሳየት የሚችሉባቸውን በርካታና የተለያዩ እድሎች ለተማሪዎች በማቅረብ ግንዛቤአቸውን ይፈትሻሉ።

በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የውጤት አሠጣጥ የሚያተኩረው የሚጠበቅባቸውን የኮርስ ማከናወን መሠረት በማድረግ ይሆናል።

በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ወቅት፣ በ "MCPS Regulation IKA-RA" መመሪያ መሠረት ለኤለመንተሪ እና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ድጋሚ የመፈተን እድሎች ይሰጣቸዋል Grading and Reporting ። አስተማሪዎች ለአንድ ተግባር ወይም ለግምገማ የሚሰጡት ውጤት/ነጥብ ከ50 በመቶ ያላነሰ መሆን አለበት። ተማሪው/ዋ የተሰጠውን/የተሰጣትን ተግባር ለመፈፀም መሰረታዊ መስፈርቶች እንኳ ለማሟላት ጥረት አላደረገም/ችም ወይም ተማሪውው/ዋ በአካዴሚያዊ ማጭበርበር ተሳትፏል/ፋለች ብሎ/ላ ካመነ/ች አስተማሪው/ዋ ዜሮ መስጠት ይችላል/ትችላለች። የአካዳሚክ እምነተቢስነት ምሳሌዎች በዚህ ብቻ ሣይወሰን፥ ማጭበርበር፣ ማታለል፣ ሌብነት፣ ተንኮል፣ በንግግር፣ በምልክቶች፣ ሆን ብሎ በሌሎች ተማሪዎች ላይ በአካዴሚያዊ ሥራ ያልተፈቀደ ኢ-ፍትሃዊ፣ ሐቀኝነት የጎደለው ወይም የማይገባ ጥቅም ማግኘት፣ መኮረጅ፣ መቅዳት፣ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዘዴ ያጠቃልላል። ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች በግምገማዎች ወይም በሌላ ውጤት/ማርክ የተሰጠበት ስራ ውስጥ የሚገኝ መረጃ እንዳያጋሩ ወይም እንዳያሳራጩ ይጠበቅባቸዋል።

ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሥራዎች-assignments ለማጠናቀቅ እንዲችሉ ተጨማሪ እድል ለመስጠት የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን መጨረስ የሚገባቸውን ጊዜ እና የጊዜ ገደቦችን ይወስናሉ። መምህራን የማስረከቢያ ቀን እና የማስረከቢያ ቀነ ገደብን/ የመጨረሻ ሰአት እንዲለዩ/እንዲነጥሉ ይጠበቅባቸዋል፤ ቢሆንም፣ ማስረከቢያ ቀንና ቀነ ገደብ አንድ ላይ የሚወድቁበት/የሚሆኑበት ወቅት ሊኖር ይችላል። ከማስረከብያ ቀን በኋላና በጊዜ ገደብ (deadline) የቀረበ ስራ ከውጤቱ/ከማርኩ ከአንድ የፊደል ደረጃ ወይም ከ10 በመቶ ባልበለጠ ዝቅ ሊደረግ ይችላል። ከጊዜ ገደብ በኋላ ገቢ የተደረገ ስራ ዜሮ ተብሎ ይመዘገባል።

ድጋሚ ፈተና ስለመስጠት፣ የድጋሚ ፈተና ውጤት የበፊተኛውን ውጤት ይተካል (ከመጀመሪያው ውጤት ከፍ የሚል ከሆነ)።

መምህራን ተጨማሪ ክሬዲት እና/ወይም የጉርሻ ነጥቦችን አይሰጡም።

"MCPS Regulation IKA-RA" Grading and Reporting ፣ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክሬዲት የሚኖራቸው ኮርሶችን ወይም በከፊል አንድን ኮርስ ድጋሚ ለመፈተን ስለሚችሉበት ሁኔታ እና የተማሪ የማጠቃለያ ፈተና ውጤት ወይም የሴሚስተር ውጤት በተማሪው(ዋ) አሠራር ላይ ከሚታየው ይልቅ በክፍል ደረጃ የተማሪው(ዋ) አሠራር የተሻለ መሆኑን ወይም የኮርስ መስፈርቶች ላይ ልዩነት መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲኖር ሊሻሻል ስለሚችልበት ሁኔታ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል።

ለወላጆች/ለሞግዚቶች እና ለተማሪዎች ስለ ውጤት አሠጣጥ እና ሪፖርት አሰጣጥ የሚገልጽ ተጨማሪ መረጃ-ኢንፎርሜሽን በዚህ የ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል www.montgomeryschoolsmd.org/info/grading፣ እና በትምህርት ቤቶች ዋና ጽ/ቤቶች ጭምር ይገኛል።

ማጣቀሻዎች፡-

የቦርድ ፖሊሲ IKA እና የ MCPS ደንብ IKA-RA ይመልከቱ።

### የላቀ ደረጃ (Honors)፣ ከፍተኛ ደረጃ(Advanced-level)፣ እና ለከፍተኛ ደረጃ ምደባ Advanced Placement(AP) ኮርሶች

የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን የላቀ ደረጃ፣ ከፍተኛ-ደረጃ፣ እና / ወይም የ AP ኮርሶችን ለመውሰድና አዳጋች ነገሮችን ለመቀበል/ለመጋፈጥ ችሎታ፣ ተነሳሽነት፣ወይም እምቅ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ሁሉ ኮርሶቹን የመውሰድ እድሉን ማግኘታቸዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ። እያንዳንዱ ት/ቤት የላቀ ማዕረግ፣ ከፍተኛ-ደረጃ፣ እና ወይም ለAP ኮርሶች ምደባ (Honors, advanced-level, and/or AP courses )፣ ፅንተው ፕሮግራሙን እና ከፍተኛ-ደረጃ የኮርስ ስራዎችን ለመከታተል ብቃት እና ትጋት ያላቸው ተማሪዎች በሙሉ እንዲገቡ ኃላፊነት የተሞላበት ክፍት ምዝገባ ማድረግ አለበት። የተማሪ ጥንካሬዎች መግለጫን (profile) በሚከተሉት በርካታ መመዘኛዎች ላይ ጠንካራ ግምገማ በማድረግ ማወቅ/መወሰን ይቻላል፡-

- ኮርሱን ለመውሰድ የቅድሚያ መስፈርቶች የዕውቀት ደረጃ (A፣ B፣ ወይም C ውጤቶች/ማርኮች)
- የወላጅ/ሞግዚት "የብቃት/ችሎታ/" የድጋፍ ሀሳቦች/ምስክርነት
- መደበኛ የፈተና ውጤቶች፣ እንደአግባቡ
- ከበድ ያሉ/ተፈታታኝ ስራዎችን ተቋቁሞ ለመፈፀም ፈቃደኛነት

- የተማሪ ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት
- የመምህር/አማካሪ (የችሎታ/ብቃት) የድጋፍ ሀሳቦች/ምስክርነት
- የስራ ናሙናዎችና የመረጃ ሰነዶች

### በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (ሚድል ስኩል) የተወሰዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶች።

2016–2017 የትምህርት ዘመን 6ኛ ክፍል ለገቡ ተማሪዎች፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርሶች የመጨረሻ ክፍል እና ክሬዲት በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁት በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት በነበሩበት ወቅት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፕት ላይ ሪፖርት ተደርጓል እና የተማሪው(ዋ) ድምር GPA ስሌት ውስጥ ተካትቷል።

2016–2017 የትምህርት ዘመን 6ኛ ክፍል ለገቡ ተማሪዎች በመለ ስተኛ ደረጃ ት/ቤት እያሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኮርሶችን በተሳካ ሁኔታ ያጠናቀቁት የመጨረሻ ክፍል እና ክሬዲት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ትራንስክሪፖት ላይ ሪፖርት ይደረጋል፣ ነገር ግን የተገኘው ውጤት የተማሪውን ድምር GPA ካላሻሻለ በስተቀር ወደ ድምር GPA ስሌት ውስጥ አይገባም። በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እያለ(ች) የተወሰደ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኮርስ የተማሪው(ዋ)ን አማካይ ድምር ጨት GPA የሚያሻሽል ከሆነ በ MCPS በቀጥታ ይተገበራል። ወላጆች/ አሳዳጊዎች በቀጥታ ስሌት ውስጥ እንዳይገባ ከፈለጉ የትምህርት ቤቱን ካውንስለር ማነጋገር ይችላሉ።

*ማጣቀሻዎች፡-*
የቦርድ ፖሊሲ IKA፣ MCPS Regulation IKC-RA
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትምህርት ውጤት እና ሪፖርት ድረ-ገጽ

## ■ የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL)

ለሜሪላንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ የሚሠሩ ተማሪዎች በሙሉ ከምዝገባ፣ ከክሬዲት፣ ከኮርሶች፣ እና ሌሎች የመመረቂያ ብቁነት መስፈርቶች በተጨማሪ የአገልግሎት ትምህርት ሰዓቶችን ማሟላት/ ማጠናቀቅ አለባቸው። የ5ኛ ክፍልን ከጨረሱ በኋላ የአገልግሎት ትምህርት ሰአቶችን ከቀጣዩ ሰመር (summer) ጀምሮ ለማጠራቀም ይችላሉ። በቅያሪ ለሚገቡ ተማሪዎች ከተወሰኑ ልዩነቶች በስተቀር ተማሪዎች ከመመረቃቸው በፊት የ75 የአገልግሎት ትምህርት ሰዓቶችን ማጠናቀቅ አለባቸው። የ MCPS የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ፕሮግራም ዝርዝሮች በዚህ አውታረ መረብ ላይ www.mcps-ssl.orgወይም በማንኛውም የመካከለኛ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ SSL አስተባባሪውን በማነጋገር ሊያገኙ ይችላሉ።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና ወላጆች/ሞግዚቶች የተማሪ የተጠራቀመ የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት SSL ሠዓቶችን በ myMCPS Classroom ላይ መመልከት ይችላሉ።

*ማጣቀሻዎች፡-*
COMAR 13A.03.02.05 የተማሪ አገልግሎት
Director, Student Leadership and Extracurricular Activities: 240-740-4692 ወይም SSL@mcpsmd.org

## ■ የተማሪዎች አመራር

### ተሳትፎ

ተማሪዎች የተማሪ አመራር/አስተዳደር የመመስረት፣ የማካሄድ፣ እና የተሳትፎ መብት አላቸው። ተማሪዎች በተማሪ አስተዳደር ድርጅት አማካ ኝነት በት/ቤት ጉዳዮች ድምፃቸውን የማሰማት መብት አላቸው። ተማሪዎች ተጠያቂነቱ ለተማሪዎች የሆነ ውጤታማ የተማሪ አስተዳደር ድርጅት ለመፍጠር የመስራት ሃላፊነት አለባቸው። በትምህርት ቤት ውስጥ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበ(ች) ማንኛውም ተማሪ፣ እና በትምህርት ቤቱ ሕግ የተቀ መጠውን ማንኛውንም መስፈርት ማሟላት የቻለ(ች) ተማሪ በተማሪ አመራ ርነት ተወዳድሮ(ራ) ቦታውን መያዝ ይችላል/ትችላለች። በተማሪዎች አስተ ዳደር መሳተፍ የአገልግሎት ትምህርት ሰአቶችን ማግኘት ያስችላል።

### የመምህራን/የፋኩሊቲ ድጋፍ

የት/ቤት ሠራተኞች አባላት የተማሪን በተማሪ አስተዳደር የመሳተፍ መብት ይደግፋሉ። የተማሪዎች አስተዳደር ተማሪዎች በት/ቤቱ ስራ/እንቅስቃሴ ላይ ሀሳባቸውን ማቅረብ እንዲችሉ ማስቻሉን ርእሰ መምህሩ/ሯ ያረጋ ግጣል/ታረጋግጣለች።

በፀደይ/ስፕሪንግ ወራት፣ የተማሪ አስተዳደር ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለሚመጣው አመት የአማካሪ መሾምን በሚመለከት ከርእሰ መምህሩ/ሯ ጋር ይመክራል፣ እናም አማካሪው/ዋ ከመሾሙ/ሟ በፊት የተማሪዎቹ አስተያየት በጥንቃቄ ይታያል።

የት/ቤት ሥራ ባልደረቦች የተማሪ አስተዳደር/አመራር የሚያስፈልገውን መገልገያ ግብአቶች እና መጠቀሚያ ክፍሎችን በመስጠት ይረዳሉ።

በት/ቤት አስተዳደር የተፈቀደ የተማሪ አመራር/አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ የትምህርት ክፍል ጊዜ የተጓደለባቸው ተማሪዎች በምክንያት የቀሩ ተደርጎ ይቆጠራል እና ያመለጣቸውን የትምህርት ሥራዎች የማካካስ ኃላፊነት አለባቸው።

### የተማሪዎች አስተዳደር ስልጣኖች

እንደአስፈላጊነቱ ከት/ቤት ሰራተኞች/አማካሪ ጋር በመማከር ተማሪዎች ለተማሪ አስተዳደሩ መተዳደርያ ደንብ ወይም በስራ ላይ ላለው መተዳደርያ ደንብ ማሻሻያዎች በፅሁፍ የማዘጋጀት ሃላፊነት አለባቸው። ሁሉም የመተ ዳደርያ ደንቦች የርእሰ መምህሩ(ሯ)ን ውሳኔ የመስጠት ስልጣን እውቅና የሚሰጥ አንቀፅ ማካተት አለባቸው። የ MCPS ደንቦችን ካልጣሰ ወይም በት/ቤት አሠራር ላይ ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት ከሌለው በስተቀር ተማሪዎች የተማሪ አመራር ደንብ እንዲጸድቅ ወይም ማሻሻያዎች እንዲደረጉ ርእሰመ ምህርን የመጠበቅ መብት አላቸው። ያልፀደቀበት ምክንያቶች ለተማሪዎች በፅሁፍ ይገለፅላቸዋል የአስተዳደሩን ቅሬታዎች አስመልክተው የመተዳደርያ ደንቡን ለመከለስ እድል መሰጠትም አለባቸው።

ተማሪዎች፣ በተማሪዎች አስተዳደር አማካይነት፣ በተማሪ አስተዳደር ለሚቀርቡ ማሳሳቢያዎች በአምስት የትምህርት ቀኖች ውስጥ ከት/ቤቱ አስተዳደር መልስ የማግኘት መብት አላቸው። ማሳሰብያዎች ተቀባ ይነት ካላገኙ ወይም ከተሻሻሉ አስተዳደሩ፣ በጽሁፍም ሆነ በቃል፣ ምክን ያቶችን ያቀርባል/ይሰጣል። ማሳሰቢያዎቹ ሰፊ ወይም ውስብስብ ከሆኑ፣ የት/ቤቱ አስተዳደር፣ ከተማሪዎች አስተዳደር ተወካዮች ጋር በመመካከር፣ የቃል ወይም የፅሁፍ መልስ የሚሰጥበትን ተቀባይነት ያለው የጊዜ ገደብ ይወስናል።

የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ፣ የተማሪዎች አስተዳደር አማካሪ፣ እና ርእሰ መምህሩ/ሯ በየወቅቱ እየተገናኙ ስለ ተማሪዎች አስተዳደር ድርጅት ግስጋሴና ቅሬታዎች ይመካከራሉ።

*መጣቀሻዎች፡-*
የቦርድ ፖሊሲ IQD
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulations IQD-RA እና IQD-RB
የ MCPS የተማሪ አመራር፡- 240-314-1039
(http://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership/ )

## ■ የመጠየቅና ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት

### ንግግር

በስቴት ወይም ካውንቲ የስርአተ-ትምህርት ሰነዶች የተቀመጡትን ገደቦች ባልጣሰ ሁኔታ ተማሪዎች አማራጭ ሀሳቦችን እንዲገመግሙ እና የራሳ ቸውን አስተያየት መያዝ እንዲችሉ ግላዊ አስተያየታቸውን መግለጽ፤ እና የመደምደሚያ ሀሳብ ላይ ከመድረሳቸው በፊት መረጃ መተንተን እና መገምገም እንዲችሉ፤ በአከራካሪ/አነጋጋሪ ርእሶች ላይ የተለያዩ ሀሳቦች የማግኘት መብት አላቸው፤። ተማሪዎች በኮርሶቻቸው ውስጥ የቀረቡትን ርዕሶች በቁም ነገር የማገናዘብ እና በውይይት በተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የተገለጹትን የተለያዩ አመለካከቶች ለማሻሻል ሀሳባቸውን ለመጨመር በክፍል ውይይቶች ውስጥ የመሳተፍ ሃላፊነት አለባቸው፤ እርስ በእርስ የመከባበር ድባብን ለመጠበቅ የተለያዩ አስተያየቶችን ማክበር፣ እና ምቹ የመማር እና የሥራ አካባቢን የሚጎዳ፣ ከዓላማው ጋር የማይጣጣም ጸያፍ፣ ነውረኛ፣ ሐሜተኛ፣ ጸያፍ ንግግርን፣ ማስፈራራት ወይም የማስፈራራት ዓላማ ካለው የቃላት አጠቃቀም መታቀብ አለባቸው። በተጨማሪም፥ ቦርዱ ቋንቋን እና/ወይም ጥላቻን የሚያራምዱ እና በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክቱ ሥራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ጫና/መሰናክል ሊያስከትሉ የሚችሉ ምስሎችን እና ምልክቶችን ማሳየትን ይከለክላል።

ሆኖም የእንደዚህ ዓይነቶቹ የቃላትና የቋንቋዎች ክልከላ ኃላፊነት ለተሞላበት ውይይት፣ ምስሎች ወይም ምልክቶችን ለትምህርት ዓላማዎች እንዳይውል ለመከላከል ጥቅም ላይ አይውልም።

## አለባበስ እና አጋጌጥ

በማህበረሰቡ የአለባበስ መመዘኛዎችና በአካባቢ ት/ቤት የዲሲፕሊን መመርያ በሚፈቅደው መሠረት፣ ተማሪዎች ለት/ቤት በአግባቡ የመልበስና መጋጌጥ ራሳቸውን የመንከባከብ ሃላፊነት አለባቸው። በሚከተሉት ምክንያቶች ካልሆነ በስተቀር ተማሪዎች በአለባበስና ራስን በመንከባከብ ፈሊጥ ላይቀጡ ይችላሉ፡-

- በት/ቤት እንቅስቃሴዎች ስራ የማደናቀፍ  አዝማምያ ካለው፤
- በትምህርት አካባቢ ውካታ/የሚያቃውስ ሁኔታ የሚቀሰቅስ ከሆነ፤
- የራስን ወይም የሌሎችን ጤንነት እና/ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል፤
- ያንድ ኮርስ ወይም እንቅስቃሴ ተቀባይነት ያለው መስፈርት የማያሟላ ከሆነ፤
- ከውንብድና ጋር ግንኙነት ካለው፤
- ብልግና/አስነዋሪ፣ ፀያፍ፣ ያልታረመ፣ ስድ፣ ራቁትነት፣ ወይም ፆታዊ የግብረ ስጋ ባህርይን የሚያጋልጥ፤ ወይም
- የትምባሆ አጠቃቀምን ያበረታታል (ይህ ህገወጥ የእጾች እና/ወይም የትምባሆ አጠቃቀም፡- Juuls, Vapes, e-cigarettes, and edibles የመሣሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላል)፣ አልኮል፣ አደንዛዥ እጾች ወይም ወሲባዊ ድርጊቶችንም ያካትታል።

አለባበሳቸው ከነዚህ መመርያዎች ጋር የሚስማማ እስከሆነ ድረስ፣ ተማሪዎች ከሀይማኖታቸው ጋር የተያያዙ ወይም የሀይማኖት መልእክት የያዙ ያንገት ሻሾች፣ ሂጃቦች፣ ያርሙልክስ፣ ፓትካስ፣ ወይም ሌላ ልብስ ወይም ጌጣጌጥ መልበስ እንዲፈቀድላቸው ይገባል።

በሚቻል ወቅት፣ በአካል ማጠንከርያ ትምህርት ወቅት ወይም በት/ቤት ስፖንሰር በሚሆኑ እንቅስቃሴዎች የተወሰኑ ልብሶችን፣ ከሃይማኖት እምነታቸው አንፃር አስነዋሪ ሆኖ ከታያቸው፣ ለመልበስ ወይም ላለመልበስ ተማሪዎች (ወይም ለወላጅ/አሳዳጊ በነሱ ፈንታ) ፈቃድ ከጠየቁ ት/ቤቶች ተገቢ መስተንገዶ መስጠት አለባቸው ።

*ማጣቀሻዎች፡-*
*የ MCPSየተማሪ ስነምግባር መመሪያ-Student Code of Conduct*
*በMontgomery County Public Schools የሀይማኖት አይነት ብዛት ማስከበርያ መመርያዎች*

## ስብሰባ

ተማሪዎች ለነሱ አሳሳቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውይይቶች ለማካሄድና በሰላማዊ መንገድ ለመሰለፍ የመሰብሰብ መብት አላቸው። ተማሪዎች ያቀዱት ተግባር/እንቅስቃሴ በት/ቤት ቀን ይፈቀድ እንደሆነ እና እንዳልሆነ፣ የሚካሄድበትን ሰአት እና ቦታ፣  እንዲሁም የሚያስፈልገውን የቁጥጥር አይነት በተመለከተ ከት/ቤት አስተደደር ጋር የመማከር ኃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች በተጨማሪ ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር ተባብሮ የመስራት፣ እንቅስቃሴው ስርአት የያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ እርምጃዎች የመውሰድ፣ እና የተሳተ ስራን የማካካስ ሀላፊነት አለባቸው።

በማናቸውም የትምህርት ቀን ከካምፓስ ጥሎ መውጣት የትምህርት ሥራ ሂደትን የሚያደናቅፍና በሚኖረዉ ተፅዕኖ ያለፈቃድ እንደመቅረት ይቆጠራል።

## አቤቱታዎች

ተማሪዎች ከት/ቤት አስተዳዳሪዎች የመገናኘትና አለመግባባቶችን ማጣራትና ለአቤቱታ መነሻ በሆኑ ርእሶች የመረጃ መለዋወጫ መድረክ የማዘጋጀት ሃላፊነት አለባቸው። የት/ቤት ሥራዎችን እስካላደናቀፉ ድረስ፣ ተማሪዎች አቤቱታዎችን ከትምህርት ክፍለጊዜ ውጭ የማሰራጨት መብት አላቸው። ተማሪዎች የሚያቀርቧቸው አቤቱታዎች የተማሪዎችን እና ሌሎች በት/ቤት ማህረሰብ የሚገኙ ሰዎችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ድርጊቶችን የማያበረታቱ መሆናቸውን እንዲሁም ስም የሚያጠፉ/የሚያጎድፍ ወይም ባለጌ/ጸያፍ አለመሆናቸውን ወይም በሌላ ሁኔታ በት/ቤቱ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ ማስተጓጎል የማያስከተሉ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።  ይህን ሃላፊነት ለማሟላት ካልቻሉ የት/ቤቱ አስተዳደር የአቤቱታዎችን መሰራጨት ለማቆም/ማስቆም ይችላል። በት/ቤት ደረጃ፣ ተማሪዎች በአምስት የትምህርት ቀኖች ውስጥ መልስ የማግኘት መብት አላቸው።

## ሕትመቶች፣ (የመድረክ) ዝግጅቶች፣ እና መረጃዊ መገልገያዎች

ሕትመቶች፣ ትርኢቶች/ዝግጅቶችን፣ እና የመረጃ ቁሳቁሶችን በተመለከተ ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው።

- ተማሪዎች በት/ቤት የተደገፉ ሕትመቶችን (ለምሳሌ፡- ጋዜጣዎች፣ ዓመታዊ መጽሔት፣ የሥነጽሑፍ መጽሔቶች) እና በት/ቤት የተደገፉ እንቅስቃሴዎችን (ለምሳሌ፡- የት/ቤት ጭውውቶች፣ እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች) ለማዘጋጀት መብት አላቸው።
- ከዚህ በታች ባሉት መመሪያዎች እና በት / ቤቱ ስፖንሰር መመሪያ እና መመሪያ መሠረት በትምህርት ቤት በሚደገፉ ህትመቶች እና ትርኢቶች ይዘት ላይ ተማሪዎች የመወሰን መብት አላቸው።
- ተማሪዎች ት/ቤት ስፖንሰር ያላደረጋቸውን ህትመቶች የማሰራጨት መብት አላቸው፣ ህትመቶቹ የስፖንሰር አድራጊውን ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም እስከያዙ/እስካሳዩ ድረስ ወይም የሚሸጡ ወይም በሌላ ሁኔታ የሚሰራጩ ህትመቶች ከሆኑ ደግሞ በMCPS ውስጥ በሚ(ምት)ማር ተማሪ እስከሆኑ ድረስ።
- ተማሪዎች በትምህርት ቤት ስፖንሰር ያልተደረጉ ቁሳቁሶችን፣ የተማሪ ህትመቶች ስርጭትን በሚቆጣጠሩት ተመሳሳይ ገደቦች እና ሂደቶች መሠረት በመደበኛነት ለመለጠፍ በሚጠቀሙባቸው የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ ግድግዳዎች ወይም ሌሎች ለመለጠፍ በሚጠቀሙባቸው ቦታዎች ላይ የማሳየት መብት አላቸው።
- ተማሪዎች በአካባቢ ት/ቤት በተዘረጋው አካሄድ ወይም "MCPS ደንብ JFA-RA" Student Rights and Responsibilities - ስለ ተማሪ መብት እና ግዴታዎች/ሃላፊነቶች በተገለጸው መሠረት የት/ቤትን ድጋፍ ሰጭ አካል/ስፖንሰርስ ውሳኔ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አላቸው ።

ርእሰመምህሩ(ሯ) በሚከተለው መስፈርት ብቻ የተማሪን የሥራ ውጤት ወይም የስነ ጽሑፍ ህትመት ወይም ሌላ የመረጃ ቁሳቁስ ስርጭት በቅድሚያ መገደብ፣ ማቆም ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል-ትችላለች።

- ጸያፍ፣ የሚያጥላላ፣ የብልግና፣ የሚያነሳሳ፣ ስም የሚያጠፋ፣ አስነዋሪ፣ ወይም የትንኮሳ፣ የማስፈራራት፣ የማሸማቀቅ ቋንቋዎችን ያዘለ ከሆነ፤
- መተማመኛ/ማረጋገጫ የሌለው ግላዊነትን የሚዳፈር ከሆነ፤
- ተማሪዎችን ግልጽና ሊፈጸም የሚችል አደጋ እንዲጠነስሱ የሚያነሳሳ ከሆነ፣ (a) ሕገ-ወጥ ድርጊት መፈጸም፣ የቦርድ ፖሊሲ እና/ወይም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህጎች ጥሰት፣ ወይም (b) የት/ቤትን ሥርዓትና የሥራ ሂደት ማቴሪያላዊ/አይነተኛ በሆነ መልኩ የሚያደናቅፍ/የሚያስተጓጉል ከሆነ። "ከባድ ማስተጓጎል" ማለት፣ በት/ቤት ስራ ጣልቃ መግባት፣ ወይም በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ሥርዓት በሌለው ሁኔታ ለአመፅ መነሳሳት፣ አድሞ ከት/ቤት መቅረት፣ አድሞ መቀመጥ፣ ንብረት ማውደም፣ እና ለቆ መውጣት።
- የስቴት ወይም የፌደራል ሕግን የሚፃረር ከሆነ፤ ለምሳሌ፡- በተማሪዎች ጤና እና/ወይም ደህንነት ላይ አደጋ ሊያስከትል የሚችል  ዕፅ፣ አልኮሆል፣ እና የትምባሆ አጠቃቀምን ወይም ማንኛውንም ዓይነት ንጥረነገር ማጨስን፣ ዓመፅ፣ ወሲባዊነትን፣ ሕገ -ወጥ መድልዎን፣ ወይም ሌሎች ሕገ -ወጥ ተግባራት።

ቢሆንም ስለእንደነዚህ ያሉ ድርጊቶች ኃላፊነት የተሞላበት ውይይት እንዳይካሄድ ለመከልከል ይህን መመሪያ መጠቀም አይገባም። የአንድ ተማሪን ዝግጅት/መሰናዶ፣ የተማሪን ህትመት፣ ወይም የተማሪዎች የጽሁፍ/ማቴሪያል ስርጭት ማስቆምን በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ርእሰ መምህራን መከተል የሚገባቸውን አካሄድ የMCPS ደንብ JFA-RA ዘርግቷል።

## የፖለቲካ መገልገያ/ቁስ

ማንም ሰው፣ ህገ መንግስታዊ ያልሆነ፣ ህገ ወጥ፣ የስቴት የምርጫ ህጎችን የሚፃረር፣ ወይም፣ በርእሰ መምህሩ/ሯ አስተያየት/አስተሳሰብ፣ ለትምህርት አካባቢ የረብሻ አደጋ ያመጣል ተብሎ የተገመተ የምርጫ ዘመቻ ፅሁፍ/ህትመት ማሰራጨት አይችልም። ይህ ውሳኔ ይግባኝ ሊባልበት ይቻላል። የይግባኙ ቅደም ተከተል በዚህ መፅሔት (ገፅ 11) የይግባኝ-አቤቱታ አቀራረብ ሂደት (Appeals-Complaint Procedure—Due Process) ተገልጿል።

እነዚህን ደንቦች መከተል ከተቻለ ሌላ ፓለቲካዊ ጽሑፎች/ማቴሪያሎች ሊሰራጩ ይችላሉ።

- ጽሑፎች/ማቴሪያሎችን ለሰው ሁሉ ከማደል ይልቅ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች ብቻ ማቅረብ። ይህን ህግ ሳይጥሱ ስርጭት ማድረግ የሚያስችሉ ጥቂት

መንገዶች እነዚህ ናቸው፡- ፍላጎት ላላቸው ብቻ ማሰራጨት፣ መግለጫ ቦታ ማዘጋጀት፣ ወይም ማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ መለጠፍ።

- አንድ ተማሪ የፖለቲካ ቁሶችን በእግረኛ መንገዶች፣ በካፌቴሪያ፣ በሕንፃ ውስጥ መተላለፊያዎች፣ ወይም የተማሪ አስተዳደር ክፍሎችና ስፍራዎች ላይ ሆኖ ማሰራጨት ይችላል። ተማሪዎች በመማርያ ክፍሎች፣ በሚድያ ማእከል፣ ወይም በሌሎች የት/ቤት ክፍሎች በትምህርት ቀን የፖለቲካ ቁሶችን ማሰራጨት አይችሉም፣ ከነዚህ በስተቀር-
  - ክፍሉ ለፈቃደኛ መሰብሰብያ ጥቅም የሚውል ከሆነ፣ ወይም
  - ማቴሪያሉን በክፍል ውስጥ የመደበኛ ማስተማሪያ ፕሮግራም አካል፣ ወይም የበጎ ፈቃድ መድረክ፣ ወይም በተማሪዎች የሚካሄድ ሴሚናር ላይ መጠቀሚያ ሲደረግ።
- የፖለቲካ ቁስ ሁልጊዜ ከትምህርት ክፍለጊዜ ውጭ ብቻ መሠራጨት አለበት።
- የምርጫ ዘመቻ ቁሳቁሶች የፈቃድ መስመር እንዲኖራቸው ያስፈልጋል (የMCPS ደንብ KEA-RA፣ በፖሊቲካ ምርጫ ዘመቻ ተሳትፎና የምርጫ ውድድር ቁሳቁሶች ስርጭትን) ይመልከቱ።

### ተሳትፎ በፖሊቲካ ምርጫ ውድድሮች

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት ሠዓቶችን በፖለቲካ ዘመቻ በመሳተፍ ለማግኘት ተማሪዎች MCPS Form 560-50, Individual Student Service Learning (SSL) Requestበመሙላት ለማንኛውም የፖለቲካ አገልግሎት ቢሮ ለሚወዳደር ሰው አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ፈቃድ ጠይቆ ማግኘት ያስፈልጋል።

*ማጣቀሻዎች፡-*
የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ/Board of Education Policy KBA፣ የህዝብ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ፖሊሲ/Policy on Public Information
MCPS Regulations JFA-RA፣ KBA-RB፣ KEA-RA፣ IGT-RA፣ እና IID-RA።

## ■ የአገር ወዳድነት እንቅስቃሴዎች

ተማሪዎች በት/ቤት በሃገር ወዳድ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ እና/ወይም ለማየት እድል ይኖራቸዋል።

ተማሪዎች በአገርወዳድነት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ ፈቃደኛ ካልሆኑ እንዳ ይገደዱ፣ ወይም ቅጣት እንዳይደርስባቸው፣ ወይም ሃፍረት እንዳይደርስ ባቸው መብታቸው የተጠበቀ ነው።

አንድ ተማሪ ሌሎች የአገር ወዳድ እንቅስቃሴዎች በሚሳተፉት ላይ ጣልቃ በመግባት ማስተጓጎል/ማቃወስ አይ(ት)ችልም።

*ማጣቀሻዎች፡-*
በሜሪላንድ የትምህርት ኮድ (Annotated Code of Maryland)፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-105

## ■ የሃይማኖት ነፃነት

ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው—

- ከኃይማኖት ጋር ያልተያያዙ/ገለልተኛ ከሆኑና የኃይማኖት ነክ ድርጊቶችን የማያካትቱ በት/ቤት አማካይነት የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች፤ እና
- በኮርሶች ወይም ት/ቤት በሚያካሄዳቸው የምረቃ ፕሮግራሞች ወይም ስብሰባዎችን በመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ኃይማኖት ነክ እምነቶች በማይሰበክባቸው አካባቢ፤ እና
- የሌሎችን መብት ካልጣሱ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን ካላስተጓጉሉ በቀር በትምህርት ቤት የማይደገፉ የተማሪ የጸሎት ቡድኖችን ጨምሮ በትምህርት ቤት ውስጥ የሃይማኖታዊ ልምዶቻቸውን ማክበር።

ቦርዱ የMCPS ተማሪ ሕብረተሰብን ልዩ ልዩ ኃይማኖቶችን፣ እምነቶችን፣ እና ባህሎችን ለማክበርና እውቅና ለመስጠት ቁርጠኛ ነው/ቁርጠኝነቱን ገልጧል። MCPS የኃይማኖት ልዩነቶችን ስለማክበር መመሪያየ MCPS ህጎችን በሚመለከት ዲስትሪክቱ እንደ ማመሳከሪያ የሚመራበትን መግለጫ ይፋ ያደርጋል።

*ማጣቀሻዎች፡-*
*ሃይማኖታዊ ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች*
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation IKB-RA

## ■ ክበቦች፣ ቡድኖች፣ እና የተማሪ ድርጅቶች

ተማሪዎች ከለቦችን፣ ቲም/ቡድን፣ የተማሪ ድርጅቶችን ለመፍጠር እና ለመሳተፍ መብት አላቸው እና ተሳትፎአቸውን ለመገደብ የሚችሉ ተገቢ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦችንየማገናዘብ/የማወቅ ኃላፊነት አለባቸው።

MCPS ሁሉን አቀፍ የሆነና በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ የአትሊ ቲክስ ፕሮግራም የMCPSና የMaryland Public Secondary School Athletic Association (የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች አትሌቲክስ ማህበር) መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ሁሉም ተማሪዎች ያቀርባል። በት/ቤቶች መካከል በሚካሄዱ አቴሌቲክስ የሚሳተፉ ተማሪዎች በMCPS የአቴ ሌቲክ ድር ገፅ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/athletics/ የሚገኙ ከጤናና ከደህንነት የተያያዙ መረጃዎችን እንዲያነቡ ይጠበቅባቸዋል።

አከራካሪ እና ውስብስብ ማህበራዊ እና ህጋዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት በማድ ረጋቸው ምክንያት ብቻ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ቡድን ከመፍጠር ሊያግዱ አይችሉም።

*ማጣቀሻዎች፡-*
የቦርድ ፖሊሲ IQD
*የተማሪ አመራር እና ከሥርዓተ ትምህርት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ዳይሬክተር*

Director of Student Leadership and Extracurricular Activities፡- 240-740-4692

### በት/ቤት የተደገፋ/ስፖንሰር የተደረጉ ድርጅቶች

ተማሪዎች በክለቦች፣ በቡድኖች፣ ወይም የተማሪ ድርጅቶች ላይ በመሪነት ደረጃ ለመስራት ለመመረጥ ወይም ምደባ የሚፈልጉ ተማሪዎች ጥሩ ስነ-ምግባር፣ ሕግ አክባሪነትን፣ የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን ህጎች መታዘዝ ጨምሮ መልካም ጠባይ፣ በMCPS ቅጥር ግቢም ይሁን  ከውጭ ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል። የዲሲፒሊን ህጎችና ደንቦችን ለማስጠበቅ ርእሰ መምህራን ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ ቁጥጥር/ገደብ የማድረግ ስልጣን ይኖራቸዋል። የተፈቀደላችው የተማሪ ድርጅቶች በት/ቤት መገልገያዎች የመጠቀም መብት አላቸው። ይህም የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ የድምፅ ማስተላለፍያ/ማጉያ መገልገያዎች/የህዝብ መድረሻ ስርዓት፣ እና የፎቶኮፒ መሳርያዎች አግባብነት ያለው አጠቃቀምን ያካትታል።

### ት/ቤት ስፖንሰር የማያደርጋቸው የተማሪ ድርጅቶች

የሚከተሉትን ሀላፊነቶች እስከተወጡ ድረስ ተማሪዎች ትምህርት በማይሰ ጥበት ጊዜ ስብሰባ የማካሄድ መብት አላቸው።

- ስብሰባው የደህንነት ወይም የፀጥታ አደጋ ስጋት አያስከትልም።
- ስብሰባዎቹ በፈቃደኝነትና በተማሪዎች ተነሳሽነት የተዘጋጁና በት/ቤት ያልተወከሉ ወይም በት/ቤት የተደገፉ ተደርገው የማይወሰዱ ናቸው።
- የት/ቤት ሰራተኞች ስብሰባዎችን ስፖንሰር አያደርጉም ወይም አያስተዋዉቁም፤ ሆኖም ግን የት/ቤት ሠራተኛ አባል ስለደህንነት ጥንቃቄ ሊቆጣጠር/ልትቆጣጠር  ይችላል/ትችላለች።
- የት/ቤት ተቀጣሪዎች/ሰራተኞች ስብሰባዎቹን አይመሩም ወይም አይሳተፉም፣ የሃይማኖት ስብሰባዎችንም ጨምሮ።
- ስብሰባው በት/ቤቱ ውስጥ በስርዓት ከሚመራዉ የትምህርት እንቅስቃሴዎች አፈፃጸም ጋር በማንኛውም ሁኔታ  ከፍተኛ ጣልቃ የመግባት/የማደናቀፍ ሁኔታ ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም።
- ከትምህርት ቤት ያልሆኑ ሰዎች በስብሰባዎች ላይ አይመሩም ወይም አዘውትረው አይገኙም።
- የህዝብ ገንዘብ ለስብሰባዎቹ ወጪ አይደረግም (ለመሰብሰቢያ ቦታ አቅርቦት ወጪ አይጨምርም)።

*ማጣቀሻዎች፡-*
የቦርድ ፖሊሲ-Board Policy IOB, እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንቦች-MCPS Regulations IGO-RA, IQD-RA, IQD-RB

# ■ ቴክኖሎጂ

## ኃላፊነት የተሞላበት የተማሪ መመርያዎች አጠቃቀም
## Student Responsible Use Guidelines

MCPS ከተልእኮው ጋር የሚሄዱ የኮምፒውተር መሣርያዎችን፣ የኮምፒ ውተር አገልግሎቶችን፣ ከት/ቤቶች እና ከተማሪዎች ጋር መገናኛ የውሂብ/የኔትዎርክ አገልግሎት ያቀርባል። ለMCPS ተማሪዎች ክፍት የሆነው ስፋት ያለው በርካታ የመረጃ ቴክኖሎጂ አዳዲስ መልካም እድሎችን እና ስጋቶችን ያስተዋውቃል። ተማሪዎች ቴክኖሎጂን በሚገለገሉበት ጊዜ ተገቢ/መልካም የአጠቃቀም ስነ-ምግባር እንዲኖራቸው ማሳወቅ እና መሠረት ማስያዝ የት/ቤት ሠራተኞች እና የእያንዳንዱ ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ የጋራ ኃላፊነት ነው። በት/ቤቶች፣ የተማሪዎች የድረ-ገጽ/ኦን ላይን መገናኛ መስመር አጠቃቀም እንቅስቃሴዎች በስርአት-አቀፍ ቴክኖሎጂ የመከላከል ጥበቃ እርምጃዎች በት/ቤት ሰራተኞች አማካይነት ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። ተማሪዎች መረጃ ዎችንና መገልገያዎችን ከስርቆሽ፣ በተንኮል ከሚደረስ ጉዳት፣ ከአልተ ፈቀደ አጠቃቀም፣ ከሚያስተጓጉልና ከኪሳራ መጠበቅ/መከላከል እንዲሁም የአካባቢ፣ የስቴትና፣ የፌዴራል ህጎችን ማክበር አለባቸው።

በ MCPS ደንብ IGT-RA የተደነገገውን ደንብ ሁሉም የ MCPS ተማሪዎች ለመከተል ይስማማሉ  ለኮምፒውተር ሲስተሞች፣ ለኤሌክት ሮኒክስ መረጃ እና ለኔትወርክ ደህንነት የተጠቃሚ ኃላፊነቶች ፤ እና የ MCPS ደንብ COG-RA፣  የግል ተንቀሳቃሽ መሣሪያዎች ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፦

- ተማሪዎች የ MCPS ኔትወርክን ውጤታማ፣ ተገቢ እና ከት/ቤት ጋር ለተያያዙ ዓላማዎች ብቻ የሚጠቀሙ ሲሆን ከዲስትሪክቱ፣ ከተማሪው ወይም በተማሪው ቤተሰብ የተሰጠውን ማንኛውንም የቴክኖሎጂ ሪሶርስ የሌሎች ተማሪዎችን እና የሥራ ባልደረቦችን እንቅስቃሴ በሚያስተጓጉል መልኩ ከመጠቀም ይቆጠባሉ።
- ተማሪዎች ኢሜል እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን (ለምሳሌ፡- ትዊተር፣ ብሎጎች፣ ዊኪዎች፣ ፖድካስት ማድረግያ፣ ጭውውት፣ ፈጣን መልእክት፣ የውይይት ሰሌዳዎች፣ ቨርቹወል የመማሪያ መድረኮችን) ኃላፊነት በተሞላበት አኳኋን ይጠቀማሉ።
- ተማሪዎች የሌሎችን ሃሳቦች እና ሥራዎቻቸውን እውቅና ይሰጣሉ።
- ተማሪዎች የግል መረጃዎችን (የቤት/ሞባይል ስልክ ቁጥሮችን፣ የፖስታ አድራሻ፣ እና የተጠቃሚ ሚስጥር ቃል) እንዲሁም የሌሎችን በሚስጢር ይይዛሉ።
- ተማሪዎች ከአግባብ ውጭ የሆነ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ወድያውኑ ያስታውቃሉ።
- አግባብነት የሌለው አጠቃቀም ተለይቶ ካልታወቀ የ MCPS ኃላፊዎች የትኛው አይነት አጠቃቀም ከአግባብ ውጭ መሆኑን ለማወቅ/ለማረጋገጥ ደንብ እና መመሪያዎችን ለመጠቀም እንደሚችሉ ተማሪዎች ይረዳሉ።
- ሁሉም የMCPS መሳርያዎች የMCPS አውታረ መረብ፣ እና ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው የMCPS አውታረ መረብ አካውንት የMCPS ንብረት መሆናቸውን እና ቁጥጥር እንደሚደረግባቸው፣ እንደሚከፈቱ፣ እና በአውታረ መረብ ፋይል እንደሚያዙ ተማሪዎች ይገነዘባሉ።
- ተማሪዎች (ህግን/መመሪያን) የሚተላለፍ/የማያከብር ድርጊት ቢፈጽሙ፣ ድርጊታቸው ኮምፒዩተር ከማግኘት መብት/ጥቅም መታገድን፣ የስነስርአት ርምጃ፣ እና/ወይም ወደ ህግ አስፈጻሚዎች መመራት የሚያጠቃልሉ እርምጃዎችን ሊያስከትል እንደሚችል ይረዳሉ።

### የግል ሞባይል መገልገያዎች

ሞባይል ስልኮች፣ የድምጽ ማንበቢያ መሣሪያዎች (e-readers)፣ እና/ወይም ታብሌቶች (tablets) ካሜራዎች የተገጠሙባቸው ተንቀሳቃሽ ስልኮች፣ የግል ኮምፒተሮች ወይም ሌሎች መሣሪያዎች እና ከ MCPS ውጭ የተሰጡ ሌሎች መሣሪያዎች ሁሉም እንደ የግል ተንቀሳቃሽ መሣሪ ያዎች (PMDs) ይቆጠራሉ እና የ MCPS ደንብ COG-RA በማክበር መጠቀም ይቻላል፣  የግል ተንቀሳቃሽ መገልገያ መሣሪያዎች  እና የ MCPS ደንብ IGT-RA፣  ለኮምፒውተር ሲስተሞች፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃ እና የአውታረ መረብ ደህንነት ኃላፊነቶች ።

የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ፣ የተማሪዎችን ጤና እና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል፣ ጸያፍ የሆነ፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን የሚያሰናክል፣ የሌሎችን ሥራ የሚያማልል ወይም የንግድ ማስታወቂያ ከሆነ PMD በመጠቀም መረጃ ሊተላለፍ አይችልም።

የግል ተንቀሳቃሽ መገልገያዎቹ (PMDs) የMCPS ደንቦችን ባልተ ከተለ መንገድ ጥቅም ላይ ከዋለ በት/ቤት ባላሥልጣናት ሊነጠቁ/ሊወረሱ ይችላሉ። በግል ተንቀሳቃሽ የመገልገያ እቃዎች መጥፋት፣ በእቃዎቹ ላይ የስርቆት ወንጀል መፈጸም፣ ወይም ብልሽት መድረስ ወይም እነዚህን የመሰሉ ማናቸውም መሣሪያዎች ባልተፈቀደ ሁኔታ ለመጠቀም MCPS ኃላፊነት ወይም ተጠያቂነት አይወስድም።

MCPS የተማሪዎችን ጎጂ የኢንተርኔት ድረ-ገጾችን አጠቃቀም ለመገ ደብና ለማጣራት ሌሎች የቴክኖሎጂ እርምጃዎችን ይጠቀማል። የግል ሴሉላር አውታረ መረቦች ተመሳሳይ የማጣሪያ መለኪያዎች ስለማይ ኖራቸው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ተማሪዎች ይበልጡን የ MCPS ኔትወርክ (ማለትም የግል ሴሉላር ኔትወ ርኮች አይደሉም) ለኢንተርኔት አገልግሎት ይጠቀማሉ። አንድ ተማሪ የሞን ትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አውታረመረብ ያልሆነ ነገር ግን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ ሌላ ኢንተርኔት PMD ከተጠቀመ(ች) ተማሪው(ዋ) የዚህን ደንብ መስፈርቶች የማሟላት ግዴታ አለበ(ባ)ት።

ተማሪዎች የ MCPS በሆኑ ቦታዎች  እና በ MCPS በሚደገፉ ዝግጅቶች ላይ  PMDs መጠቀም ይችላሉ። ተማሪዎች PMDs እንዲጠቀሙ የሚፈቀ ድላቸው ከታች በተገለጸው መሰረት ብቻ ነው።

ሁሉም ትምህርት ቤቶች፡-

- ለተማሪው(ዋ) ልዩ ፍላጎት የተመቻቸ PMD፣ የትምህርት አገልግሎት ወይም ድጋፍ ለመስጠት በሚውልበት ጊዜ፣ የግለሰባዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ወይም 504 እቅድ ያላቸው ተማሪዎችን ጨምሮ በተለይ መጠቀም የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች፣ ትምህርት የመቀበል ልዩነት ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች። IEP ወይም 504 እቅድ ለሌላቸው ተማሪዎች PMD መጠቀም እንደሚያስፈልጋቸው ሲገልጹ እንደዚህ አይነት አጠቃቀም የሚፈቀደው ከትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ጋር በመተባበር በርእሰመምህሩ አማካይነት ነው።
- ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ወይም ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር ወደተደረጉ እንቅስቃሴዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ወይም ቻርተር በተደረጉ አውቶቡሶች ሲጓዙ የአውቶቡስ ደህንነትን እና ተግባርን ካላሰናከለ እና እነዚህ እና ሌሎች ተዛማጅ የ MCPS ህጎችን ካልተጣሰ  PMDs ለመያዝና ለመጠቀም ይችላሉ።
- ለመጠቀም ባልተፈቀደ ጊዜ PMDs እንዲጠፉ እና እንዳልያዙት ማረጋገጥ የተማሪው(ዋ) ሃላፊነት ነው።
- PMDs በማንኛውም ወቅት በኣስተማማኝ ሁኔታ መያዛቸውን ማረጋገጥ የተማሪዎች ሃላፊነት ነው።

የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች PMDs ከትምህርት ቀን በፊት ወይም በኋላ ሊጠቀሙ ይችላሉ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በትም ህርት ጊዜ፣ በምሳ ሰአት፣ ወይም በክፍለጊዜዎች ሽግግር ሠዓት PMD መጠቀም አይፈቀድላቸውም።

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች PMDs ከትምህርት ቀን በፊት ወይም በኋላ ሊጠቀሙ ይችላሉ። የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በክፍል ትምህርት ሠዓት/በሽግግር ሠዓት PMD መጠቀም አይፈቀድላ ቸውም። ከትምህርት ጋር ተያያዥ ለሆነ ጉዳይ በአስተማሪ ፍቃድ መጠቀም ይቻላል። በምሳ ሰአት ለመጠቀም ከትምህርት ቤቱ አመራር ቡድን ጋር በመተባበር በርዕሰ መምህሩ ውሳኔ ሊፈቀድ ይችላል።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች PMDs ከትምህርት ቀን በፊት ወይም በኋላ እና በተማሪው ምሳ ወቅት መጠቀም ይችላሉ። ከትምህርት ጋር ተያያዥ ለሆነ ጉዳይ በአስተማሪ ፍቃድ መጠቀም ይቻላል። በክፍለጊዜዎች ሽግግር ጊዜ መጠቀም በዳይሬክተሩ ምርጫ ከትምህርት ቤቱ አመራር ቡድን ጋር በመተባበር ሊፈቀድ ይችላል።

ማጣቀሻዎች፦

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንቦች-MCPS Regulations COG-RA እና IGT-RA

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ-MCPS የተማሪ ስነምግባር ደንብ-Student Code of Conduct)(

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የማህበራዊ መገናኛዎች/MCPS Social Media ፡- ለሠራተኞች እጅግ ጠቃሚ ምክሮች/ልምምዶች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ-MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ደንብ-Employee Code of Conduct

ስለተማሪ የግል ህይወት/ጉዳይ መመሪያ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዓመታዊ ማስታወቂያ

ለኢሜል እና ለሌሎች ዲጂታል ግንኙነቶች MCPS ምርጥ ተሞክሮዎች

## ■ አድሎአዊ አሠራርን ስለማስቀረት

ቦርዱ ሁሉም ተማሪዎች እና ሰራተኞች የግለሰቦችን ትክክለኛ ወይም በይሆናል ግንዛቤ የግል ባህሪያትን ሳይጨምር እርስ በእርስ መከባበርን በሚያሳዩበት መንገድ ዘርን፣ ጎሳን፣ ቀለምን፣ የዘር ሐረግን፣ የትውልድ ቦታን፣ ዜግነትን፣ ሃይማኖትን፣ የስደተኝነት ሁኔታን፣ ጾታን፣ የሥርዓተ -ፆታ ማንነትን፣ የሥርዓተ -ፆታ መግለጫን፣ ወሲባዊ ዝንባሌን፣ የቤተሰብ አወቃቀር/የወላጅነት ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ (ዕውቀት፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት፣ እና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በሕጋዊ ወይም በሕገ መንግሥት የተጠበቁ ባህሪዎችን ወይም ግንኙነቶችን በሙሉ የሚያክብር ስነምግባር እንዲኖራቸው ይጠበቅባቸዋል።

ማናቸውም ዓይነት ህገወጥ የሆኑ አድሎአዊ አሠራሮች ከትግስት ውጪ ከመሆናቸውም በላይ ተቀባይነት አይኖራቸውም። የቦርዱ መርህ/ፖሊሲ "Board Policy ACA" መድሎ የሌለበት የእኩልነት/ፍትሃዊና፣ የዳበረ ባህልን በማስፈን ሁሉንም ተማሪዎች እንዲልቁ እና ዓለም አቀፋዊ አስተ ሳሰብ ባለው ኅብረተሰብ ውስጥ እንዲኖሩና እንዲሰሩ የሚያዘጋጀውን ማዕቀፍ መመስረት፣ እና ሁሉንም ልዩ እና ግላዊ ልዩነቶች የሚያቅፍ አዎንታዊ የትምህርት ሁኔታን ያበረታታል።

መድሎአዊነት የሚያካትተው በቅንዓት ተገፋፍቶ ግለሰቦች ላይ ያነጣጠረ ምንም እርግጠኝነት በሌለው ነገር በይሆናል የግል ባህርይ የጥላቻ ድርጊቶች፣ የሃይል/የአመጽ ድርጊቶች፣ ደንታቢስነት፣ የንቀት ተግባር፣ የበቀል እርምጃ፣ ማንቋሸሽ፣ ማዋከብ፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ መሳደብ፣ ማስፈ ራራት፣ ዝርፊያ፣ ወይም ንብረት ማውደም/ማፈራረስ፣ የትምህርት ወይም የሥራ አካባቢ ላይ እንቅፋት/የሚያስተጓጉሉ እንቅስቃሴዎችን መፈጸም ናቸው። አድልዎ ላይላዩን ግልጽ ያልሆነ ነገር ግን በግላዊ ባህርይ ሁኔታ ወይም ግምታዊ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ተገቢ ያልሆነ ተፅእኖ ያላቸው ልዩነቶችን የማድረግ ስነምግባሮችን ወይም ልምዶችን በተጨማሪ ያካትታል። አድልዎ፡- ዘረኝነትን፣ ፆተዊ ትምክህተኛነት/sexism፣ እና ድርጅታዊ ስር የሰደዱ አግባብነት የሌላቸው ጥላቻዎችን ከሞላ መገለጫዎ ቻቸው ጋር ያካትታል።

ከላይ በተዘረዘሩት ግላዊ ባህሪያት ላይ በመመስረት በተማሪዎች ላይ የሚደርስ መድልዎን በሚመለከት ቅሬታዎች፣ ስጋት ወይም ጥያቄዎችን በት/ቤት ደረጃ መፍታት ካልተቻለ፣የዲስትሪክቱ ዋና ኦፕሬሽን ኃላፊ/የተማሪ ደህንነት እና ሥርዓት አክባሪነት ውሳኔ የመስጠት ሃላፊነት አለበት። ለተጨማሪ መረጃ፥ በዚህ የመመሪያ መጽሔት የኋላ ሽፋን ውስጠኛው ገጽ ላይ የሚገኘውን ፀረ-መድልዎ መግለጫ ይመልከቱ። የግል ሁኔታን መሠረት ያደረገ በጉልበት ዛቻ ማድረግ፣ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ወይም ወከባ ተከስቶ ከሆነ ተማሪዎች MCPS Form 230-35 በመሙላት በጉልበት ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ወይም ወከባ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ፣MCPS Regulation JHF-RA ላይ እንደተገለጸውተማሪን ማስፈ ራራት፣ ማስጨነቅ፣ ወይም ወከባ። የአካል ስንክልና ያለባቸው ተማሪዎች የሚያቀርቡት ቅሬታ/ስሞታ በሚከተለው አድራሻ፡- Office of Special Education, Resolution and Compliance Unit, የስልክ ቁጥር፡- 240-740-3230 ወደ ልዩ ትምህርት ጽ/ቤት ሊመራ ይችላል።

ማጣቀሻዎች፡-

የቦርድ ፖሊሲ-Board Policy ACA፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation JHF-RA

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ-MCPS የተማሪ ስነምግባር ደንብ-Student Code of Conduct)(

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ-MCPS የሠራተኛ ስነምግባር ደንብ-Employee Code of Conduct

ሃይማኖታዊ ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለተማሪ የጾታ ምንነት መገለጫ የ MCPS መመሪያ

## ■ ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈ ራራት

በሜሪላንድ ህግ መሠረት፣ ጉልበት/ሥልጣን ተጠቅሞ መጨቆን-ማጥቃት፣ የዘር/የጾታ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት/ማስገደድ የማይታገሱት ከባድ ነገር ነው። የ MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራሪያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ፣ በተማሪ መሞላት አለበት፤ የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ወይም የቅርብ ዘመድ; ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኛ አባል ስለደረሰብኝ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ሪፖርት ለማድረግ። የተሞላው ቅጽ ተጎድቷል ለተባለው ተማሪ ትምህርት ቤት ለርእሰመምህሩ መመለስ አለበት። ለተጨማሪ መረጃ ወይም ዕርዳታ ትምህርት ቤቱን በማንኛውም ጊዜ ማነጋገር ይችላሉ።

ቦርዱ የሳይበር ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን (ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ ወይም MCPS ንብረት ውስጥ ያለ ማንኛውንም ሰው የጥላቻ አድሎአዊ ድርጊቶችን ጨምሮ የቃል፣ የአካል ወይም የጽሁፍ (የኤሌክትሮኒክስ ጨምሮ) ጉልበተኝነት የተከለከለ ነው። ይህም ትምህርት ቤቶችን፣በ MCPS የሚተዳደሩ ግቢዎችን ወይም የ MCPS አውቶቡሶችን፣ ፋሲሊቲዎችን እና/ወይም በ MCPS የሚደገፉ ተማሪዎችን በሚያ ካትቱ እንቅስቃሴዎች ላይ የኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሚከናወኑ ትንኮሳዎችን ሁሉ ያካትታል።

በሜሪላንድ ህግ መሰረት፣ የቦርድ ፖሊሲ JHF የተከለከለ ባህሪ ማለት ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ማለት ነው-

- ሆን ተብሎ የሚደረግ መጥፎ ተግባር፣ የቃል፣ የአካል ወይም የጽሁፍ ባህሪ፣ ወይም በ MCPS ንብረት ላይ ሆን ተብሎ የሚደረግ ያልተገባ የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት፣ በትምህርት ቤቶች፣ MCPS በሚያስተዳድራቸው ግቢዎች፣በ MCPS አውቶቡሶች፣ ተቋም እና/ወይም የ MCPS ተማሪዎችን የሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች ላይ፣ ወይም የትምህርት ቤቶችን ተግባራት በእጅጉ የሚያበላሹ ስነምግባሮችን ሁሉ ያካትታል፣ እና
- በተማሪው የትምህርት ጥቅሞች፣ እድሎች ወይም አፈጻጸም ላይ፣ ወይም በተማሪው አካላዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጣልቃ በመግባት ከጥላቻ የመነጨ የትምህርት አውድ መፍጠር፣ እና –
  - » በቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድሎአዊ አለመሆን፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃት በተገለጹት ተጨባጭ ወይም በሚታዩ ግላዊ ባህሪያት የተነሳሳ፤
  - » ወሲባዊ ተፈጥሮ፣ የተማሪ የሰውነት ክፍሎች የተጋለጠበት ወይም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተግባር ላይ ያለ ተማሪን የሚገልጥ ተግባር ወይም ምስሎችን ጨምሮ፤ ወይም
  - » ማስፈራራት ወይም ከባድ ማስፈራራት

በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) መመሪያ መሰረት፣ የሚከተሉት ትርጓሜዎች ጉልበተኞች (ሳይበር ጉልበተኝነትን ጨምሮ)፣ ትንኮሳ፣ ወይም MCPS ንብረት ላይ ያለ ማንኛውንም ሰው ማስፈራራትን ለመከላከል ጥቅም ላይ ይውላሉ፡

ጉልበተኝነት ማለት በተማሪዎች መካከል ያልተፈለገ ወራዳ ባህሪ ማለት በፖሊሲ JHF የተከለከለ ስነምግባር መስፈርት የሚያሟሉ እና የሚከተሉትን ያጠቃልላል –

- » የሃይል አለመመጣጠን (ጉልበተኞች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ ወይም አካዳሚያዊ ሀይላቸውን ተጠቅመው ሌሎችን ለመቆጣጠር፣ ለማግለል ወይም ለመጉዳት መጠቀም) እና
- » መደጋገም (ከአንድ ጊዜ በላይ የተከሰቱ የጉልበተኝነት ባህሪያት ወይም በሚሰበሰቡ መረጃዎች ሊረጋገጡ የሚችሉ የመደጋገም ዕድላቸው ከፍተኛ የሆነ ጉልበተኝነትን ማሳየት)።

ሳይበር ጉልበተኝነት ማለት በፖሊሲ JHF ውስጥ የተከለከሉ ድርጊቶችን መስፈርቶች የሚያሟላ እና በተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሳሪያ አማካኝነት ግለሰቦች እንዲመለከቱት ወይም እንዲያጋሩ በሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት የሚተላለፍ ትንኮሳና ጉልበተኝነት ማለት ነው።

- » የሳይበር ጥቃት ስለ አንድ ሰው ውርደትን የሚያስከትል የግል ገመና ወይም ግላዊ መረጃን ማሠራጨት፣ መለጠፍ ወይም ማዳረስን ያጠቃልላል።
- » በትምህርት ቤት መቼት የሳይበር ጥቃት ከተፈጸመ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል። ትምህርት የሚሰጠው በአካል ወይም ቨርቹወል ቢሆንም በትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ላይ የጉዳት አደጋን ይፈጥራል፣ ወይም የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ያውካል።

የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት ስልክ፣ ኮምፒውተር፣ ወይም ተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሣሪያን ጨምሮ በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የሚተላለፍ ግንኙነት ነው።

ትንኮሳ ማለት በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው በፖሊሲ JHF ውስጥ የተከለከሉ ድርጊቶችን መስፈርት የሚያሟሉ እና የአንድን ግለሰብ ትክክለኛ ወይም በይሆናል የሚታሰብ የግል ባህሪያትን በተመለከተ ሌላ ግለሰብን ማስቀየም፣ መሳለቂያ ማድረግ ወይም ማዋረድ ማለት ትክክለኛ ወይም የተገነዘቡ አሉታዊ ድርጊቶች ማለት ነው፣ አድሎአዊ ያልሆነ፣

ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ፣ ወይም ወሲባዊ ተፈጥሮ ያላቸው ናቸው፣ በቦርድ ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ጾታዊ ትንኮሳ ፣ ወይም የቦርድ ፖሊሲ ACI፣ የሰራተኞች ጾታዊ ትንኮሳ ፣ የተማሪው የሰውነት ክፍሎች የተጋለጠበት ወይም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተግባር ላይ እያለ(ች) የሚያሳይ መግለጫዎች ወይም ምስሎችን ይጨምራል።

ማስፈራራት ማለት በፖሊሲ JHF የተከለከለ የስነምግባር መስፈርቶችን የሚያሟሉ እና የፍርሃት እና/ወይም የበታችነት ስሜትን የሚፈጥር ወይም የሚያነሳሳ በሌላ ግለሰብ ላይ የሚደረግ ማንኛውም እርምጃ ነው። የበቀል እርምጃ እንደ ማስፈራራት ሊቆጠር ይችላል።

ቦርዱ የጉልበተኝነት ትንኮሳን ወይም የማስፈራራት ድርጊቶችን ሪፖርት በሚያደርጉ ግለሰቦች ላይ ማናቸውንም የበቀል እርምጃ ለመከላከል ቁርጠኛ ነው። በጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ተጎድተዋል የተባሉ ተማሪዎችን፤ ወይም ምስክሮችን፣ ተመልካቾችን፣ ወይም ሌሎች ስለ ጉልበተኝነት ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራራት ድርጊት አስተማማኝ መረጃ ያላቸው ግለሰቦችን ከበቀል እርምጃ ለመታደግ ቁርጠኛ ነው።

ጉልበተኝነት አካላዊ (መምታት፣ መግፋት፣ መገፍተር) ሊያካትት ይችላል ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን የቃል (መሳለቅ፣ ማስፈራራት፣ ማስገደድ፣ መሳለቂያ ማድረግ፣ የስድብ ስም መጥራት) ወይም ተዛማጅ የሆኑ(ወሬ ዎችን ማሰራጨት፣ ወይም ማግለል) ነው።

ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ከተከሰተ ተማሪ፤ የተማሪ ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም የቅርብ ዘመድ፤ ወይም የትምህርት ቤት ሰራተኛ በ MCPS ደንብ JHF-RA ድንጋጌ መሠረት የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ደንብ ላይ እንደተገለፀው የ MCPS ቅፅ 230-35 ስለ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራሪያ ሪፖርት ቅጽ ሞልቶ(ታ) ማቅረብ አለበ(ባ)ት። እና ወዲያውኑ ለት/ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም ተገቢውን የሕዝብ ትምህርት ቤት ባለሥልጣን/አስተዳዳሪ ማሳወቅ ይገባል። የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጹ ተሞልቶ በወረቀት፣ በአካል ወይም በኦንላይን MCPS ድረ ገጽ ላይwww.montgomeryschoolsmd.org/info/bullying ለቀርብ ይችላል። የት/ቤት ኃላፊ/አስተዳዳሪ ሁሉም ወገን ማስረጃ የሚያቀርቡበትን እድል ጨምሮ በፍጥነት ተገቢ፣ ተአማኒነት ያለው፣ እና አድሎ የሌለበት ምርመራ ያደርጋል/ታደርጋለች። ምርመራው እንደተጠናቀቀ፣ የትምህርት ቤት ኃላፊ/አስተዳዳሪ የመፍትሔ ርምጃዎችን እና ውጤቶችን እንደየአግባቡ ተግባራዊ ያደርጋል/ታደርጋለች፣ ጥቃቶችን፣ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ ማስገደድ የመሣሰሉትን ነገሮች ድጋሚ እንዳይከሰቱ እርምጃ መዉሰድ እና እንዲሁም ለወላጆች/ለሞግዚቶችም ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

### ተገቢ ያልሆነ ወሲባዊ ጠባይ እና ወሲባዊ ትንኮሳ

MCPS በማንኛውም ዓይነት የትምህርት መርሃ ግብሮች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ ወይም በንብረቱ ላይ በማንኛውም ዓይነት የጾታ ብልግና ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ አይታገስም። ይኼውም፡- እንደ ወሲባዊ ስነምግባር ወይም የወሲብ ትንኮሳ ሊቆጠር የሚችል ተቀባይነት የሌለው ድርጊትን ሊያካትት ይችላል፤ ነገር ግን በዚህ አይገደብም—

- አስጸያፊ ቀልዶች፣ ስድቦች፣ ፀያፍ ምሳሌዎች ወይም ያልተገባ ስም መጥራት፣ አካላዊ ጥቃቶች ወይም ዛቻዎች፣ ማስፈራራት፣ መሳለቅ ወይም ፌዝ፣ ስድብ ወይም ማዋረድ/ማሳፈር፣ አፀያፊ ነገሮች ወይም በግለሰቦች ላይ ወይም በአንድ የተወሰነ ቡድን ላይ የተቃኙ ሥዕሎች፥
- በዚያ ግለሰብ ወይም ቡድን ትክክለኛ ወይም በይሆናል ግምት የጾታ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የሥርዓተ-ፆታ ማንነት፣ የሥርዓተ-ፆታ አገላለጽ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የእርግዝና/የወላጅነት ሁኔታ፣ እና/ወይም በጾታ ላይ የተመረኮዘ አመለካከት፣ በወንድነት ወይም በሴትነት አመለካከት ላይ የተመሠረተ አመለካከት ወይም አለመስማማት ላይ በመመስረት፣ ወይም
- የወሲባዊ ጥቃት፣ በፍቅር ጓደኝነት ውሎ ላይ የሚፈጸም ሁከት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ ወይም ማሳደድን ይጨምራል።

የጾታ ብልግና ወይም የወሲብ ትንኮሳ ቅሬታዎች ሪፖርት መደረግ አለባቸው። በ MCPS ደንብ JHF-RA ውስጥ በተቀመጡት ቅደም ተከተሎች መሠረት MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም የማስፈራራት ሪፖርት ቅጽ ለትምህርት ቤት ሠራተኞች ወይም ለርእሰ መምህሩ መስጠት አለበት። የተማሪዎች ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ። የወሲባዊ ሥነ ምግባር ጉድለትን ወይም የወሲባዊ ትንኮሳን ሁኔታ ሪፖርት በማድረጉ(ጓ) ምክንያት ወይም በምርመራ ላይ በመሳተፍ ወይም በመተባበር ምክንያት በግለሰቡ(ቧ) ላይ ምንም ዓይነት አሉታዊ እርምጃ አይወሰድም።

በአንዳንድ ሁኔታዎች የወሲባዊ ጥሰት ወይም የወሲባዊ ትንኮሳ የሕፃናትን በደል ወይም ቸልተኝነትን ሊያመለክት ይችላል። የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ወድያውኑ ለChild Welfare Services/የልጅ ደህንነት አገልግሎቶች (በተጨማሪ Child Protective Services/የልጅ ከለላ አገል ግሎቶች ተብሎ በዘልማድ ለሚጠራው) በMCPS ደንብ JHC-RA፣ የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ሪፖርት ምርመራ የተቀመጡትን ቅደም ተከተሎች በመከተል መቅረብ አለባቸው። ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሪፖርት መደረጉን በተመለከተ ጥርጣሬ ያላቸው ግለሰቦች ሪፖርት ማድረግ ትክክለኛ አቅጣጫ ነው።

- ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ማንኛውንም አድልዎ እና/ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ በ TitleIX@mcpsmd.org ለ Title IX አስተባባሪ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን የሚመለከቱ ሪፖርቶች እና ቅሬታዎችን ወዲያውኑ "Office of Human Resources and Development, Department of Compliance and Investigations (DCI)" ሊመለከተው ይችላል። DCI@mcpsmd.org ሊደረሳቸው ይችላል
- Safe Schools Maryland Tip Line ዛቻ-ማስፈራራት እና/ወይም ለደህንነት የሚያሰጋ ሁኔታን እና/ወይም የተማሪዎችን ደህንነት የሚያሰጉ ሁኔታዎችን ይፋ የማይደረግ ሪፖርት የሚቀርብበት ሲስተም ነው። 1-833-MD-B-SAFE ይደውሉ ወይም "app" ያውርዱ-ይጫኑ።
- ሌሎች ሪሶርሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ ስልክ መስመር 240-777-4357 ወይም 301-738-2255 (EveryMind) ያካተተ ሲሆንበማዳመጥ ድጋፍ ለመስጠት እና መረጃ ለመለዋወጥ የሰለጠነ ሠራተኛ ወይም በጎ ፈቃደኛ ይገኛል። EveryMind የስልክ መስመር በየቀኑ 24 ሰዓት በሳምንት ሰባቱንም ቀኖች ይሠራል። "EveryMind" እንዲሁ ሰው ከማነጋገር ይልቅ ቴክስት መፃፍ ለሚመርጡ ሰዎች የተዘጋጀ መለያ አለው። EverMind የውይይት ባህሪ፣ Chat Now፣ https://www.every-mind.org 7፡00 a.m. እስከ እኩለ ሌሊት ይኖራል። ቤተሰቦች ወይም ተማሪዎች ድጋፍ ለማግኘት ሲፈልጉ፥ የተጎጂ እርዳታ እና የወሲብ ጥቃት መከላከል ፕሮግራም/Victim Assistance and Sexual Assault Program (VASAP) ማነጋገር ይችላሉ። VASAP መረጃ እና ሪፈራል፣ መሟገት፣ እንዲሁም የከባድ ቀውስ ሁኔታ ድጋፍ ይሰጣል፥ እንዲሁም ለወሲባዊ ጥቃት ሰለባዎች ቀጣይነት ያለው የካውንስሊንግ አገልግሎት ይሰጣል።

*ማጣቀሻዎች፡-*

*የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንቦች*-MCPS Regulations ACF-RA, GKA-RA, JHC-RA, and JHF-RA

*የ MCPSየተማሪ ስነምግባር ደንብ* - Student Code of Conduct

## ■ የተማሪ መዝገቦች

ት/ቤቶች የሁሉንም ተማሪዎች መረጃዎችን/መዝገቦችን/ሪኮርዶችን ይይዛሉ። በተማሪ ፋይል ላይ በ MCPS ቅጾች በቅድሚያ የተጠረቀመ መሠረታዊ ሪኮርድ ይገኛል። ባንዳንድ ሁኔታዎች፣ ሚስጢራዊ ማህደር ሊፈጠር ይችላል። የት/ቤት ሰራተኞች ሚስጢራዊ ማህደር ሲፈጥሩ ወላጆችን/ሞግዚቶችን ማሳወቅ አለባቸው።

ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በሚካሄድ ስብሰባ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው የተከማቸ የተማሪ ሬኮርድ የማየት መብት አላቸው። ሲጠየቅ፣ የት/ቤት ሰራተኛ የተከማቸ የተማሪ ሬኮርድ ለተማሪዎችና ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማብራራት ወይ መተርጎም ይችላል/ትችላለች።

የትምህርት ዓመቱ ከተጀመረ በ 30 ቀናት ውስጥ፣ የ MCPS ቅፅ 281-13 "Annual Notice for Directory Information and Student Privacy" ወይም የ MCPS ቅጽ 281-13ISC "Annual Notice for Directory Information and Student Privacy for Innovative School Year Calendar Schools" ለሁሉም የ MCPS ተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ከ MCPS ይሰጣል። ይህም የመረጃ ማውጫዎችን ይዘረዝራል። የቤት አድራሻዎችና የስልክ ቁጥሮች ሊገለፁ የሚችሉት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ድርጅቶች፤ ለመምህራን፣ እና ለት/ቤት ተማሪዎች፤ ለሚሊታሪ ቅርንጫፍ፤ በት/ቤቱ ወይም በትምህርት ቦርድ ለተቀጠረ ሰው፤ ወይም ለሜሪላንድ የማህበረሰብ/community ኮሌጅ ብቻ ነው። ወላጆች/አሳዳጊዎች የተወሰነ ወይም ጭራሹንም የግል መረጃ ዎችን ለተወሰነ ጊዜ በይፋ እንዳይገለፅ መከልከል ይችላሉ፤ እናም፣ እንደ ማኛውም ሌላ የተማሪ ሬኮርድ፣ መረጃው በሚስጢር ይያዛል።

ተማሪዎች ሲጎለምሱ፣ ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪን መረጃ በሚመለከት ተመሳሳይ መብት አላቸው። ቢሆንም፣ የእድሜ ብቃት ያላቸው በወላጆቻቸው ጥገኝነት የሚኖሩ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ያለ ተማሪ ው/ዋ ፈቃድ የልጃቸውን መረጃ ለማግኘት ይችላሉ።

ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቃት ያለው/ያላት ተማሪ ከተማሪው(ዋ) ጋር የተገናኙ የትምህርት መረጃዎች ትክክል አይደሉም፣ ወይም ያሳስታል፣ ወይም የተማሪ የግል ህይወትን መብት ይጻረራል፣ ተብሎ ከታመነ፣ ወላጅ/ሞግዚት ወይም ብቃት ያለው(ያላት) ተማሪ ፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ቅጽ-MCPS Form 270-8 በመጠቀም የሞን ትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሪኮርዱን እንዲያሻሽል ለመጠየቅ ይቻላል፣ ከህዝብ የሚቀርብ ቅሬታ/ስሞታ።

*ማጣቀሻዎች፡-*
*የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ*-MCPS Regulations JOA-RA *እና* KLA-RA

## ■ መፈተሽ/መፈለግና መያዝ

የMCPS ሠራተኞች በተማሪው ላይ ወይም እቃውን ፍተሻ የሚያካሄዱበት እና ፍተሻ የተደረገበትን ነገር ለመያዝ የሚያስችላቸው ሁኔታዎች በሞን ጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ደንብ "MCPS Regulation JGB-RA" ፍተሻ ማካሄድ እና መያዝ/መንጠቅ /Search and Seizure ላይ ተገልጿል። መደበኛ ትምህርት እንዳይደናቀፍ ፍተሻ በማድረግ ለመውረስ እና ይዘው የተገኙ ተማሪዎችን ምንተፍረት ለመቀነስ የተቻለ ሁሉ ጥረት ይደረጋል።

የፍተሻ እና/ወይም የመውረስ ስልጣን የተሰጣቸው፡- የትምህርት ቤት ኃላፊዎች ዋና ወይም ረዳት ርዕሰ መምህር፣ የ MCPS ስርዓት አቀፍ የደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር (DSSEM) ሠራተኛ አባል እና/ወይም በ MCPS የተቀጠረ(ች) የት/ቤት የደህንነት ሠራተኛ እና ፍተሻ ለማድረግ የሰለጠነ(ች) በትምህርት ቤቱ ስፖንሰር የተደረገ ጉዞ ላይ በጽሑፍ ኃላፊነት የተሰጠው/የተሰጣት ሠራተኛ ይሆናሉ።

መቆለፊያ ሣጥን፣ ወይም እቃ ማስቀመጫ ክፍል፣ ወይም ሌሎች ከት/ቤት የተሰጡ ቁሳቁሶች የተማሪ የግል ንብረት ተደርጎ ስለማይቆጠር እንዲህ ዓይነቶቹ ቁሳቁሶች ላይ ፍተሻ ለማካሄድ ተማሪው/ዋ ያልተ ፈቀደ ነገር መያዙን/መያዟን እርግጠኛ መሆን አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ቢሆንም፤ የተማሪውን በመቆለፊያ ሳጥን ውስጥ ወይም በእቃ ማከማቻ ቦታ ላይ ያለ የተማሪ በጀርባ እቃ መያዣ ቦርሳ ወይም የሴት ተማሪ ቦርሳ (e.g., backpacks or purses) ፍተሻ የሚደረገው ያልተፈቀደ ነገር መያዙን ሲታመንበት እና በማናቸውም እንዲህ ዓይነት ፍተሻ በተማ ሪው/ዋ ላይ ወይም እቃቸው ላይ ፍተሻ በሚካሄድበት ወቅት ተጨማሪ የት/ቤት ሠራተኛ አብሮ መኖር አለበት። የተማሪ ፍተሻ መጨረሻ ላይ፣ የተፈተሸ(ች)ውን ተማሪ ወላጅ/አሳዳጊ ለመገናኘት ተቀባይነት ያለው ሙከራ ይደረጋል ፍተሻ የተደረገበትን ምክንያት እና ስለውጤቱ መረጃ ለመስጠት።

ህጋዊ ፍተሻ ለመፍቀድ የተማሪው/ዋ ተቃውሞ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል።

*ማጣቀሻዎች፡-*
*የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ*-MCPS Regulation JGB-RA
*በሜሪላንድ የትምህርት ኮድ* (Annotated Code of Maryland)፣ *የትምህርት አንቀፅ*፣ §7-308
*ድረ-ገጽ* www.montgomeryschoolsmd.org/departments/security/

## ■ ስርዓት-አቀፍ የደህንነት እና የአደጋ ጊዜ አስተዳደር

አወንታዊ የመማርያ አካባቢ እንዲሰፍን/እንዲኖር ለማድረግ የተማሪዎችና የሰራተኞች ደህንነት ወሳኝ ነው። የዲስትሪክት ስምምነቶችን/ፕሮቶኮሎችን፣ ልምዶችን፣ እና ተዛማጅ መሠረተልማት በጥብቅ አስፈላጊ የሆነውን ለሁሉም ተማሪዎች ሠላማዊ የሆነ የትምህርት አካባቢን መጠበቅን የሞንት ጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ገምግሟል።

ለሁሉም ትምህርት ቤቶች ሰባት ቅድሚያ የሚሰጣቸው መስኮች:-

1. ከመረጃ የመነጨ ኃላፊነት/ተጠያቂነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በጠቅላላ ስለ ት/ቤት ሠላምና ደህንነት እና አዎንታዊ የት/ቤት ባህል የትምህርት ምህዳሩ/ስርዓቱ ተቀዳሚ ትኩረት ይሆናል።
2. የት/ቤት ደህንነት ጥበቃ ሠራተኞች እና የሌሎች ሠራተኞች ውጤታማ ምደባ፣ አጠቃቀም፣ እና ማኔጅመንት።
3. የሰኩሪቲ ካሜራዎች፣ እና አጠቃቀማቸውን ጨምሮ ቴክኖሎጂ መዘርጋት
4. ለብቻቸው የተለዩ ህንፃዎችንና የት/ቤት መገልገያዎችን መጫወቻ ሜዳዎችን መግቢያ ላይ ጥብቅ ማድረግ።
5. በትምህርት ቀናት በሙሉ መልካም የተማሪ ስነምግባርን የመደገፍ ሥርዓትና አፈጻጸሞች፡፡
6. ሥርአት አቀፍ የመከላከል እና ቅድሚያ ጣልቃ ገብ ፕሮግራሞች፡፡
7. ከህግ አስከባሪዎች እና ሌሎችም አጋር ኤጀንሲዎች ጋር በትብብር መስራት፡፡

የት/ቤቶቻችን ደህንነትና ፀጥታ ሁሉንም ሰው የሚመለከት ጉዳይ ነው። MCPS ለት/ቤት ደህንነት፣ ለእቅድ እና ስልጠና ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ቀልጣፋ አቀራረብ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋል። አስቸኳይ ሁኔታ ፈጣን ምላሽ የሚጠይቅ መተንበይ የማይቻል፣ ዕቅድ ያልተደረገ ሁኔታ ነው። የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች የሚባሉት:- የእሳት ቃጠሎ፣ ከአየር ሁኔታ ጋር የተዛመዱ ክስተቶች፣ አደጋዎች፣ በአደገኛ ቁሳቁሶች ምክንያት የሚፈጠሩ ክስተቶች፣ የቦምብ ማስፈራራት ወይም የወንጀል ተግባርን ሊያካትቱ ይችላሉ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰኑም። በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) አሠራር መሠረት፥ MCPS ከአደጋ የማምለጥ፤ ይኼውም መጠለያ፣ ወደቦታ የመመለስ እርምጃ፣ ለከባድ የአየር ሁኔታ፣ ለድንገተኛ ሁኔታዎች ተገቢ ምላሽ ለመስጠት የአሠራር ሂደቶችን አዘጋጅቷል። እነዚህ ሂደቶች የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአስ ቸኳይ ዝግጁነት ዕቅድ አካል ናቸው።

ማንኛውም ድንገተኛ ሁኔታ፣ እሳት፣ ከአየር ሁኔታ ጋር የተዛመደ ክስተት፣ ወይም የወንጀል ተግባር፣ ተማሪዎቻችንን እና ሰራተኞቻችንን ሊያጨናንቅ እንደሚችል MCPS ይረዳል። ስለዚህ MCPS የብሔራዊ ምርጥ ተሞክ ሮዎችን እና የአዕምሮ ጤና ባለሞያዎችን ምክር በመውሰድ ልምምዶችን በማካሄድ ከስቴቱ የተሰጠውን መመሪያ ያከብራል። ተማሪዎች፣ የአስተ ዳደር አባላት፣ እና ወላጆች/ሞግዚቶች የእነዚህ ቅደም ተከተሎች ግንዛቤ እንዲኖራቸው ወሳኝ ነው።

"Lockdown" በ MCPS ተቋም ውስጥ ለአደጋ ጊዜ አንድ ዓይነት ምላሽ ለመስጠት የሚያገለግል ቃል ነው። "Lockdown" መመሪያ የሚሰጠው በህንፃው ውስጥም ሆነ ከቤት ውጭ አደጋ መኖሩን እና ወደ አስቸኳይ የመሸሸግያ ሁኔታ በፍጥነት መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ሠራተ ኞችን ያስጠነቅቃል። ሁሉም ተማሪዎች የጎልማሳ/አዋቂ ሰው ክትትል እንዲደረግላቸው ይጠይቃል። ተማሪዎች እና ሰራተኞች በፍጥነት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ መንቀሳቀስ፣ ዝም ማለት እና የሰራተኞችን መመሪያዎች መከተል አለባቸው። MCPS ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ፣ እና ከብሔራዊ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስቶች ማህበር (NASP) ጋር በመተ ባበር ወሳኝ የህይወት አድን ሁኔታን እና ሊሆኑ ለሚችሉ አማራጮችን ለመረዳት የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ለማስተማር "Lockdown" የሰራተኞች ስልጠና ከአማራጮች ጋር ይሰጣል።

ከስፍራው ማስለቀቅ/ማስወጣት (Evacuate) በት/ቤት ውስጥ የሚደርስን አስቸኳይ ሁኔታ ለመግለፅ ስራ ላይ የሚውል ቃል ነው። የእሳት አደጋ ማስወገጃ ማንቂያ ደወል ወይም በትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች የሚመ ራውን የሕዝብ ማስታወቂያ በመጠቀም ሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች ሕንፃውን ለቀው እንዲወጡ ይደረጋል።

መጠለያ አግኝ (Shelter) በMCPS መገልገያ ወይም ባቅራቢያው ለሚደርስ አስቸኳይ ሁኔታ መኖሩን የሠራተኛ አባላትን ለማስጠንቀቅ ስራ የሚውል ቃል ነው። ሁሉም ተማሪዎች መኖራቸው እንዲረጋገጥና በአዋቂ ቁጥጥር ስር ህንፃ ውስጥ እንዲሆኑ ይጠይቃል። ሶስት ዓይነት የመጠለያ ማስጠን ቀቂያዎች አሉ፡- የህዝብ ደህንነት፣ መጥፎ የአየር ሁኔታ፣ እና የአደገኛ ቁሳቁሶች/ንጥረነገሮች ወደ ዉጭ መለቀቅ።

የ MCPS የድንገተኛ አደጋ ምላሽ ፕሮቶኮሎችን ለመገምገም እና ለማሻሻል MCPS ከ MSDE፣ ከሜሪላንድ የት/ቤት ደህንነት ጥበቃ ማዕከል፣ ከአከባቢ የህግ አስከባሪ አጋር ኤጀንሲዎች እና ከ NASP ጋር በትብብር መስራቱን ይቀጥላል።

ተማሪዎች በአስጊ ሁኔታ የዛቻና ማስፈራራት ባህርይን እንዲገነዘቡ እና የዛቻና ማስፈራራት ባህርይን-ድርጊትን ሪፖርት የማድረግ መመሪያ ይሰጣ ቸዋል፣ እንዲሁም ማናቸውንም በሌላው ሰው ላይ ጉዳት የማድረስ፣ የግን ኙነቶችን ሁኔታ፣ ወይም ማስፈራራትና ዛቻን የሚያደፋፍሩና የሚያባብሱ ሁኔታዎችን ወይም ማንኛውም ግለሰብ በሆነ ሰው ላይ ዒላማ አድርጎ ጥቃት የማድረስና የረብሻ ዝንባሌን ተማሪዎች በፍጥነት ለርእሰመምህር/ለተወካይ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በሜሪላንድ ህግ መሠረት፣ ዛቻ-ማስፈራራት ማለት አካላዊ ጉዳት የማድረስ ዝንባሌ ነው። የማስፈራራት ወይም የዛቻ መገለጫው በባህርይ፣ በቃል፣ በአይን-ግልምጫ፣ በጽሑፍ፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ ወይም በማናቸውም ሌላ ዘይቤ ሊገለጽ የሚችል ሲሆን፣ የተቃጣበ(ባ)ት ሰው በቀጥታም ይሁን በተዘ ዋዋሪ እንዲያውቀው-እንድታውቀው ወይም የተቃጣበ(ባ)ት ሰው ቢያውቅም/ ባያውቅም በሌላ ሦስተኛ ወገን አማካይነት መልእክት ይተላለፋል። ዛቻና ማስፈራራት በቀጥታ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ፡- እመታሃ(ሻ)ለሁ “I am going to beat you up.”) ወይም በተዘዋዋሪ (ለምሣሌ፡- አገኘዋለሁ- አገኛታለሁ “I’m going to get him.”).

ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችን፣ እና ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ስለ ደህንነት እና የደህንነት ስጋቶችን ለማሳወቅ ስም-አልባ በሆነ መንገድ ለማቅረብ በሚደ ረገው ጥረት፣ MCPS በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ውስጥ ከሜሪ ላንድ የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ማዕከል ጋር በመተባበር አደጋን ለመጠቆም እና ሪፖርት ለማድረግ- "Safe Schools Maryland" የተሰኘ አሠራር ይጠቀማል። ይህ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሞግዚቶች፣ እና የማህበ ረሰብ አባላት በሜሪላንድ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ለደህንነት ስጋት የሚሆኑ ነገሮችን በቀላሉ በሚስጥር ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችላቸዉ ይፋ የማይ ደረግ ጥቆማ ማቅረቢያ ነው። የተቀበሉት ምክሮች ለአካባቢያዊ እና ለክልል ትምህርት፣ ለሕዝብ ደህንነት፣ ለጤና ጥበቃ ባለሥልጣናት እና/ወይም ለማህበራዊ አገልግሎቶች ድጋፍ ሠራተኛ ለክትትል በተገቢው መንገድ ይተላለፋሉ።

እንደ ---- የመሳሰሉ ስጋቶችን ለማጋራት ግለሰቦች ይህንን ድረ-ገጽ፣ ስልክ፣ እና መተግበሪያ መሣሪያን መጠቀም ይችላሉ—

- የአእምሮ ጤንነት ችግሮች፣
- ጉልበተኝነት፣
- በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ የሚፈጠር ሁከት፣
- አደንዛዥ ዕፅ ማዘዋወር፣
- በደል፣ እና
- ትንኮሳ።

ያስታውሱ፣ የትምህርት ቤቶቻችን እና የፋሲሊቲዎቻችን ሠላም እና ደህንነት ሁሉንም ሰው የሚመለከት ስለሆነ፣ እንደዚህ አይነት ስጋቶች ወዲያውኑ በሜሪላንድ የስልክ ክፍት መስመር ሃላፊነቱ ለሚመለከተው አዋቂ-ጎልማሳ ሰው ሪፖርት መደረግ አለበት Safe Schools Maryland Hotline ።

ስለ ት/ቤቶች ሠላም የሜሪላንድ ክፍት-ቀጥታ መስመር፡- 833-632-7233 (833-MD-B-SAFE)

በቀን 24 ሰአት በሳምንት ለ7 ቀኖች ሰራተኛ የተመደበባቸው ተጨማሪ አስቸኳይ መስመሮች፡-

የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ (Montgomery County Police) —
አስቸኳይ ሁኔታ ያልሆነ፡- 301-279-8000
የእፅ መጠቆሚያ የአስቸኳይ ጥሪ መስመር፡- 240-773-DRUG (3784)
የወንበዴ/ወሮበላ መጠቆሚያ የአስቸኳይ ጥሪ መስመር፡- 240-773-GANG (4264)
የአደንዛዥ እፆችና የወንበዴ ጥቆማዎች፡- 240-773-TIPS (8477)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤናና ስብአዊ አገልግሎቶች
የመረጃ መስመር (ከሰኞ እስከ አርብ 8:30 a.m.–5:00 p.m.):- 240-777-0311, TTY 240-251-4850

MCPS ስርዓት አቀፍ ደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር መምሪያ 240-740-3066

ድረ-ገጽ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/security/
ማጣቀሻዎች፡-
የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ COA
የ MCPS ደንብ COA-RA
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ "MCPS Regulation EKA-RA"

## ■ ከስቴት ተፈላጊ የሕክምና ጣልቃ ገብነቶች

MCPS የድንገተኛ/አስቸኳይ ሁኔታ ተጠሪን እና የጤና መረጃ መስጠት ወላጆች/አሳዳጊዎች myMCPS Parent Portal ላይ የተማሪ የድን ገተኛ/አስቸኳይ ሁኔታ መረጃ /Student Emergency Information/ ክፍልን ወይም MCPS ቅጽ 565-1፣ የተማሪ የድንገተኛ/አስቸኳይ ሁኔታ መረጃን መሙላት አለባቸው። ስለ አንዳንድ ልዩ የሕክምና ጉዳዮች የተወሰኑ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

### ስለ "Anaphylaxis Awareness" ግንዛቤ

ወላጆች/አሳዳጊዎች የተማሪው(ዋ)ን ልዩ የጤና እንክብካቤ ሁኔታ፣ ወይም "anaphylaxis" ምርመራ፣ መድሃኒቶችን ስለመስጠት እና ተገቢውን የፈቃድ ቅጾችን ሞልቶ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው። እነኚህ የህክምና መድሃኒቶች ለልጅዎ/ለተማሪዎ በአጣዳፊ ወቅት እንዲጠቀምበት-እንድትጠቀምበት በት/ቤቱ የጤና ክፍል ይቀመጣል። የሜሪላንድ ስቴት ሁሉም ትምህርት ቤቶች ሠራተኞቻቸውን የ "anaphylaxis" ምልክቶችን እንዲያውቁ እና አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም የ epinephrine auto-injectors (ለምሳሌ፡- EpiPens) ክምችት እንዲኖራቸው መሰልጠን እንዳለ ባቸው ይደነግጋል። በየት/ቤቱ የተመደቡ ሠራተኞች epinephrine auto-injectors መስጠት እንዲችሉ የሠለጠኑ ናቸው። የወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ ከተሰጣቸው እና "MCPS Form 525-14" ቅጽ ላይ ተሞልቶ ከሆነ ተማሪዎችም epinephrine auto-injectors ለመያዝ ይችላሉ፣የአለርጂ በሽታ ላለበት/ባት ተማሪ የአስቸኳይ ሁኔታ እንክብካቤ Epinephrine Auto Injector የጉዳት ካሳ ስላለመፈለግ/ስላለመጠየቅ የተደረገ ስምምነት መግለጽ "Release and Indemnification Agreement for Epinephrine Auto Injector"

### ስለ ስኳር በሽታ ግንዛቤ "Diabetes Awareness"

ወላጆች/አሳዳጊዎች ተማሪያቸው የስኳር በሽታ ካለበ(ባ)ት ለትምህርት ቤቱ የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው፤ የተማሪው(ዋ) የስኳር በሽታ ህክምና እንክ ብካቤ ጋር የተዛመደ የተሟላ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ የሕክምና መረጃ፣ የጽሑፍ የስኳር ህክምና ጥንቃቄ ዕቅድ (DMMP) ወይም የጤና እንክ ብካቤ ሰጪ የህክምና ትዕዛዝ ቅጽን ጨምሮ ለትምህርት ቤቱ መደበኛ እና የድንገተኛ ጊዜ መድኃኒቶችን እና የመድኃኒት አስተዳደር መሣሪያዎችን ማቅረብ፤ ተገቢውን የፈቃድ ቅጽ መሙላት፣ እና በተማሪው(ዋ) የሕክምና ፍላጎቶች ላይ ማናቸውንም ለውጦች ለት/ቤቱ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።

የስኳር በሽታ ላለባቸው ተማሪዎች የዕለት ተዕለት ኃላፊነት ያላቸው ሠራተኞች የተማሪዎቹን DMMP እና/ወይም የጤና እንክብካቤ ሰጪዎችን የህክምና ትዕዛዞች አፈፃፀም ለመደገፍ ተጨማሪ ሥልጠና ያገኛሉ። የት/ቤት ማህበረሰብ የጤና ነርስ ተማሪው/ዋ ት/ቤት በሚፈቅድላቸው ትምህርታዊ የመስክ ጉዞዎች ላይ በትክክል ለመሳተፍ እንዲችል/እንድትችል፣ በአግባቡ የስኳር በሽታ ክወናን/ቁጥጥር እውቀት ያለው "diabetes management activities" ተገቢውን የት/ቤት ሥራ ባልደረባ ለመወከል ከት/ቤቱና ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር በመተባበር ትሠራለች/ይሠራል።

### ስለ Naloxone እና Opioid አደንዛዥ እፆች ግንዛቤ

"Start Talking Maryland Act of 2017" የሜሪላንድ ዲስትሪክቶች ስለ ሄሮይን (heroin) እና ኦፒዮይድ (opioid) ሱስ እና በመከ ላከል ላይ ያተኮረ ተጨማሪ ትምህርት እና እውቀት እንዲሰጡ ይጠይቃል። የት/ቤት ነርስ፣ የት/ቤት የጤና አገልግሎት ባለሞያዎች፣ እና ሌሎችም በ MCPS የሚታወቁ ሠራተኞች ከመጠን በላይ የተወሰዱ መድኃኒ ቶችን ማርከሻ ለመስጠትና ጉዳቱን ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸዉ ሲሆን፣ Naloxone, or other overdose-reversing medication፣ ለተማሪዎች በድንገተኛ ሁኔታ ጊዜ የሚያገለግሉ መድሃኒቶች በት/ቤት ይቀመጣሉ።

ማጣቀሻዎች፡-
የቦርድ ፖሊሲ IGN፥ የ MCPS Regulations JPC-RA፥ እና JPD-RB

## ■ መጓጓዣ/ትራንስፖርት

MCPS ከተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች፣ እና የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት ሠራተኞች ጋር በመተባበር ወደ ትምህርት ቤት እና ከት/ቤት ወደ ቤት በሁሉም አይነት መጓጓዣዎች ሠላም እና ደህንነታቸው ተጠብቆ መጓጓዝ እንዲችሉ ትብብር ማድረግን ያበረታታል።

የትምህርት ቤት አውቶቡስ ወይም የተማሪ አክቲቪቲ አውቶቡስ የተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ ሲስተም እንዲያስር/እንድታስር ሲያስፈልግ (ማለትም፦ በትክሻ የሚጠልቁ ቀበቶዎች)፣ ሁሉም ተሳፋሪዎች ይህንኑ በመከተል ሠላማዊ/ጤነኛ ጉዞ ማድረግ አለባቸው። ለሁሉም ተሳፋሪዎች እንደየእድሜአቸው ሁኔታ፣ በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ በአግባቡ እንዲጠቀም/እንድትጠቀም መመሪያ ይሰጣል። በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ የማይጠቀሙ ወይም ያለአግባቡ የሚጠቀሙ ተማሪዎች የዲስፕሊን ቅጣት ይጠብቃቸዋል። የአካል ስንክልና ያለበ(ባ)ት ተማሪ በተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ ለመጠቀም ካልቻለ/ች ወይም በአግባብ ካልተጠቀመ(ች)፣ የአውቶቡስ አሽከርካሪው(ዋ) ለርእሰመምህር ያሳውቃል/ታሳውቃለች። ርእሰመምህሩ(ሯ) ስለ ተሳፋሪ መቀመጫ ላይ የሚገታ/የሚይዝ ቀበቶ አጠቃቀም የ IEP ማሻሻያ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ለመወሰን የ IEP ስብሰባ ማድረግ ያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል/ትወስናለች።

የተማሪዎችን ደህንነት ለመጨመር የ MCPS አውቶቡሶች ካሜራዎች ተገጥሞላቸዋል። ካሜራዎቹ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚታዩ እንቅስቃሴዎችን እና የንግግር ተግባሮችን ሪኮርድ ያደርጋሉ።

የስነምግባር እና የደህንነት ህጎችን የሚጥሱ ተማሪዎች በ "MCPS Regulation EEA-RA" መመሪያና ድንጋጌ መሠረት በአውቶቡስ የመጓጓዝ ጥቅም በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ሊታገድባቸው ይችላል ስለ ተማሪ መጓጓዣ ።

## ■ መልካም ጤንነት

ተማሪዎች ስለ ግል ጤንነታቸው ሃላፊነት እንዲወስዱ፣ እና ጤናማ የአመጋገብ ልምድ፣ በየቀኑ የአካል እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ። የቦርድ ፖሊሲ- Board Policy JPG ደህና መሆን/ጤንነት የአካል እና የአመጋገብ ጤንነት በት/ቤት የልጆች ጤነኛ አመጋገብ እና የአካል እንቅስቃሴዎችን የማዘውተር ባህል እንዲዳብር እና ጤንነታቸው እየተጠበቀ ለመማር እንዲችሉ ለመደገፍ የቦርዱን ቁርጠኝነት ማረጋገጫ ነው።

MCPS Regulation JPG-RA፣ ጤነኛ ቁመና/ደህንነት/መልካም ጤንነት የአካል እና የአመጋገብ ጤንነትበ/ት ቤቶች አካባቢ የአካል ብቃት እና የአመጋገብ ጤንነትን፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነት እና ባህርይን እና እንቅስቃሴዎችን ለጤናማ የአኗኗር ዘይቤ የሚጠቅሙ መልካም ተምሳሌቶችን ለማስተማር ቅደም ተከተልን ለማስፈን ይረዳል። በትምህርት ቀናት መጀመሪያ፣ በመካከል እና ከትምህርት በኋላም የአካል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ በጣም ይበረታታል።

የ MCPS ተነሳሽነት የሆነው የጤንነት ቁመና 365 (Be Well 365)፣ የተማሪዎቻችንን አካላዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነ ልቦናዊ ደህንነት ይመለከታል። ተማሪዎች በአካላቸው፣ በአዕምሮአቸው እና በመንፈሳቸው ጤናማ ሲሆኑ በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ያስመዘግባሉ።

“የጤንነት ቁመና 365 (Be Well 365) ተማሪዎች በት/ቤት እና በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ መልካም አባላት እንዲሆኑ አስፈላጊ ክህሎቶች እንዳላቸው ለማረጋገጥ ይሠራል። ስሜታቸውን እንዲቆጣጠሩ፣ የአካዳሚክ እና ማህበራዊ ጥንካሬን ለመገንባት፣ ለራሳቸው ወይም ለጓደኛ ድጋፍ መስጠት እና መድረስ፣ ግጭትን በሰላም መፍታት፣ እና ሌሎች አዎንታዊ ውሳኔዎችን ለማረጋገጥ ይሠራል።

### ተማሪ Sunscreen አጠቃቀም

አንድ ተማሪ ከጤና እንክብካቤ ባለሙያ የጽሑፍ ፈቃድ ሳይዝ-ሳትይዝ በትምህርት ቤቱ ንብረት ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር በተደረገ እንቅስቃሴ ላይ "sunscreen" መያዝ እና መጠቀም ይችላል/ትችላለች። ለፀሐይ የመጋለጥን አደጋ ለመከላከል ተማሪዎች "sunscreen" እንዲጠቀሙ ይመከራል።

### ራስን ስለ መግደል-ግንዛቤ

ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል) ራስን የመግደል ግንዛቤን ለማስተዋወቅ እና የአዕምሮ ጤንነትን ስጋቶች ለመቅረፍ ራስን የመግደል ምልክቶችን የመለየት እና የመከላከል ፕሮግራም ላይ ይሳተፋሉ። ዋናው መልእክት ሰዎች ስለ ጓደኞቸውም ሆነ ስለራሳቸው ስጋት ካደረባቸው እርምጃ (to ACT) እንዲወስዱ ነው:-

» ጓደኛህ/ሽ እርዳታ ያስፈልገው/ያስፈልጋት እንደሆን ግንዛቤ መስጠት ያስፈልጋል
» ስለጓደኛህ(ሽ) ጥንቃቄ/እንክብካቤ አድርግ(ጊ)
» ለሚታመን አዋቂ/ጎልማሳ ሰው ተናገር(ሪ)

ማንኛውም ተማሪ፣ ወላጅ/ሞግዚት፣ ወይም የሥራ ባልደረባ ጭንቀት ስለሚታይበ(ባ)ት ተማሪ ካወቀ(ች) ወይም እርዳታ የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ከሆነ ACT ማድረግ/እርምጃ መውሰድ እና ለሚታመን አዋቂ/ጎልማሳ ሰው ወይም ለአእምሮ ጤና ባለሙያ መንገር ያስፈልጋል።

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት ሰባት ቀናት ድጋፍ እና እርዳታ ይገኛል።

**የሞንጎመሪ ካውንቲ የቀውስ ሁኔታ ማእከል (Montgomery County Crisis Center)**

የቀውስ ሁኔታ ማእከል . . . . . . . . . . . . . . . 240-777-4000
General Hotline . . . . . . . . . . . . 301-738-CALL (2255)
(ከእሁድ እስከ ሐሙስ 12:00–9:00 p.m.
የቴክስት አገልግሎት ይኖራል)
አገር አቀፍ ራስ መግደልን መከላከል/
National Suicide. . . . . . . . . . . 1-800-273-TALK (8255)
የመከላከል ዘወትር ክፍት መስመር በየቀኑ
24 ሰዓት ይገኛል/ክፍት ነው/
Prevention Lifeline (Available 24 hours a day)
ኦንላይን መነጋገሪያ - Online chat at
www.contact-usa.org/chat
Text CONNECT to 741741 በዩናይትድ ስቴት ውስጥ ከየትም ቦታ ሆነው ቴክስት መላክ ይችላሉ

በተጨማሪም ት/ቤት-ተኮር የባህሪ ስጋት ግምገማ ቡድኖች (BTATs) ለሁሉም የትምህርት ቤት ደረጃዎች (ማለትም፥ የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች) ለተማሪዎች እና ለሠራተኞች አስጊ ባህሪን ሪፖርት ስለማድረግ ዕውቅና ይሰጣሉ። በሌሎች ላይ ጉዳት ለማድረስ በሚያስፈራራ/በሚዝት-በምታስፈራራ/በምትዝት ተማሪ ላይ BTAT ምርመራ በሚያደርግበት ወቅት፣ ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገው BTAT ራስን ስለመጉዳት እና ራስን ስለማጥፋት ሃሳብ ጭምር መመርመር ይኖርበታል። አስጊ ሁኔታን በመመርመር ሒደት በ MCPS Regulation COA-RA ድንጋጌ መሠረት፣ አስጊ ባህርይን ስለመመርመር - Behavior Threat Assessment ፣ BTAT ማናቸውንም ራስን የመጉዳት ወይም ራስን የማጥፋት ዝንባሌን እና ተገቢነት ካለው፣ ተማሪው(ዋ)ን ወደ "Montgomery County Crisis Center" እና/ወይም ለየራሳቸው አገልግሎት ሰጪ ማስተላለፍ ይኖርበታል።

## ■ የህክምና አሰጣጥ

MCPS እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (DHHS) በትምህርት ቀን ለተማሪዎች የህክምና መድኃኒት መስጠትን አያደፋፍሩም/አያበረታቱም። ከት/ቤት በፊት እና በኋላ ሊሰጡ የሚችሉ ማንኛውም አስፈላጊ መድሃኒት እንደዛው መታዘዝ ይኖርባቸዋል። ከመድኃኒት መደርደሪያ የሚገዙ መድሃኒቶችና homeopathic እንዲሁም ከዕፅዋት የሚቀመሙ መድኃኒቶች በሐኪም በሚታዘዙ ሕክምናዎች መሠረት ይሰጣሉ። በእርግጠኝነት አስፈላጊ ሲሆን የት/ቤት ሰራተኞች ከክፍል ውጪ በሚከናወኑ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች እና የመስክ ጉዞዎች እየተሳተፉ ለሚገኙ ተማሪዎች በ MCPS Forms 525-13 ቅደምተከተል መሠረት የህክምና መድኃኒት ይሰጣሉበኃኪም የታዘዘ መድኃኒት ለመስጠት የሚሰጥ ፈቃድ/Authorization to Administer Prescribed Medicationወይም 525-14በተማሪ ላይ Anaphylaxis ሲያጋጥም አስቸኳይ ጥንቃቄ/እንክብካቤ ስለማድረግ - Emergency Care for the Management of a Student with a Diagnosis of Anaphylaxis፡፡

በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት መመሪያዎች መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ መድሐኒቶችን ትንፋሽ ሲያጥር የሚወሰድ እና epinephrine ራሳቸው የሚወጉት-መርፌዎች በህክምና በለሙያ ፈቃድ ሊሰጥ እና በ DHHS የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጤና ነርስ መጽደቅ አለበት።

*መጣቀሻ: -*
የ MCPS ደንብ JPC-RA

## ■ የተማሪ የስነ-ምግባር ደንብ

ሁሉም ተማሪዎች የሚማሩበት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ የማግኘት መብት አላቸው። አወንታዊ የት/ቤት ድባብን የሚያበረታቱ ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች በመማር ላይ ለማሳተፍ እና ትምህርት የሚያታግላቸው ተጋላጭ ተማሪዎችን ለመደገፍ በተገቢው ሁኔታ ጣልቃ ይገባሉ። ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ጣልቃገብነት፣ ደህንነት እና የጤንነት ቁመና እቅድ፣ የባህሪ ጣልቃገብነት ፍልስፍና እና የተማሪ ባህሪያትን እና የመጥፎ ባህሪ መዘዝን ይገልጻል። የዚህ መመሪያ ትግበራ ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ቤተሰቦች በሥነ ምግባር ደንቦች እና በመተግበሪያ ደንቦች ላይ ወጥነት ያለው የሚጠበቅ ሥነምግባር እና የተማሪን ባህሪ መዘዞችን ይዘረ ዝራል ከተማሪ ስነምግባር ጋር የማይጣጣም የ MCPS የስነምግባር ደንብ።

*ማጣቀሻዎች-*
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulations JGA-RA, JGA-RB, እና JGA-RC.

## ■ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሠራተኛ ሥነምግባር ደንብ/ Employee Code of Conduct

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የቦርዱ ዋና እሴቶች የሆኑትን ትምህርት፣ መልካም ግንኙነት፣ አክብሮት፣ ልቀት፣ እና ፍትሃ ዊነት ድርጅታዊ ባህል ለማስፋት ቁርጠኝነት አለው። በ MCPSየሠራተኛ የስነምግባር መመሪያ ኮድ/Employee Code of Conduct ዉስጥ እንደተ ገለጸው ለሁሉም ተማሪዎች የሚመች ሠላማዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትም ህርት አካባቢ ለመፍጠር እና ለመጠበቅ ሁሉም ሠራተኞች የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ሁሉም ሰራተኞች ከሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በሁሉም ደረጃ ከሚገኙ ባልደረባዎች፣ እና ማህበ ረሰብ ጋር እጅጉን ከፍ ባለ ሃቀኛነትና ባለሞያዊነት/professionalism እንዲገናኙ ይጠበቅባቸዋል።

### ማህበራዊ ሚዲያ:- ለሠራተኞች እጅግ ጠቃሚ ምክሮች/ ልምምዶች

በተጨማሪም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለ ማህበራዊ መገናኛ አውታር/ሚዲያ አጠቃቀም ለሠራተኞች መመሪያ ይሰጣል፡፡ መመሪያዎቹ በዚህ አውታረመረብ ላይ ይገኛሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/social-media-best-practices/

*ማጣቀሻዎች: -*
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሠራተኛ ሥነምግባር ደንብ/ Employee Code of Conduct
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ማህበራዊ መገናኛ /ሚድያ ለሠራተኞች እጅግ ጠቃሚ ልምምዶች/ተሞክሮዎች
ለ MCPS ሠራተኞች ምርጥ የሆኑ የኢ-ሜይል እና የዲጂታል መገናኛ ተሞክሮዎች
በቦርድ፣ MCPS፣ እና በ MCPS ሠራተኛ ማህበራት መካከል የሰፈነ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመከባበር ባህል/Culture of R.E.S.P.E.C.T

## ■ ይግባኞች-የቅሬታ ቅደም ተከተል— ተገቢው ሂደት

ይህ ክፍል የተተለመው ቅሬታ፣ የአድልዎ አቤቱታ፣ መታገድ ወይም ስንብት የማያጠቃልል የዲሲፕሊን እርምጃ፣ ወይም የስክልና ትምህርት ያላቸው ግለሰቦች አዋጅን የመሳሰለ በሌላ ህግ ወይም ደንብ ተለዋጭ የአለ ማግባባት እርቅ በተለይ የቀረበባቸው ሌሎች ጉዳዮች ውስጥ ለሚገኝ ለያን ዳንዱ ተማሪ ስለ ርትአዊ አስተዳደር መረጃ ለማቅረብ ነው። እንዲህ ዓይነቱን አያያዝ/አፈጻጸም ለማረጋገጥ የት/ቤት ሕግ ከፌደራል እና ከስቴት ሕጎች ጋር፣ እንዲሁም ከቦርድ መርኖ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

### በት/ቤት ደረጃ ውሳኔ

A. ተማሪው/ዋ ለ --- መብት አለው/አላት

1. ይፋ ያልሆነ መፍትሔ/ውሳኔ ለማግኘት ከርእሰ መምህር ወይም ሌላ ተወካይ ጋር መገናኘት። ርእሰ መምህር ወይም ተወካዩ ይፋ ባልሆኑ ዘዴዎች ጉዳዩን ለመፍታት ይሞክራል/ትሞክራለች፤ ወይም
2. ቅሬታ ወይም ስጋት የሆነ ነገር ይፋ ባልሆነ ስልት ችግሩ ካልተፈታ ይፋዊ በሆነ መንገድ መፍትሔ ለማግኘት ለርእሰ መምህር/ተወካይ በጽሑፍ ማቅረብ/መጠየቅ ይቻላል። (MCPS Form 270-8 ከህዝብ የሚቀርብ ቅሬታ/ስሞታ)።

ተማሪው/ዋ A.1 ከመረጠ/ች፣ ነገር ግን በማግባባት ሂደት ወይም በቀረበው መፍትሄ ካልተደሰተ/ች፣ ወይም አቤቱታ ከቀረበበት እለት ጀምሮ 15 የትምህርት ቀናት ምንም ውሳኔ ሳይሰጥ ከታለፈ፣ ርእሰ መምህሩ/ሯ አቤቱታውን በአግባቡ እንዲመለከተው/ እንድትመለከተው ተማሪው/ዋ በፅሁፍ ለማስመዝገብ ይችላል/ ትችላለች።

B. ርእሰ መምህሩ/ሯ የተማሪው(ዋ)ን አቤቱታ በይፋ በሚመለከት/ በምትመለከት ወቅት፣ ተማሪው/ዋ አቤቱታውን የሚደግፉ ምስክሮችና ማስረጃዎችን የማቅረብ መብት አለው/አላት። ቅሬታ በጽሑፍ በቀረበ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ርእሰ መምህሩ/ሯ በቀረበው ጉዳይ ላይ ቅሬታ አቅራቢው/ዋ ጋር ውይይት ለማድረግ ቀጠሮ (ቀን እና ሰዓት) ለመያዝ ያነጋግራል። የፅሁፍ አቤቱታ ከተቀበለ(ች)በት፣ ወይም ከተቀጠረው የስብሰባ ቀን፣ በ10 የሥራ ቀኖች ውስጥ፣ ርእሰ መምህሩ/ሯ የጽሁፍ ውሳኔ በመስጠት ቅጂውን ለባለጉዳዩ /ለባለጉዳይዋ ያስተላልፋል/ታሰላልፋለች። አቤቱታው ውስብስብ ከሆነ ወይም በ10 ቀናት ውስጥ በአግባቡ ሊፈታ ካልተቻለ ርእሰ መምህሩ/ሯ የጊዜ ገደቡን በተጨማሪ 10 የሥራ ቀናት ለማራዘም ይችላል/ትችላለች።

### የርእሰ መምህሩ/ሯ ውሳኔ ይግባኝ

A. የይግባኝ አቀራረብ

ተማሪ በተሰጠው ውሳኔ ካልረካ(ች)፣ ውሳኔውን ለዲስትሪክቱ ኦፕሬሽን ኃላፊ ወይም ለተወካዩ በጽሁፍ ይግባኝ ለማለት ይችላል/ትችላለች፥ ርእሰመምህሩ በጽሑፍ ውሳኔ ከሰጠ15 የትምህርት ቀናት ውስጥ ወይም ውሳኔ መሰጠት ከነበረበት ቀን፣ የትኛውም ቀዳሚ ቢሆን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል/ትችላለጭ ይግባኙ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡-

1. የአቤቱታውና የርእሰ መምህሩ/ሯ ውሳኔ ድህረ እይታ እንዲደረግባቸው ጥያቄ
2. ሁሉም ተፈላጊ ሃቀኛ መረጃዎች
3. የሚጠየቀው መፍትሔ/ፍትሕ

B. የይግባኝ ድህረ እይታ

1. የዲስትሪክቱ ኦፕሬሽን ዋና ኃላፊ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢን ተንደንት ተወካይ ሲሆን ጉዳዩን እና ተዛማጅ መረጃዎችን ይመረምራል/ትመረምራለች።
2. ይግባኙ በደረሰ 15 የትምህርት ቀናት ውስጥ፣ የዲስትሪክቱ ኦፕሬሽን ኃላፊ ወይም ተወካይ ተጨማሪ ምርመራ ካላስፈለገ በስተቀር ውሳኔ መስጠት እና ለተማሪው(ዋ) እና ለርእሰመምህር በጽሁፍ ያሳውቃል/ታሳውቃለች።

### የዲስትሪክት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ውሳኔ ይግባኝ

ተማሪው(ዋ) በፋይናንስ እና ኦፕሬሽንስ ኃላፊ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማለት መብት አለው-አላት። የዲስትሪክቱ ኦፕሬሽን ኃላፊ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በይነመረብ (boe@mcpsmd.org ወይም በፋክስ ቁጥር 301-279-3860) ውሳኔው ይግባኝ ሊባል ይችላል።

*ማጣቀሻዎች:-*
የቦርድ ፖሊሲዎች-Board Policies BLB እና BLC, እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation KLA-RA
የ "MCPS Pupil Personnel" ሠራተኞች እና የተሳታፊዎች አገልግሎት:- 301-315-7335

# የተመረጡ አባሪዎች - APPENDIX—SELECTED የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደምቦች-MCPS REGULATIONS

**ድረ-ገጽ** www.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/

**የMCPS ደንብ ABC-RA፣ የወላጅና የቤተሰብ ተሳትፎ**

ይህ ደንብ ጠንካራ በቤት እና ት/ቤት መካከል አጋርነት/ግንኙነትን ለማዳበር፣ በአካባቢ ት/ቤቶች የወላጅ/አሳዳጊ እና የቤተሰብ ተሳትፎ በየአካባቢው ት/ቤቶች የማህበረሰብ ብዙሃነትን የሚያንፀባርቅ ስኬታማ የሆነና ሁለገብ የወላጅ/አሳዳጊ እና ቤተሰብ ልምምዶችን እና ድጋፍ የማድረግን ጥረት ለማረጋገጥ የሚያስችል መሠረት ይሰጣል።

**MCPS Regulation ABA-RC፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም አጠገብ ተቋራጮች/Vendors**

ይህ መመሪያ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ህንፃዎች ላይ በትምህርት ቀን ቢዝነስ ለመስራት የሚፈልጉ ተቋራጮች ከርእሰመምህር ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል፣ እና ወቅታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ኮድ እና በማናቸውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ህዝባዊ መንገድ ወይም ከመንገድ ክልል 500 ጫማ እርቀት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የፈቃድ መስጫ አገልግሎት ዲፓርትመንት ዳይሬክተር እና የትምህርት ቤት ርእሰመምህር/ት ለልዩ ሁነት ካልተፈቀደ በስተቀር ተቋራጮች በሞንትጎመሪ ካውንቲ መመሪያዎች መሠረት ፈቃድ ሊኖራቸው እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል። ከትምህርት ቤት አውቶቡስ ማቆሚያ 100 ጫማ ርቀት ያነሰ ለአውቶቡስ መዳረሻ ከተያዘው የጊዜ ሠሌዳ 10 ደቂቃ እና አጠገብ በሚገኝ የግል ንብረት አንዳንድ የተቋራጭ እንቅስቃሴዎችን የሞንትጎመሪ ካውንቲ  በጥብቅ ይገድባል።

**የ MCPS ደንብ ACA-RA፣ ሰብአዊ ግንኙነቶች**

ይህ ደንብ የሰብአዊ ግንኙነቶችን ተሞክሮዎችና ባህላዊ ብቃት በMCPS ለሚያጠናክሩ ሰብአዊ ግንኙነት ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች፣ እና እንቅስቃሴዎች ምስረታ፣ መተግበር፣ እና ቀጣይነት መዋቅር/ቅርጽ/ማዕቀፍ ይሰጣል።

**የMCPS ደንብ CNA-RA፣ የመረጃ ቁሳቁሶችና ማስታወቂያዎችን ለእይታ ማቅረብና ስርጭት**

ይህ ደንብ ስለ ቁሳቁሶች/መገልገያዎች ማስታወቂያ እና/ወይም መግለጫዎች ፈቃድ እና ስርጭት ወይም የምርቶች አገልግሎትና ሽያጭን በተመለከተ መመርያ ይሰጣል።

**የMCPS ደንብ CNA-RB፣ ማስታወቂያ**

ይህ ደንብ በሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) በሙሉ ስለስፖንሰሮች ማስታወቂያና የእውቅና/ፈቃድ መስፈርቶችን ይገልጻል። ደንቡ ማስታወቂያዎች ዬት እንደሚቀመጡና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ ይገልፃል፣ ስለ ማስታወቂያዎች ይዘት መመዘኛ/መስፈርት ያስቀምጣል፣ የማስታወቂያ ውል ስለሚገባበት ሁኔታ መመሪያ ይሰጣል።

**MCPS Regulation COA-RA, Behavioral Threat Assessment/አስጊ ባሕርይን መፈተሽ-መመርመር/ማጤን**

ይህ መመሪያ ከተማሪዎች፣ ከሠራተኞች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ኮንትራክተሮች፣ እና ግንኙነት የሌላቸው/የማይመለከታቸው ግለሰቦች በትምህርት ቤት ንብረት ክልል ውስጥ ለትምህርት ቤት ሠራተኞች ወይም ለተማሪዎች ደህንነት  አስጊ የሆነ ባህርይ ሲስተዋል MCPS ክትትል/ምርመራ ለማድረግ ጣልቃ የሚገባበትን አሠራር-አፈጻጸም መመሪያ ይደነግጋል።

**MCPS Regulation COB-RA, Incident Reporting/የተከሰተ ነገርን ሪፖርት ስለማድረግ**

ደንቡ በት/ቤት ንብረት ላይ ወይም ከት/ቤት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ከባድ ሁኔታ ሲያጋጥም መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ቅደም ተከተል ያስቀምጣል።

**MCPS ደንብ COC-RA፣ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ንብረት ላይ ጥሶ መግባት ወይም ሆን ብሎ የሚደረግ ረብሻ**

ይህ ደንብ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ንብረትን ጥሰዉ በሚገቡ ሰዎች ላይ የት/ቤት ሰራተኞች መውሰድ የሚገባቸውን ርምጃ ስልጣን ይገልጻል፤ ህጉንም ለማስከበር ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል። ከት/ቤት ለጊዜው የታገዱ ተማሪዎች ከርእሰ መምህር/ወይም ከተወካዩ ፈቃድ ካልተሰጣቸው በስተቀር ወደ ት/ቤት ግቢ እንዲገቡ አይፈቀድም።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ COE-RA፣ የጦር መሳሪያዎች**

ይህ ደንብ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS ) ንብረት ውስጥ አደገኛ/ወይም ገዳይ ተብለው የሚገመቱ መሳርያዎችን መያዝ የሚከለክልና ህጉ ከተጣሰ መከተል የሚባቸውን ቅደም ተከተሎች ይገልጻል። የጦር መሳሪያዎቹ "... የአካል ጉዳት የሚያስከትሉ መሳርያዎች ተብለው ተገልፀዋል። ይህም የሚተኮሱ መሳርያዎች፣ ጩቤዎች፣ እና ማንኛውም እንደ ጦር መሳርያ የሚያገለግልን ያጠቃልላል።"

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች እፆች በ MCPS ንብረት ላይ**

ይህ ደንብ በሀኪም ትእዛዝ ካልተፈቀደ በስተቀር በት/ቤት ግቢ ውስጥ ማንኛውም ግለሰብ የአልኮል መጠጦች ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች መብላት፣ መያዝ፣ ወይም ማሰራጨት ህገ ወጥ የሚያደርገውን የስቴት ህግ ያስቀምጣል እናም እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የት/ቤት አስተዳዳሪዎች ምን አይነት ቅደም ተከተሎችና መቀጮዎች ስራ ላይ እንደሚያውሉ ያስቀምጣል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ COG-RA, የግል ተንቀሳቃሽ መገልገያዎች (Personal Mobile Devices)**

ይህ ደንብ ተማሪዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤት ውስጥ ወይም MCPS በሚያካሄዳቸው እንቅስቃሴዎች በሚሳተፉበት ወቅት የግል ሞባይል መገልገያዎችን የአጠቃቀም ሥርዓት ይደነግጋል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ ECC-RA፣ የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች ንብረት መጥፋት ወይም መበላሸት/መጎዳት**

ደንቡ፣ በአደጋና በተንኮል በሁለቱም ለደረሰ ጉዳት፣ የተሰረቀ ንብረት፣ በእሳት የጠፋ ወይም የተበላሸን ጨምሮ የጠፋ ንብረት መለየትና ማመልከት፤ የተሰረቁ ወይም የወደሙ ነገሮችን ከት/ቤት ንብረት ዝርዝር መሰረዝ፤ እናም ለጠፋ ንብረት መተኪያ ማግኘት ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS ) ደንብ ECG-RA፣ የተማሪ መኪና መንጃና ማቆሚያ መገልገያዎች፡**

ይህ ደንብ ርእሰ መምህራን በየአመቱ ያሉትን መገልገያዎችና የተማሪዎችን የማቆሚያ ፍላጎቶች እንዲገመግሙ ያለባቸው ን ሃላፊነት ያስቀምጣል እንዲሁም ለተማሪዎች የማቆሚያ መገልገያዎች የመመደቢያ መስፈርቶችን ያስቀምጣል። የአካባቢ ት/ቤት ማህበረሰብ የመኪና ማቆሚያ ስርአትን መተላለፍ በተመለከተ ተገቢ የዲሲፕሊን እርምጃ የመውሰድ/የመወስን ስልጣን ተሰጥቷቸዋል። በት/ቤት ግቢ ተሽከርካሪዎችን መንዳትና ማቆምን በሚመለከት ተማሪዎች ለሁሉም የአካባቢ ት/ቤት ህጎችና ደንቦች ተጠያቂናቸው።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS )ደንብ ECI-RA፣ የዩናይትድ ስቴትስና የሜሪላንድ ሰንደቅ አላማዎችን በሚታይበት ቦታ ማድረግ።**

ደንቡ የሰንደቅ አላማዎች ማሳያ ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል የመክፈቻ/መስቀያ ተግባሮች አፈቃቀድ እና ተማሪዎች በነዚህ ተግባሮች እንዲሳተፉ ማበረታታትን ይደነግጋል። ደንቡ ያለመሳተፍ ቅጣቶችን ይከለክላል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ EEA-RA፣ የተማሪ ትራንስፖርት/መጓጓዣ**

ይህ ደንብ ለያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የእግር ጉዞ ርቀት መጠን ያስቀምጣል እናም ተማሪዎችን በማጓጓዝ፣ ተገቢ ሪፖርቶችን በመያዝ፣ እና ተገቢ የደህንነት ጥንቃቄዎች መወሰዳቸውን በማረጋገጥ ርእሰ መምህሩ/ሯ መከተል ያለበትን/ያለባትን መርሆች ይዘረዝራል። ያውቶቡስ አሽከራካሪ የዲሲፕሊን ችግሮችን ለማመልከት መከተል ያለበትን/ያለባትን ቅደም ተከተል ያስቀምጣል ርእሰ መምህሩ(ሯ)ም የተማሪ ዲሲፕሊን በሚገባ የመከታተል ሃላፊነቱ(ቷ)ን ይገልፃል። የልዩ ትምህርት ተማሪዎች እና ስለ አካለስንኩል ተማሪዎች ትራንስፖርትም ተመልክቷል።

**የ MCPS ደንብ EGF-RB የቪዲዮ ሪኮርዶችን ስለማቆየት እና ይፋ ማድረግ**

ይህ ደንብ በኮሪደሮች፣ በካፍቴሪያዎች፣ በጂምናዚየሞች፣ በአዳራሾች እና በውጪ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እንዲሁም በ MCPS ትምህርት ቤት አውቶቡሶች ከውስጥ እና ከውጭ የሚገኙ የ MCS የደህንነት ካሜራዎች የቪዲዮ ቀረጻዎችን ለማቆየት እና ይፋ የማድረግ አሰራር ሂደቶችን ይገልጻል። የመማሪያ ክፍሎች እንደ የሕዝብ ቦታዎች አይቆጠሩም፣ እንደዚሁም MCPS በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በቪዲዮ ካሜራ ክትትል አይደረግም።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ EKA-RA፣ ለአስቸኳይ ሁኔታና ለአደጋ ጊዜ ቅድመ-ዝግጅት**

ይህ ደንብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ቦታዎች ላይ ለሚገኙ ሰዎች ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በት/ቤት የሚከሰቱ ቀውሶችን ለመከላከል የሚያስችሉ ሁለገብ እቅዶችን አሠራር ቅደምተከተል ማጎልበትና አጠባበቅ ሥርዓት ይደነግጋል።

**MCPS Regulation FAA-RA, Educational Facilities Planning/የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ**

ይህ በቅርቡ ክለሳ የተደረገበት ደንብ የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy FAA ሦስት ቁልፍ ክፍሎች የሚተገበሩበትን ሂደት ይገልጻል፡- 1) የተማሪ ምዝገባ ግምትን እና ቁስ-አካላዊ የትምህርት ፋሲሊቲዎች እና የህንፃ ሲስተሞችን በቀጣይነት በዝርዝር መገምገም፣ 2) ስለፋሲሊቲ ውሳኔ አስጣጥ ላይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና አስተዋጽ፣ እና 3) ምላሽ አማራጮችን ጠቋሚ እና ወደ ፍትኃዊ ሃላፊነት የተሞላበት የገንዘብ እና ትርጉም ያለው ትምህርት ውሳኔዎች፣ የአካባቢ፣ ስቴት፣ እና ፌደራል መስፈርቶች፣ የቦርድ ፖሊሲ/Board Policy ACA ሚዛናዊ አንድምታ፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ፍትሐዊ፣ እና ባህላዊ ብቃትን ሁሉ ወደሚያገናዝብ ውሳኔ የሚያመራ የውሳኔ አሰጣጥ ማዕቀፍ።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ IGO-RA ተማሪዎችን የሚመለከት የአልኮል መጠጥ፣ትምባሆ፣ እና ሌሎች የእፅ መዳኒቶች ክስተቶች መመሪያ**

ይህ ደንብ አልኮል፣ ትምባሆ፣ ሌሎች እፆችን በሚመለከት ከተማሪዎችና ወላጆች ጋር ስለሚካሄድ ግንኙነት ቅደም ተከተል ያስቀምጣል፤ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች መለየት፤ ተማሪዎችን የሚያካትቱ ትግባሬዎች አመዘጋገብ፤ እና የሚጠረጠሩ ቁሶች አያያዝ።

የMCPS Regulation IGT-RA፣ የኮምፒውተር ስርአቶች፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃዎች፣ እና የአውታረ መረብ ጥበቃ ተጠቃሚ ሀላፊነቶች

ይህ ደንብ ስለ ኮምፒውተር አውታረ መረቦች፣ እንደ ኢ-ሜይል አካውንቶች አግባብነት ያላቸውን የስቴት፣ የአካባቢ፣ እና የፌደራል ህጎችን በመጠበቅ/በማክበር ስለመጠቀም የሚጠበቁ ሥርአቶችን ይደነግጋል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ IID-RA፣ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የትምህርት አውታሮች ስለሚሰራጩ/Cablecast/ ፕሮግራሞች

ይህ ደንብ በሜሪላንድ ስቴት ተፈላጊ የሆነዉን እና የሞንጎሞሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የተቀበለው/የተስማማበት ሁለገብ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ለሁሉም ተማሪዎች መሰጠት እንዳለበት ቅደም ተከተሎችን ይዘረዝራል።

የMCPS ደንብ IGP-RA፣ አጠቃላይ የጤና ትምህርት ማስተማርያ ፕሮግራም

ይህ ደንብ በሜሪላንድ ስቴት ተፈላጊ የሆነዉን እና የሞንጎሞሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የተቀበለው/የተስማማበት ሁለገብ የጤና ትምህርት ፕሮግራም ለሁሉም ተማሪዎች መሰጠት እንዳለበት ቅደም ተከተሎችን ይዘረዝራል።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS )ደንብ IKA-RA፣ የትምህርት ውጤት/ማርክ አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

ይህ ደንብ ማርክ አሰጣጥንና-የሪፖርት አቀራረብ ሂደቶችን በተመለከተ ከሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) እና በሜሪላንድ ስቴት በደረጃ ስርአተ ትምህርትና ግምገማዎች ጋር በማቀናጀት የተማሪ ግኝትን/የምህርት ክህሎትን በትክክል የሚያንፀባርቁ ማርክ አሰጣጦችን ያንጸባርቃል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ IKB-RA፣ የቤት ስራ ቅደም ተከተሎች

ይህ ደንብ ስለቤት ስራ ቅደም ተከተሎችና የሚሰጡ ስራዎች ዝርዝር መመርያ ይሰጣል። በተጨማሪም በኃይማኖት ምክንያት ተፈቅዶላቸው ትምህርት ያመለጣቸው ተማሪዎች የማካካሻ ቤት ሥራ የመስራት እድል እንደሚሰጣቸው ይገልጻል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ IKC-RA፣ የክፍል ትምህርት ማርክ/ነጥቦች አማካይ ውጤት(GPA) እና Weighted Grade Point Averages/ የተመዘነ የአጠቃላይ ነጥቦች ማርክ አማካይ (WGPA)

ይህ ደንብ የክፍል ማርክ አማካይ ነጥብ እና የተመዘነ የአጠቃላይ ማርክ አማካዮች ውጤት አወሳሰንና ለአሁንና ለወደፊት ቀጣሪዎች እንዲሁም እንደ ማመልከቻና የመቀበያ ሂደት አካል የሚጠይቁት ከ2ኛ ደረጃ በላይ ላሉ የትምህርት ተቋሞች ዘግቦ ለማስተላለፍ ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation IOE-RA ስለ ነፍሰጡር እና ወላጅ የሆኑ ተማሪዎች ትምህርት የመቀጠል መመሪያዎች፡ ፡

ይህ መመሪያ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚማሩ ነፍሰጡር እና ወላጅ ተማሪዎች በትምህርት ለመቆየት እንዲችሉ በት/ቤት ትምህርታቸውን ለመቀጠል የሚያስችላቸውን የአፈጻጸም ሥርአት ቅደምተከተሎች፣ እንደአግባቡ ከፌደራል እና ከስቴት ህግ ጋር የሚጣጣም ኃላፊነት ስለመስጠት ይደነግጋል።

MCPS Regulation IOE-RB, የሽግግር ማስተማር አገልግሎት/Interim Instructional Services

ይህ መመሪያ በሜሪላንድ ህግ መሠረት በታወቀ አካላዊ ወይም የአእምሮ የጤና ሁኔታ ምክንያት በተመዘገበ(ች)በት የ MCPS ትምህርት ቤት ሊሳተፉ ያልቻሉ ተማሪዎች የ MCPS የትምህርት መስፈርት እንዲያሟሉ ስለ ሽግግር የማስተማር አገልግሎት (IIS) የትምህርት አሰጣጥ ሂደት ይደነግጋል።

MCPS Regulation IPD-RA፣ የትምህርት ጉዞ ፕሮግራሞች፣ የመስክ ጉዞዎች፣ እና የተማሪዎች ድርጅት ጉዞዎች

ይህ ደንብ ስለ መስክ ጉዞዎች፣ ስለተማሪ ድርጅት ጉዞዎች፣ እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚተገበር የትምህርት-ጉዞ ፕሮግራሞች፣ እና እቅድ ማዘጋጀት፣ ፈቃድ/ይሁንታ ስለማግኘት፣ እና የተፈቀዱ ጉዞዎችን ስለመተግበር ይዘረዝራል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS ) ደንብ IOA-RA፣ የከፍተኛ ተሰጥኦና የላቀ ችሎታ ትምህርት

ይህ ደንብ የከፍተኛ ተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ ላላቸው ትምህርት መመርያ ተግባራዊ የሚደረግበትን ቅደም ተከተል ይዘረዝራል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ IQA-RA፣ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በት/ቤቶች መካከል የአትሌቲክ ፕሮግራሞች (High School Interscholastic Athletic Programs) አስተዳደር

ይህ ደንብ በMontgomery County 2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች መካከል የሚከናወን አትሌቲክስ ካውንቲ-አቀፍ የት/ቤቶች ፕሮግራሞች አስተዳደር ስልጣን ያብራራል። የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት አትሌቲክስ ገፅታዎች የሚመለከቱ ፕሮግራሞች፣ ህጎች፣ እና መመርያዎች በ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት አትሌቲክስ የመምሪያ መጽሐፍ ውስጥ (MCPS High School Athletic Handbook) ተካትተዋል፣ ይህም በርእሰ መምህሩ/ሯ ፅ/ቤት እና በእያንዳንዱ 2ኛ ደረጃ ትም/ቤት የሚድያ ማእከል ይገኛል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ IQB-RA፣ ከስርአተ ትምህርት-ውጭ እንቅስቃሴዎች

ይህ ደንብ ከስርአተትምህርት-ውጭ እንቅስቃሴ ፕሮግራምን ለመመስረትና ለማስተዳደር/ለመምራት መስፈርቶችን ያስቀምጣል።

MCPS ደንብ IQD-RA፣ ከስርአተ ትምህርት-ውጭ እንቅስቃሴዎች ላይ ለሚሳተፉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አካዴሚያዊ ብቃት

በዚህ ደንብ ላይ የተመሰረተው ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ማሟላት የሚገባቸውን/ብቃት ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ IQD-RB፣ ከስርአተ ትምህርት-ውጭ እንቅስቃሴዎች ለሚሳተፉ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች አካዴሚያዊ ብቃት

በዚህ ደንብ መሠረት ለመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ብቃት ቅደም ተከተሎች ተቀምጠዋል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation IRB-RA፣ በት/ቤት በጎ ፈቃደኝነት

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የወላጅ/ሞግዚት እና የማህበረሰብ በጎፈቃድ አገልግሎቶችን ስለማበረታታ እና በውጤታማነት የመጠቀም ሥርአት/ቅደምተከተሎችን ይደነግጋል።

MCPS ደንብ ISB-RA፣ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመመረቅ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

ይህ ደንብ የስቴት እና የካውንቲ ለመመረቂያ ተፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን እና የአፈፃፀም ቅደም ተከተሎችን ያመለክታል። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የኮርስ መጽሔት ላይ ተጨማሪ ዝርዝር ለማግኘት ይችላሉ።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ JEA-RA፣ የተማሪ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት

ይህ ደንብ ከት/ቤት ቀሪ የሚሆኑ ተማሪዎችን መቅረትን እንዳያዘወትሩ ክትትል ስለማድረግ፣ በይቅርታ የሚታለፉበት ሁኔታ፣ ክትትል ስለማድረግና የሚቀሩባቸውን ቀናት መዝግቦ መያዝ፣ መቅረትን ስለማሻሻል ተግባራዊ የሚሆኑ አግባብነት ያላቸውን ን/ክፍሎች ለይቶ ያስቀምጣል፣ ክትትልን ለማሻሻልና ከተማሪዎችና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ለመከታተል ቅደም ተከተሎችን ይገልጻል።

የ MCPS ደንብ JEA-RC፣ የአለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ

ይህ ደንብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል የሚከናወኑ የውጭ፣ እና ዓለም አቀፍ ተማሪዎችን ምዝገባ እና የምደባ ሂደቶችን ይደነግጋል።

የ MCPS ደንብ JEA-RE ፣ በትምህርት ክፍያ ላይ የተመሠረተ ምዝገባ

ይህ ደንብ ከሚማሩባቸው ክፍሎች ለመውጣትና ከት/ቤት ለዘለቄታው ለማቋረጥ ተማሪዎች መከተል ያለባቸው ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል። እንደዚህ ለመሳሰሉት እርምጃዎች የጊዜ ገደቦችን ይገልፃል ለትምህርት ውጤት/ማርኮችና ለክሬዲቶች አሰጣጥም መመርያዎችን ያስቀምጣል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation JEE-RA፣ የተማሪ መዛወር እና አስተዳደራዊ ምደባዎች

በዚህ ደንብ ላይ ተማሪው/ዋ ከተመደበ(ች)በት የአካባቢ ት/ቤት ወደ ሌላ ት/ቤት ለመዛወር ስለሚቀርብ ጥያቄ ቅደም ተከተል/ስነተግባር ተገልጿል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶችና ኃላፊነቶች

ይህ መመርያ የቦርድ መመርያ JFA፣ የተማሪ መብቶችና ኃላፊነቶች አተገባበር ቅደም ተከተሎችን ይሰጣል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ደንብ JGA-RA፣ የመማርያ ክፍል አስተዳደርና የተማሪ ስነምግባር እርምት እርምጃዎች

ይህ ደንብ ጤናማ እና ለመማር አመቺ ሁኔታዎችን ለማዳበር የተቀየሱ በመማርያ ክፍል ውስጥ ዘላቂ የሆኑ ፅኑ የዲሲፕሊን እና የቁጥጥር ሥርአት ለመዘርጋት የሚያስችሉ ቅደም ተከተሎችን ይገልጻል። ደንቡ በዚህ ሰነድ አግባብነት በሞንጎሞሪ ካውንቲ (Montgomery County) የትምህርት ማህበር እና በቦርዱ መካከል ባለው ስምምነት መስረት የርእሰ መምህሩ(ሯ)ን ኃላፊነቶች በሚመለከት ግልጽ/ዝርዝር አቅጣጫዎችን ያሳያል።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS )ደንብ JGA-RB፣ ስለ እገዳና ስንብት

ይህ ደንብ በተማሪዎች ላይ ስለሚደረግ እገዳ እና ስንብት የስቴቱን ህግ በስራ ላይ ያውላል፣ ስለሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ሰራተኛ ሃላፊነቶች የሚገልፁ ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል፣ በአሰራር ሂደት ላይ የተማሪዎች መብቶችን ያብራራል፣ እና የአቤቱታ መንገዶችንም ይጠቁማል።

የ MCPS ደንብ JGA-RC, ስንክልና ያለባቸውን ተማሪዎች ስለማገድና ማባረር/ማሰናበት

ይህ ደንብ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራሞች Individualized Education Programs (IEPs) የሚገኙ ተማሪዎችና ለRehabilitation Act of 1973/ የማገገሚያ ህግ አንቀጽ 504 የታቀፉ ተማሪዎች እገዳና ስንብትን የሚመለከቱ በፌደራል ህግ ስር የሚገኙ መመዘኛዎችን ይገልፃል/ያብራራል።

MCPS Regulation JGB-RA፣ ፍተሻ እና ውርስ/Search and Seizure

ይህ ደንብ ተማሪዎች የMCPS ደንብ የጣሰ የማይገባ/አደገኛ ነገር ይዘዋል ተብሎ በሚጠረጠሩበት ነገር ፍተሻ ስለማድረግና በጥርጣሬ ፍተሻ የተገኙ ነገሮችን ስለመውረስ በዝርዝርና በግልጽ የተቀመጠ መመሪያ ነው።

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation JHC-RA፣ ስለ ህፃናት መጎሳቆል እና ትኩረት መነፈግ ምርመራ እና ሪፖርት ማድረግ**

ይህ ደንብ ህፃን/ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁሉንም የሰራተኛ አባላት የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን በመወከል ያዩትን ሪፖርት አቅራቢዎች፣ ስለ ሃላፊነታቸው፣ የህፃን/ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነትን ምልክቶች እንዴት ማወቅ እንደሚቻል፣ እናም የሜሪላንድ ስቴትን ህግን አለማክበር ስለሚያስከትለው መዘዝ ለማሳወቅ እና ለማሰልጠን  የሚወስዳቸውን ሂደቶች ይገልፃል። ይህ ደንብ በሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የሰራተኛ አባለት ተፈፀመ የሚባል የህፃን/ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት፣ ወይም ሌላ ተገቢ ያልሆነ ስነምግባር ጥቆማዎችን/ጥርጣሬዎችን ለመመርመር MCPS የሚከተላቸውን ሂደቶች በተጨማሪ ይገልፃል።

MCPS Regulation JHF-RA፣ **ተማሪን ጉልበት/ሥልጣን ተጠቅሞ ማጥቃት-ጭቆና**/Student Bullying፣ **ትንኮሳ**/Harassment፣ **ወይም ማስፈራራት**/ Intimidation

ይህ ደንብ ት/ቤቶች ለመማርያ ሰላማዊ ቦታ ይሆኑ ዘንድ ከወከባ፣ ከማስፈራራት እና ከማሸማቀቅ ነፃ የሆነ አካባቢ ለማስፈን MCPS ያለውን ቁርጠኝነት ይገልፃል። ደንቡ "ስለ ወከባ፣ ማስጨነቅ፣ እና ማስፈራራት" ይገልፃል እንዲሁም መከላከል፣ ጣልቃ-ገብነት፣ መዘዞች፣ እና የመፍትሔ እርምጃዎች፣ እናም የማሸማቀቅ፣ የወከባ፣ እና የማስፈራራት ተግባርን ሪፖርት የማቅረብ ቅደም ተከተል ደረጃዎችን ያስቀምጣል።

**የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች** (MCPS) **ደንብ** JHG-RA፣ **ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ ወይም ተመሳሳይ አጥፊ ወይም ህገወጥ የቡድን ስነምግባር መከላከል**

ይህ ደንብ የሚገልጸው የትምህርት/አካዴሚያዊ ስኬት እና ማህበራዊ እድገት የሚጎለብቱት ተማሪዎችና ሰራተኞች ሰላም እንደሰፈነ ሲሰማቸው ነው የሚለውን የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) እምነት ይገልፃል። ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ ወይም ተመሳሳይ አፍራሽ ወይም ሕገ-ወጥ የቡድን እንቅስቃሴዎች (የወሮበላነት-ስነምግባሮች) በት/ቤቶች ሰላማዊ የሥራ ሂደት ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ። ደንቡ ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ የመከላከያ ተግባሮች፣ እና የጣልቃገብ እንቅስቃሴዎችን ይገልፃል። ለመከላከል የሚደረጉ ቅደምተከተሎች፣ ጣልቃ ገብነት፣ መዘዞቹ፣ የሪፖርት/የጥቆማ ቅደም ተከተሎች፣ የምርመራ ቅደም ተከተሎች እና የድጋፍ አገልግሎቶችን ቅደም ተከተሎች ይገልጻል።

**የ**(MCPS) **ደንብ** JIA-RA፣ **የላቀ ትምህርት ማህበረሰብ እና የልቀት ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች**

ይህ ደንብ በመካከለኛ እና በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የልቀት ትምህርት ስርአት፣ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ደግሞ የላቀ ማህበረሰብ ስለማቋቋም ቅደም ተከተሎችን ይሰጣል።

**የ**(MCPS) **ደንብ** JNA-RA፣**ለተማሪዎች ከትምህርት ጋር የተገናኙ ወጪዎች**

ይህ ደንብ የተማሪዎች የኤኮኖሚ ሁኔታዎች ሳይገድባቸው፣ ሁሉንም ኮርሶች እንዲማሩ/እንዲያገኙ ማስቻል፣ ለኮርሶች የሚያስፈልጉ የትምህርት ቁሳቁሶች፣ እና የትምህርት ፕሮግራም ለሁሉም ተማሪዎች የሚቀርብበትን ስርአት ይገልጻል።

**የ**(MCPS) **ደንብ** JNA-RB፣ **ከተማሪ የፋይናንስ ክፍያ/ግዴታዎችን መሰብሰብ**

ይህ ደንብ የተማሪ የፋይናንስ ግዴታዎች መመርያዎችን ይዘረዝራል። የ(MCPS) ንብረት በመጥፋቱ ወይም በመበላሸቱ ለመተካት ወይም ለመጠገን፣ ወይም ያልተከፈሉ የተማሪ እዳዎችን ለሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ስለመክፈል።

**የ**(MCPS) **ደንብ** JOA-RA፣ **የተማሪ ማህደር/መዝገቦች**

ይህ ደንብ ስለ ተማሪዎች መረጃ አሰባሰብ፣አያያዝ/ጥበቃ፣ እና ስርጭት ሃላፊነቶች የሚመለከት ስርአት ይገልጻል።

MCPS Regulation JPA-RB፣ **ደህንነት እና የምልመላ ፕሮግራሞች፡- ሊድ/** Lead፣ **መስማት፣ እና ማየት**

ይህ መመሪያ  በ ሊድ/Lead የመመረዝ አደጋ ስለተጋለጡ ተማሪዎች እና የመስማት እና የማየት ችግር የሚኖርባቸውን ተማሪዎች የመመልመል እና ለመስማትና ለማየት ያልቻሉ ተማሪዎችን ክትትል ለማድረግ ለመመልመል የስቴት እና የፌደራል መመሪያዎችን ተግባራዊ ስለማድረግ አስፈላጊ መስፈርቶችን ያስቀምጣል። ይህ መመሪያ በተጨማሪም በትምህርት ቤት እና በየቢሮዎቹ የመጠጥ ውኃ ጤናማነት ከስቴት እና ከፌደራል መመሪያዎች ጋር የሚጣጣሙ ቅደምተከተሎችን ያስቀምጣል።

MCPS Regulation JPG-RA፥ **ጤነኛ ቁመና፡- የአካል እና የአመጋገብ ጤንነት**

ይህ ደንብ በት/ቤት ደረጃ ስለ ጤናማነት አማካሪ ቡድን እና ስለ ጤና እንቅስቃሴን እንደ ስሜታዊ እና ማህበራዊ ደህንነት በቅንጅት ማስኬድ በትምህርት ቤት ስለ ጤንነት መሻሻል ከሚደረጉ ተግባሮች አንዱ ሆኖ እንዲያዝ ይደነግጋል። ደንቡ በተጨማሪም አሁን በመካሄድ ላይ ያሉ የጤና ትምህርት፣ ስነ-አመጋገብ ትምህርት፣ የአካል እንቅስቃሴ ትምህርት፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ በተመላሽ ክፍያ የት/ቤት ምግብ ፕሮግራም፣ እና ከተመላሽ ክፍያ ምግብ ውጭ ለሚገኙ ተማሪዎች የት/ቤት ምግብና የሚጠጡ ነገሮች ፕሮግራም አሠራርን ይገልጻል።

**የ**(MCPS) **ደንብ** KBA-RB፣ **የትምህርት አላማዎች እና የ**MCPS **ድረ-ገጽ/የመረጃ መረቦች አስተዳደር**

ይህ ደንብ ለሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ድረ-ገፅ ቅርፅና ይዘት መዋቅር ይደነግጋል። ድረ-ገፁ የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን (MCPS) ትምህርታዊ አላማ ማገልገሉን ያረጋግጣል የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን (MCPS) ሰራተኞችና ተማሪዎችን የግል ገመና (privacy) ስለመጠበቅ መቆጣጣርያ ስልቶችን ይደነግጋል።

**የ** MCPS **ደንብ** KEA-RA፣ **በፖለቲካ ዘመቻ ተሳትፎ ማድረግ እና የምርጫ ቁሳቁሶች ስርጭት**

ይህ ደንብ በፖለቲካ ዘመቻና እንቅስቃሴ ስለ ተማሪ ተሳትፎ መስፈርቶች እና ለተሳትፎ ፈቃድ ማግኛ ቅደም ተከተሎችን ይገልጻል።

**የ** MCPS **ደንብ** KLA-RA፣ **ከህዝብ ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ምላሽ ስለመስጠት**

ይህ ደንብ ከህዝብ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ወድያውኑ በፍትሃዊነት፣ በርትአዊነት የመያያዝና የመፍታት ቅደም ተከተሎችን ይገልፃል። ደንቡ በተቻለ መጠን ኦፊስዬላዊ/መደበኛ ያልሆነ የቅሬታ አፈታት ያበረታታል፣ እናም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ይግባኝና ድህረ እይታ ሊደረግባቸው የሚያስችል ቅደም ተከተል ያስቀምጣል።

# የቃላት ፍቺ ዝርዝር እና ማስታወሻዎች

**አጓጉል/መጥፎ አጠቃቀም**

1. ማናቸውም የአካል መቁሰል፣ በግልጽ የሚታይ ባይሆን እንኳ፣ የልጅ ወይም ለጉዳት የተጋለጠ/ች ጎልማሳ የአእምሮ መቁሰል/መጎዳት በማናቸውም በጊዜያዊነትም ይሁን ወይም በቋሚነት በሚያሳድግ-በምታሳድግ ወይም ስለልጁ እንክብካቤ ለማድረግ ወይም ለመቆጣጠር ሃላፊነት ያለበ(ባ)ት ጎልማሳ ሰው*፣ የልጁ/ጅቷ ወይም ለጉዳት የተጋለጠ/ች ጎልማሳ ጤንነት ወይም ደህንነቱ/ቷ ተጎድቶ ቢሆን ወይም ለጉዳት በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጠ መሆኑን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ሲኖሩ።
2. ልጅን ወይም አቅመደካማ አዋቂ ሰው በዘላቂነት ወይም በጊዚያዊነት የመንከባከብ ወይም የመጠበቅ ሃላፊነት ያለው ማንኛውም ግለሰብ በልጅ እና በደካማ አዋቂ ሰው ላይ የተፈፀመ ማንኛውም ፆታዊ የመድፈር ተግባር ወይም ተግባሮች (አካላዊ ጉዳቶች ይድረሱም አይድረሱም) ፣ የዘመድ ፆታዊ ድፍረት/ግንኙነት፣ በማስገደድ የፆታ ግንኙነት መፈጸም፣ ወይም በማንኛውም ደረጃ የፆታ ጥቃት፣ ግብረ ሶዶም ወይም ከተፈጥሮ ውጭ የፆታ ልምዶችን በልጅ ወይም አቅመደካማ አዋቂ ሰው ላይ የሚፈጸም፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም። በልጆች ላይ የሚፈጸም ፆታዊ መድፈር/የማስነወር ሁኔታዎች :- አባብሎ ወይም በአመፅ የጾታ ግንኙነት መፈጸም፣ ሰውነትን እርቃን ማጋለጥ፣ ብልት ማየት/ማሳየት፣ በሌሎች እየተከናወነ በሚታይ ፆታዊ ግንኙነት/አሰራር እርካታ፣ ፆታዊ ማሻሸት፣ ለፍትወት ማነሳሳት ፣ መሳም፣ መደባበስ፣ በማን ኛውም ደረጃ የፆታ ወንጀል፣ አስገድዶ ግብረስጋ መፈፀም፣ ግብረ ሰዶም፣ ሽርሙጥና፣ ማቃጠር፣ ወይም አንድን ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው ለፆታዊ ትርእይት፣ ስእል፣ ፊልም፣ ማደፋፈር ወይም ማጥመድ፣ ወይም በህግ የተከለከለ ሆኖ ሳለ ልጅን ማጋለጥ ወይም ከአንድ የተመዘገበ ፆታዊ እጥቂ ጋር አብሮ እንዲኖር ወይም አዘውትሮ እንዲቆይ በማድረግ ማገናኘት ወይም ማድረግን የሚያካትት ሲሆን በዚህ ብቻ ግን አይወሰንም ።
   * በቋሚነትም ወይም በጊዜያዊነት ልጅን ወይም አቅመደካማ አዋቂ ሰውን የመቆጣጠር/የመንከባከብ ሃላፊነት የተሰጠው ሰው የሚያካትተው:- ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ አባል፣ ጎረቤት፣ የ(MCPS) ሠራተኛ፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭ ወይም በኮንትራት የሚሰራ፣ በኃላፊነት ደረጃ ላይ የተቀመጠ ሰው ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው፡፡

**ስር የሰደደ /chronic/**
በተደጋጋሚ የሚከሰት የስነምግባር መገለጫ

**በትብብር**
ከሌሎች ጋር አብሮ በመስራት የተፈፀመ

**የምረቃ ስነ-ስርአት**
የትምህርት ዓመት ማብቂያ ላይ ዲግሪ የመሸለም ወይም ዲፕሎማ የመስጠት ስነ-ስርአት

**የግዴታ**
የሆነ ነገር ለማከናወን መገደድ ወይም መገፋፋት

**የቀጠለ/continuum**
በተከታታይ ቢያንስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አማራጮች ያሉት

**አወዛጋቢ**
በርካታ ውይይት፣ አለመግባባት፣ ወይም ጭቅጭቅ የሚያስከትል

**ባህላዊ ጥበብ**
አንድ ሰው ስለራሱ ባህል የበለጠ ለማወቅና በጥልቀት ለመረዳት አዘውትሮ ጥረት እንደ ሚያደርገው ሁሉ የሌሎችንም በርካታ ባህሎች ለማወቅና ማክበር መጣር አድናቆትን፣ መረዳትን፣ እንዲሁም በአንድ ድርጅት ውስጥ በሚኖሩ ግንኙነቶች፣ ባህልን ለማስተዋወቅ/ለመግለጽ፣ ድርጅትን ለማጠንከርና ማህበረሰቡንም በበርካታ ባህል ታጅቦ እንዲጠነክር ድጋፍ ይሰጣል።

**ክምችት**
በአብዛኛው ቀስ በቀስታ መሰብሰብ፣

**ተወካይ**
ለኃላፊነት/የሥራ ቦታ የተሰየመ ወይም የተመረጠ(ች) ግለሰብ

**ለውሳኔ መደረግ ያለበት ጥንቃቄ**
በራስ አስተሳሰብ የመወሰን ወይም እርምጃ የመውሰድ ስልጣን ወይም መብት

**መድልዎ**
በቅንዓት ወይም በምቀኝነት ምክንያት የሚነሱትን ድርጊቶች ጨምሮ ግለሰቦች ላይ ያነጣጠረ በግላዊ ሁኔታ/ባህርይ ወይም በይሆናል ላይ የተመሰረት ጥላቻ፣ ረብሻ፣ ደንታቢስነት፣ ንቀት፣ ወይም በቃላት/በንግግር ማንቋሸሽ፣ ማበሻቀጥ፣ ማስፈራራት፣ አካላዊ ሁከት፣ ማወክ፣ እንቅፋት መፍጠር፣ ንብረት ማፈራረስ/ማውደም፣ ብቀላ፣ የትምህርትና ሥራ በሠላም እንዳይካሄድ የሚያስተጓጉል ተግባራት። አድልዎ:- ላይላዩን አድሎአዊነት የሌለው የሚመስል ነገር ግን ግለሰብ ባለበት ሁኔታ ወይም የተገመቱ ግላዊ ሁኔታዎች ላይ በመመ ስረት ተገቢ ያልሆነ ተፅእኖ ያላቸው ስነምግባሮችን ወይም ልምዶችን በተጨማሪ ያካትታል። አድልዎ:- ዘረኝነትን፣ ፆተዊ ትምክህተኛነት/sexism፣ እና ድርጅታዊ ስር የሰደዱ አግባ ብነት የሌላቸው ጥላቻዎችን ከሞላ መገለጫዎቻቸው ጋር ያካትታል።

**እኩልነት ማስፈን**
ግዴታን ለመወጣት በሚደርገው ጥረት ሁሉም ተማሪ እና የሥራ ባልደረቦች ስለግላዊ ማንነ ታቸው ወይም በይሆናል ተፈርጀው ሳይሸማቀቁ ያሉበትን ሁኔታ አሸንፈው የተሻለ እድል ላይ ለመድረስ ጠንካራ የጋራ መስፈርት በመያዝ ለአካደሚክ እና ለሥራ ስኬታማነት መቆም አለባቸው።

**መድረክ**
የስብሰባ ቦታ

**ብልግና/ነውረኛነት**
በአጠቃላይ ተቀባይነት ያላቸው የመልካም ስነምግባር መለኪያዎችን የሚጻረሩ የሚፈጸሙ ነገሮች

**ህገ ወጥነት**
ህግን ወይም መመርያን የመጣስ ተግባር

**የሚያሰክሩ-የሚያፈዙ ነገሮች**
አልኮል ወይም ሌሎች እፆች

**ጥላቻና ቅናት መፍጠር**
ተቀባይነት የማይኖረው፣ ህገወጥ አድሎ ወይም ኢ-ፍትሃዊነት

**ከወሲብ ጋር የተገናኘ ብልግና**
ጾያፍ-ብልግና-ስድ ወይም አሳፋሪ-አስነዋሪ

**ስም አጥፊነት**
ሆንተብሎ፣ ሃሰተኛ፣ ወይም በፅሁፍ ወይም በቃላት፣ በስእሎች ወይም በሌላ በአፍ ወይም በሰውነት እንቅስቃሴ የሌላን ሰው መልካም ስም የማጉደፍ ተግባር

**ክፉ/ተንኮለኛ/ምቀኛ**
ሆን ተብሎ ያለምንም መነሻና ምንም ሳይነኩት/ሳይነኳት

**በቁሳዊ ነገሮች**
በሚያሳስብ ሁኔታ፣ በሚያሰጋ ደረጃ

**ቸልተኝነት**
ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ሰው በጊዜያዊነት ወይም ለዘለቄታ የመጠበቅ ወይም የመንከ ባከብ ኃለፊነት ያለበት ግለሰብ የሚከተሉትን የእንክብካቤ ወይም የመቆጣጠር ሁኔታዎች የሚጠቁም:- አንድን ልጅ ወይም አቅመደካማ አዋቂ ሰው ያለጠባቂ ጥሎ መሄድ፣ ወይም አግባብ ያለው እንክብካቤ ያለመስጠት፣ ወይም ጥንቃቄ አለማድረግ ጉድለት፣ ወይም ተገቢነት የሌለው አያያዝ ሁኔታ ወይም የጥንቃቄ ጉድለት፣

1. የልጁ/የልጅቱ ወይም የደካማ አዋቂ ሰው ጤንነት ወይም ደህንነት መጎዳቱ ወይም ለጉዳት አስጊ ሁኔታ ላይ መገኘቱ፣ ወይም
2. በልጅ ወይም በደካማ አዋቂ ሰው ላይ የአእምሮ ጉዳት ወይም ለጉዳት አስጊ ሁኔታ።

**ፀያፍ/ስድነት**
ግብረገብነት የጎደለው፣ አስቀያሚ፣ ባለጌ

**መለያ ባሕርያት**
ግለሰባዊ ባህሪዎች ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሐረግ፣ ብሄራዊ አመጣጥ፣ ዜግነት፣ ጎሳ፣ ሃይማኖት፣ የስደት ሁኔታ፣ ጾታ፣ ጾታዊ ማንነት፣ የሥርዓተ-ፆታ መግለጫ፣ የጾታ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ አወቃቀር/የወላጅነት ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ)፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ፣ እና አካላዊ፣ ድህነት እና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ቋንቋ ወይም ሌላ በሕጋዊ ወይም በሕገ -መንግሥት የተጠበቁ ባህሪዎች ወይም ግንኙነቶች የመሣሰሉትን ያጠቃልላል።

**ፀያፍ አነጋገር**
ያልታረመ፤ ስድ፤ ምግባረ ብልሹ፤ ፀያፍ፤ ባለጌ

**ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ**
በህብረተሰብና በአኮኖሚያዊ ታሳቢዎች መካከል ያለ ግንኙነትን የሚመለከት

**በአመርቂ ሁኔታ**
በቂ፣ በርካታ፣ ወይም ልክ/መጠን፣ ብዛት

**ይተካል/ተተክቷል**
በስልጣን፣ በሃላፊነት፣ በውጤታማነት፣ በተቀባይነት መተካት

**ማባባስ/ጣልቃ መግባት**
ማባባስ/ጣልቃ መግባት፣ በተለይ ልዩነት ለመፍጠር፣ ለመጉዳት፣ ወይም ለማበላሸት

**አስነዋሪ/ፀያፍ**
ያልታረመ፤ ስድ፤ ምግባረ ብልሹ፤፤ ፀያፍ፤ ባለጌ

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኢሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Maryland's Largest School District

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

ህትመት፡- Department of Materials Management for the Office of Student and Family Support and Engagement

0850.22ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 9/22 • NP